ማውጫ

የፍትሐ ብሔር ፍትህ ስርዐትና ህገ መንግስቱ

አዘጋጆች ፦ አቶ ውብሸት ሸፈራው
አቶ ኃይሌ አብርሃ

1. መግቢያ ----------4
2. አላማ----------4
3. የፍትሐ ብሔር ፍትህ ስርዓትና ህገ መንግስቱ----------6
4. ንፅፅራዊ ምልከታ----------8
የሲቪል ሎው ስርዐት----------8
የኮመን ሎው ስርዐት----------10
5. የፍታሐ ብሔር ፍትህ ስርዐት በኢትዬጵያ----------12
የህግ ማዕቀፍ----------12
የህገ መንግስቱ የፍታሐ ብሔር ህግ----------12
የቤተሰብ ህግ----------15
የንብረት ህግ----------18
የግዴታዎች ህግ ----------24
- የውል ህግ እና አሠሪና ሠራተኛ ህግ----------
- የውል ሣይኖር ኃላፊነት ህግ
- አላግባብ መበልፀግ ሕግ
5.1.5 የንግድና ሌሎች ህጐች ----------27
5.2. የህግ ምንጮች እና ህጐች ----------29
5.2.1 የታወጀ ህግ ----------30
5.2.2 ባህል ወይም /custom/----------30
5.2.3 ጠቅላላ መርሆዎች /General principles/----------32
5.2.4 የፍርድ ቤት ውሣኔ/ ኬዝ ሎው/----------34
5.2.5 የህግ ምሁራን ፁሑፍ ----------36

5.2.6 ስነ ስርዐት /procedure /----------37
6. ተዋንያን /actors/----------46
7. ጠንካራና ደካማ የፍትሐ ብሔር ስርዐት ----------49
7.1 ጠንካራ የፍትሐብሔር ፍትህ ስርዐት ----------50
7.2 ደካማ የፍትሐ ብሔር ፍትህ ስርዐት እና መፍትሔዎች-----52
7.3 የጉዳዬች አካሄድ አመራር ----------57
7.4 አመራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች----------58
7.4.1 አይነቶች ----------58
7.4.2 ጥቅሙ----------59
7.4.2.1 ቅልጥፍና ----------59
7.4.2.2 ወጪ----------59
7.4.2.3 የሂደቱ ቁጥጥር----------59
7.4.2.4 ግንኙነት ----------60
7.4.2.5 የመፍትሔ አማራጮች----------61
7.4.2.6 ምስጥራዊነት ----------61
7.4.2.7 ዲስኘሊን እና ትኩረት----------61
7.4.2.8 የተከራካሪ እርካታ----------61
7.4.3 ያሉት አደጋዎች ----------62
8. ማጠቃለያ ----------63

1.የስልጠናው አላማ፤

ስልጠኞች ከዚህ ስልጠና በኋላ

- ህገ መንግስቱ ከፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ጋር ያለውን ግንኙነት ይለያሉ
- የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ምንነት ይረዳሉ
- የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደርና ጠንካራ የህግ ማስፈፀም ጥያቄን ይረዳሉ
- የደካማ አፈፃፀም ውጤቶች ይገነባሉ
- ደካማ አፈፃፀምን ለማሻሻል መወሰድ ስለለበት ርምጃ ይረዳሉ፡፡

2.መግቢያ

የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓት እጅግ ሰፊ ቁም ነገርን የያዘ ነው፡፡ በጥቅሉ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓት /civil justice system / በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ የህግ ተቋሚነት፣ የስነ-ስርዓት ህጐችን፣መደበኛ ህጐችን፣ ውሳኔዎችን እና መርሆዎችን ይመለከታል፡፡ ኢትዩጵያ ፌዴራል ስርዓትን የምትከተል እንደመሆኗ መጠን የክልል እና የፌደራል መንግስታታ አሉን፡፡ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓት በኢትድጵያ ማለት በየመንግስታት ያሉ የፍ/ብሔር ተቋማት፣ መሠረታዊ ህጉችና የስነ ስርዓት ህጐችን መቃኘት ማለት ነው፡፡ ሁሉም መንግስታት አንድ አይነት ተቋማት ፣ ህግ ወዘተ አላቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ጉዳዩ ከሀገር ሲወጣም በዛው ልክ ልዩነቱ እና ይዘቱ እየሰፋ ይመጣል፡፡ ስለሆነም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የሀገራችን የፍ/ብሔር ፍትህ ስርዓት ብቻ ሆኖ የጋራ በሆኑት ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ በፊዴራል እና በክልል መንግስታት መገከል ልዩነት ቢኖርም መሠረታዊ ተደርጉ በፀሐፊዎች አልተወሰደም፡፡ የርዕሱ ሰፊ መሆን ቢያንስ በዚህ ፅሑፍ በሁሉም ጉዳዬች ላይ ሁሉንም ነጥብ ለማንሣት አያስችልም / በፅሁፍ ውስጥ ህጐች፣ ሀገራት አልፎ አልፎ የፍ/ብሐር ፍትህ አስተዳደሩ ቢጠቀሱ የስርዓቱን መኖር ለማሳየት እንጅ በህጉ ላይ ትንታኔ ለማድረግ አይደለም፡፡ የሚነሱ ህጐች በሙሉ የራሣቸው ሰፊ ክፍል ጊዜ ያላቸው በመሆኑ ህጉን መጥቀስ ቢያስፈልግ ያለንን የፍ/ብሔር ፍትህ ስርዓታችን እንደ ስርዓት ለማመልከት ብቻ መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡ በሌላ በኩል ፅሑፍ ለማመልከት የሚፈለገው ያለንን የፍትህ ስርዓተ ብቻ ነው፡፡ ከሌላ ሀገር ስርዓት ጋር በንፅፅር የተቀመጡ ጉዳዬች ቢገኝ አንዱን ከሌላው ለማበላለጥ አይደለም፡፡ ፅሁፍ የሚያበላልጠው ነገር ቢኖር ለተቀላጠፈ የኢኮኖሚ እድገት የሚሻለውን መንገድ ብቻ ነው፡፡ የፍትሐ ብሐር የፍትህ ስርዐትን ስንመለከት በዋነኛነት የትኩረት ነጥባችን ህግን በመተርጓም ወይም በመፈፀም የህግ ስርዐቱ ሰላም ፣ብልፅግና፣ እድገት፣ የተሟላ ፍትህ እና የኢኮኖሚ እድገት ምን ያህል አስተዋፆዖ ያደርጋል የሚለው ነው ፡፡

ፅሁፉ በዋነኝነት በሁለት የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው የፅሑፉ ክፍል የሀገራችንን የፍትህ ስርዐት በጥቅሉ የሚያሣይ ነው፡፡ 2ኛው የፅሑፉ ክፍል ደግሞ

የፍትህ ስርዐት በአፈፃፀም ያለበትን ደረጃ ያመለክታል ። በፍትህ ስርዐተ ማሻሻያ ኘሮግራሞች ትግበራ መነሻነት ያለው የፍትህ መሻሻል እንደተጠበቀ ሆኖ የፍትህ ስርዓታችን አፈፃፀም በደካማ ጉኑ የሚገለፀሙ ጕልቶ የመፍትሔ ሃሣብም ይቀርብበታል።

መልካም ንባብ

3.የፍትሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት እና ህገ-መንግስቱ

Civil Justice System and the constitution

በፍትሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ የፍታሐ ብሔር ክርክሮች እንዴት እልባት እንደሚያገኙ ወይም ሊያገኙ እንደሚገባ እንመለከታለን። የፍታሐ ብሔር ጉዳዬች ውሣኔ የሚያገኙበት የራሱ የሆነ መንገድ ያለው ቢሆንም ምንጩ ህገ- መንግስቱ ነው። በፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ልንከተላቸው የሚገቡ በርካታ መርሆዎች አሉ። ተገቢውን የህግ መስመር ተከትሎ መወሰን /due process of law/፣ በፍ/ቤት መቅረብ እና የመስማት መብት /To have a day in court& to be heard/፣ በተፋጠነ ስርዓት ውሣኔ ማግኘት /speedy trial/፣ማስረጃ ማቅረብና ማስመዘን፣በህግ እና በፍሬ ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ ማግኘት ወዘተ በፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙና ሊተገበሩ የሚገባቸው የክርክሩ ሂደት መርሆዎች ናቸው። እነዚህ ፅንሰ ሐሣብ መሰረቶች ደግሞ ህገ መንግስቱ ነው። ስለሆነም በፍትሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ መነሻ እና መድረሻ ነጥቦችን ህገ መንግስቱ ነው ማለት ነው።

ውድ ሰልጣኞች ከዚህ ቀደም በነበሩ የህገ መንግስት ስልጠናዎች ላይ እንደተመለከታችሁት ሁሉ የፍትህ ማስተዳደር ተግባር /administration of justice/ የሁሉም የፍትህ አካላት ኃላፊነት ነው። እኩል ለሆኑት ተመሣሣይ እኩል ላልሆኑት ደግሞ እንደልዩነታቸው የተለያየ ህግ ማውጣት የፍትህ አስተዳደር /legislative Justice/ ነው። ይህ የወጣው ህግ የሚጠብቀው ፍትሐዊ ሚዛን /just balance /በተዛባ ጊዜም ወደ ትክክለኛ ሚዛኑ መመለስም ፍትህን ማስተዳደር ነው። የኃለኛው ሚዛኑን የሳተውን ፍትህ መልሶ ማስተካከል /corrective justice/ ፍትህን በፍትህ አካል ዘንድ ለማስተዳደር መሞከር ነው። የዚህን አይነቱን ፍትህ አስተዳደር ነው በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የምንመለከተው ። በዚህ አይነቱ የፍትህ አስተዳደር ውስጥ አንድ "ጥሩ" ሰው " ሌላው "ጥሩ ያልሆነ ሰው" ላይ ጉዳት ማድረሱ ወይም የተገላቢጦሹ አንድ በተለምዶ "ጥሩ ያልሆነ ሰው" "ጥሩ በሆነው ሰው" ላይ ጉዳት ማድረሱ ለውጥ አያመጣም።ህጉ የሚመለከተው ጉዳት መድረሱን የጉዳቱን መጠን፣ ካሳ የሚያስፈልገው መሆኑን ነው ።ሁለቱን ሰዎች ህጉ በእኩልነት ይመለከትና ሊመልሣቸው የሚፈልጋቸው ጥያቄዎች

አንዱ ጉዳት ማድረሱ እና ሌላው በዚሁ ጉዳት የተጠቃ/የከሰረ / መሆኑን ነው። ህጉ በዚህ መልኩ የተፈጠረውን እኩል ያልሆነ ግንኙነት እኩል ለማድረግ ይሞክራል። ይህም በአብዛኛው በፍ/ቤቶች የሚፈፀም ነው። የዚህ አይነት የፍትህ አስተዳደር መነሻ ምክንያቶች በርካታ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰዎች በግዥና ሽያጭ፣ በብድር/ወልድ-ያለወለድ/፣በመያዣ /moor gage/፣ በአደራ ጠባቂነት፣በኪራይ እና በመሣሠሉት ምክንያቶች ወደውና ፈቅደው በሚገቡባቸው የህግ ግንኙነቶች ሊፈጠር ይችላል። አለዚያም በስርቆት ፣ዝሙት፣ ግድያ፣ አካል ጉዳት ማድረስ፣ስድብ፣ ዝርፊያ እና በመሣሠሉት የተነሣ ተገደው የገቡባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። የመጀመሪያው በውል ህግ ዓይነት የሚመነጨ ሲሆን /Hart "power conferring" የሚለው/ የኋላኛው ውል ሣይኖር ወይም በወንጀል ጉዳይ /Primacy rule of obligation/ አይነት የሚመነጩ ናቸው። በዚህ መልኩ በሚፈፀሙ ድርጊቶች ለደረሰ ጉዳት ህጉ ጣልቃ በመግባት በፍትህ አካላት አማካኝነት ማስተካከል ያደረጋል። በዚህን ጊዜ የፍትህ አካሉ /ዳኞች/ ህጉን በአግባቡ ተፈፃሚ በማድረግ ፍትህን ያስተዳድራሉ። ዳኞች /የሚፈፅሙት/ የሚተገብሩት ህግ ጠቅላላ ይህንና ለእያንዳንዱ ጉዳይ በቀጥታ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል። አለዚያም ጉዳዩን በቀጥታ የሚመለከት ህግ ላይሆን ይችላል። ህጉ በግልፅ የሚያዝ ከሆነ ርትህን /equity / መሠረት በማድረግ መወሰን የሚገባ ሲሆን ይህ በሌለበት ጊዜም ጉዳዩ ለህግ አውጪው ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ሊመጣ ይችል የነበረውን ህግ በመገመት መወሰን ግድ ነው። ርትዕ ወረድ ብለን ከምንመለከተው የኮመን ሎው ሰርዓት ርትዕ ይለያል። በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ውስጥ ርትዕ ቀዳሚ ቦታ የለውም። ተፈፃሚ የሚሆነው በህግ ሲገለፅ ነው። ለምሳሌ ከውል ውጪ ለዳረሰ ጉዳት የካሣውን መጠን በእርግጥ ማወቅ ካልተቻለ በርትዕ እንዲወሰን ህጉ ይፈቅዳል። ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ውጪ ቢያልቅ የሚሻል ከሆነም ይህንን መምራት አለዚያም ፍርድ ቤቱ ከሌሎች የማህበረሰቡ አካላት ጋር በመሆን ለጉዳዩ እልባት መሰጠት የሚችሉ ከሆነም መመልከት ተገቢ ነው። ለተዛቡ ግንኙነቶች ህግን ወይም ርትህን መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቶ ግንኙነቶች ወደ ነበሩበት መመለስ መቻል / መሞከር/ አለዚያም ጉዳት ባይደርስ ሰዎች ሊኖራቸው እሚችለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ... ቦታ እንዲገኙ ማስቻል የፍትህ አስተዳደር ልንለው እንችላለን።

የፍትህ አስተዳደር በወንጀል ፣ በፍ/ብሔር እና እንደ ሁኔታው/ በአስተዳደር ህግ ሊተገበር ይችላል። በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የፍ/ብሔር የፍትህ አስተዳደር ሲሆን በውስጡም የሀገራችን የፍ/ብሔር ተቋማት ማንነት፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ

ህጐች የስነ ስርዓቱ ህጐች፣ ያሉብን ችግሮች እና የመፍትሔ ነጥቦች ይቀመጣሉ። የፍ/ብሔር የፍትህ አስተዳደር ስንል እነዚህ ነጥቦች በሀገር ደረጃ እንደ ስርዓት መመልከትን የሚያጠቃልል ነው።

4. ፅፅራዊ ምልከታ/Comparative analysis /

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በአለማችን ያሉ ዋነኛ የሚባሉ የህግ ስርዓቶችን እንመለከታለን። ንፅፅር በበርካታ ነጥቦች ላይ ማድረግ የሚቻል ቢሆነም መሠረታዊ በሆነው ህግ /Substantive law/ ንፅፅረ ማድረግ የዚህ ፅሁፍ አላማ አይደለም። ለተያዘው የስልጣና ርዕስም አስፈላጊ መስሎ አልታየንም። ንፅፅር በሚደረግበት ጊዜ መሠረታዊ ህግን /የህግ ቁጥርን/ መመልከት የሚቻል ቢሆንም አላማው ስርዓቱን ለመግለፅ / illustrative/ ከሚሆን የሚዘል አይደለም።

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ አሁንም ንፅፅር ሲደረግ አላማው ሙያዊ እና ሳይንሳዊ/ Professional and scientific / ከሚሆን ይልቅ ባህላዊ" /cultural/ አንዲሆን ታስቦ ነው። ስለሆነም ስልጣኖች የሀገራችን የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓት ይረዱና ምን ያህል የሀገር ችግርን ፈቺ እንደሆነ ይረዳሉ ተብሎ ይጠበቃል።

4.1 የሲቪል ሎው ስርዓት

በአለማችን ላይ ያለው የህግ ስርዓት በበርካታ ስርዓቶች የተከፋፈለ ነው። የሲቪል ሎው እና የኮመን ሎው ስርዓት የሚባሉት በአንፃሩ ቀደምትና በስፋት የሚታወቁት ናቸው ። የሲቪል ሎው የህግ ስርዓት የጥናት የህግ ስርዓት ሆኖ ክክርስቶስ ልደት በፊት 450 ዓመት ቀደምት ታሪክ ያለው ነው። በዘመኑ ህግ ከፍተኛ እድገት ማሣየት የጀመረው በሮማን "ጅረስከንሰልት" እየተባሉ ይጠሩ በነበሩትና በህግ የተካኑ ሰዎች ሞያቸው አድርገው በያዙት ጊዜ ነው። በወቅቱ የነበሩ "ያልተማሩ ዳኞች" /lay-judges/ ለያዙት ጉዳይ ወደ እነዚሁ ሰዎች ለምክር በመጡ ጊዜ ከሚሰጡ አስተያየቶች በመነሣት መዳበሩ ይነገራል። ይህም በመሆኑ ከቋሚ ህግ ወደ ተለዋዋጭ ህግ / fixed to flexible/ እና ከተጨባጭ ነገር ተነስቶ ከማሰብ ወደ ረቂቅ /abstract/ ነገር ተነስቶ ማሰብ /ማሰላሰል/ ተሸጋጋሯል። እድገቱ እየዳበረ መጥቶም የሮማን ህግ በጥራዝ /compilation/ መልክ እንዲቀመጥ ሆኗል። ይህም "corpus juries civil" እየተባለ በሚታወቀው 4 ክፍሎች /institutes, digest, codes and novels/ ባሉት ጥራዝ እንዲጠቃለል ሆኗል። ጥራዙ የሚያጠቃልለውን ለመለየት የረዥም ጊዜ ምርጫ /selection/ እና ማግለል

/rejection/ ግድ ብሏል። ይህ የህግ ስርዓት ወደ አውሮፓ ቢስፋፋም መሠረቱ የሆነው አገዛዝ ከወደቀ በኋላ ለረዥም ጊዜ /ለመቶ አመታት/ ጥቅም ላይ ሣይውል ቆይቶ አውሮፓ በ11ኛ ክፍለ ዘመን ባሳየችው የኢኮኖሚ መስፋፋት እንደገና ተፈፃሚ ለመሆን በቅቷል። የኢኮኖሚው መስፋፋት በህግ የመመራትን ብቻ ሣይሆን ተገማች የሆኑ ህግ እንዲኖርና ቀጣይነት ዓይነት ያለው የግጭት መፍቻ መንገድ እንዲኖር በማስገደዱ የመጣ ፍላጐትም ለተግባራዊነቱ ሚና ተጫውቷል። ኢኮኖሚው እድገት ጐን ለጐንም ዩኒቨርስቲዎች /በተለይ የኢጣሊያ/ ይህንን የህግ ስርዓት ከአውሮፓ ለመጡ ተማሪዎቻቸው በስፋት ያስተምሩም ስለነበር ተማሪዎችቹ በተመለሱበት ቦታ ሁሉ እንዲሰፋፋ ሆኗል። ከበርካታ ትችቶች /comments/ እና ፅሁፎቹ ጋርም ይህ የህጉ ስርዓት በአውሮፓ የጋራ ህግ /jus commune/ እንዲኖር አድርጓል። ይህ ማለት ግን ህጉ በሁሉም የአውሮፓ ሀገሮች በተመሣሣይ መልኩ ይፈፀም ነበር ለማለት አይደለም። ከጋራው ህግ ጐን ለጐን የንግድ ተሞክሮ መለያየት፣ የተማከለ መንግስት/ በተለይ በመካከለኛው ዘመን/ አለመኖር የአካባቢ ህጉች ተፈፃሚ እንዲሆንም አድርጓል። ህጉ መሠረታዊ በሆነ መልኩ እንደ አጠቃላይ መመሪያ /guideline/ ያገለገለ ሲሆን በዘመኑ የነበረውን "ውስብስብ" የኢኮኖሚ ስርዓት ለመምራትም ያስቻለ ነው። ይሁን እንጅ በሂደት የብሔረተኝነት /nationalism/ ስሜት እየተስፋፋና ስልጣንም በአንድ ቦታ /Royal power/ እየተሰበሰበ በመጣ ቁጥር የአካባቢን ህግ ብሔራዊ ህግ አድርጐ የማውጣት ፍላጐት ዳብሯል። ይህም በተለይ የተገለፀው ህግን በመፅሐፍ መልክ /Codification/ በማውጣት ነው። በዚህ መልኩ መውጣት ከጀመሩት ህጉች ውስጥ የመጀመሪያውና ዘመናዊው የፈረንሣዩ የፍታሐ ብሔር ህግ መፅሐፍ /civil code/ ነው። በ1804 በናፖልዩን ዘመን የወጣ ሲሆን አሁን በአለም ላይ ያለው የፍታሐብሔር ስርዓት ላይ ወሳኝ ተፅኖ ያሳረፈ ነው።ናፖሊዬን በዘመኑም የወንጀል ፣ የሁለቱ ስነ-ስርዓት ህጐችንና የንግድ መፅሐፎችን አውጥቷል።የመጽሐፍ መነሻ ሰው ባለው የማሰብ /የመመራመር/ ችሎታው ምክንያታዊ የሆነ፣ ግልፅ እና የተጠቃለለ /Rational, clear and comprehensive/ህግ ማውጣት ይችላል የሚል ነው። ይህም ስለሰው፣ ህግ እና መንግስት ለየት ያለ አመለካከት እንዲመጣ ያደረገ ነው። ይሁን እንጅ የህጉ አርቃቂዎች የቀደም የሮማን ህግ ተፅዕኖ የነበራቸው በመሆኑ ህጉ ሙሉ በሙሉ ከሮማን ህግ ስርዓት ነፃ ነበር ለማለት ያስቸግራል።

መፅሐፍ ሲወጣ በተራው ዜጋ ሁሉ እንዲነበብ እና ተራዊ ዜጋ በቀላሉ እንዲረዳው ታስቦ ነው። ይሁን እንጅ ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር፣ የሚመራ ህግ ማውጣት እንደሚያስቸግር በወቅቱም ግንዛቤ ስለነበረ ጠቅላላ መርሆዎችን እንዲይዝ ተደርጓል። ቀጥሎም በተመሣሣይ መልኩ /ነገር ግን ታሪክና የህዝቡን ባህል መሠረት በማድረግ /የህግ መፅሐፍ ሊወጣ ይገባል በሚል እምነት ጀርመን በ1900 ተፈፃሚ መሆን የጀመረውን የፍታብሔር ህንንና ስርዓቷን በመፅሐፍ መልክ አውጥታለች።የፍታሐ ብሔር የፍትህ ስርዓታቸው ከእነዚህ ሀገራት /በጋራ/ የቀዱ ወይም የወሰዱ ሀገራት የሲቪል ሎው ሀገራት ሊባሉ ይችላሉ። እነዚህ በሀገራት በጥቅሉ በዚሁ ሰያሚ ይጠሩም እንጅ በውሰጣቸው ራሱን የቻለ ክፍፍልም አለው በክፍፍሉ ውስጥም እያዳንዱ ሀገር የራሱ የሆነ ልዩ ስርዓት ያለው ሆኖ እናገኘዋልን።

4.2 <u>የኮመን ሎው ስርዓት</u>

በሌላ በኩል የህግ ስርዓታቸው ከእንግሊዝ የወረሱ ሀገራት ይገኛሉ። ኮመን ሎው የህግ ስርዓት የሚከተሉ የሚባሉት ናቸው።የእድገቱም መነሻ ፍ/ቤቶች ባህልን፣ ልማድን፣ ኘሬዚዳንትን መሠረት በማድረግ የሚሰጡት ውሣኔ ነው። ነዋሪዎች ባልተፃፈ የአካባቢ ልማዶች ይተዳደሩ የነበረ ሲሆን ይህ ልማድም ከአካባቢ አካባቢ የተለያየ የነበረ። ሲሆን "ፍርድ ቤት" የሚባለውም መደበኛ ባልሆኑ "ተሰብሣቢዎች" ለግጭቶች ውሣኔ የሚሰጡ ሰዎችን የሚመለከት ነበር። እንደ የአካባቢው በአጋጣሚ / በተአምር/ trial by ordeal/ የመዳኘት ሁኔታም ሰፊ ነበር። ይህንን ሁኔታ ለማስቀረት ሔነር 2ኛ የወንጀል እና የፍታብሔር ጉዳይን በቃለ መሀላ ስር ሆነው በመመርመር ውሣኔ የሚሰጡ ጁሪዎችን /juries/ አቋቋመ። በጐጥ የዳኝነት ቁጥጥርን፣ ዘፈቃዳዊነትን /arbitrariness/ ለማስቀረትም ዳኞች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ክርክሮችን እንዲሰሙም ተደረገ። ዳኞችም በሄድበት ቦታ ያለው ባህል ምን እንደሆነ በመተርጐም ውሣኔ ከሰጡ በኋላ መደበኛ ቦታቸው /ለንደን / ሲመለሱ ጉዳዬቹ ውይይት ይደረግባቸውና ይመዘገቡ ነበር። በሂደትም በተበታተነ መልኩ ውሣኔ ይሰጥባቸው የነበሩ ጉዳዬች በተመሣሣይ መልኩ ውሣኔ እየተሰጠባቸው ለተመሣሣይ ፍሬ ነገርም ተመሣሣይ ውሣኔ እና መርህ መከተልና የጋራ የሆነ ህግ መመሥረት ተጀመረ ። ለዛም ነው የአሁኑ ሰያሜ "የኮመን ሎው" የሚባለውና ስርዓቱም የኮመን ሎው ስርዓት እየተባለ የሚጠራው ። በዚህ የህግ ስርዓት ውስጥ የተፃፈ ህጐች/ አሁን አሁን /ያሉ ቢሆንም ጉዳዬች እልባት የሚያገኙት በመሠረቱ

የቀድሞ ውሣኔዎችን በመፈለግና አስፈላጊ ከሆነም በመተርጐም ነው። በዚህ የህግ ስርዓት ውስጥ ርትዕ /equity / ከህግ ጋር ተመዛዛኝ ቦታ ያለው / የነበረው/ ሲሆን አሁን አሁን ባብዛኛው እየተጣመሩ መጡ እንጂ የህግ /court of law/እና የርትዕ ፍ/ቤቶችም /equity courts/ ተለይተው ይቋቋሙ ነው። የህግ ፍ/ቤቶች በገንዘብ የሚተመን ጉዳት ላይ ውሣኔ የሚሰጡ ሲሆን የርትዕ ፍ/ቤቶች ደግሞ ሌሎች መፍታሔዎች / relief Injection / ይሰጡም ነበር። በኮመን ሎው የህግ ስርዓት ውስጥ ህግን በመፅሐፍ መልክ ፅፎ ማስቀመጡ ያልተለመደ የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን ግን ይህ እየተለመደ ወጥቷል። በአብዛኛው ኮመን ሎው የሚባሉት ውሣኔዎች በዚህ መልክ ይወጡም እንጅ የሲቪል ሎው ስርዓት የሚከተሉ ሀገሮች የሚያወጧቸው ህጐች አይነትም በመፃፍ መልክ ሲወጡ ይታያሉ። የአሜሪካን ህጐች ብንመለከት "ኮመን ሎው" ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ መልኩ በህግ አውጪው ከመጡ ህጐች ጋር ወይም ከህብረተሰቡ አኗኗር ጋር ካልተጋጨ ወይም በህግ አውጭው ባልተሸፈኑ ነጥቦች ላይ ሆኖ እናገኘዋልን። የመጀመሪያ ምርጫቸው የተፃፉ ህግ ነው ማለት ነው። ይህንን መስመር በጥቅሉ የተከተሉ ሀገራት የኮመን ሎው ሀገራት ሲበሉ ስርዓቱ የኮመን ሎው ስርዓት ይባላል።

በአጠቃላይ የህግ የፍትህ ስርዓቶችን በንፅፅር ስንመለከት የአንድ ሀገር ያህል ስርዓት በጥቅሉ ከሌላው ይሻሻል/ ያንሣል/ ለማለት አይደለም። ይህ ተገቢ አይመስልም። አንድ ሀገር ያለው ህግ እና የፍትህ ስርዓቱ የዛው ሀገር ታሪክ፣ ባህል፣ ማህበራዊ እሴቶች፣ እና የህዝቡ ንቃት እና ግንዛቤ መገለጫ ነው ብሎ /መገመት/ ተገቢ ነው። ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ/ indigenization/ ይወጣል እንጂ ምንም አይነት ለውጥ ሳይደረግበት የተገለበጠ ስርዓት ማግኘት ያስቸግራል ። የፍትህ ስርዓቱ የዛው ሀገር ታሪካዊ/ ልምድ/ መገለጫ ነው። የፍትህ አስተዳደሩን ስርዓት ስናጠና/ ስናነፃፅር/ በዛው በስርዓቱ ውስጥ ባለው የባለሙያ /ታሪክ/ ሁኔታ መመልከት እንጂ አስቀድሞ ለአንድ ፍትህ ስርዓት በወገነ /ethnocentric bias/ መመልከት የለብንም።

ሌላው ማንም ሰው ከያዘው ነገር ጋር ያለው የስሜት ትስስር የፍትህ አስተዳደሩን በትክክል ለማየት እንዳይችል ሊገታው አይገባም። የፍትህ አስተዳደሩን በትክክል ለመመልከት አስቀድሞ ከያዙት ጥብቅ ትስስር ወይም ጥላቻ ራስን ማላቀቅ ይገባል። በተመሣሣይ መልኩ የትኛውም የህግ ስርዓት በፍፁም መጥፎ ወይም በፍፁም ጥሩ ነው ከሚባለውም አመለካከት መላቀቅ ይገባል። የትኛውም የፍትህ አስተዳደር ቢሆን ከሌላው ምንም የማይፈልግ /የማይወሰድ/ ፍፁም ጥሩ ሊባል አይችልም። በዚህ

መነሻነትም አንድን የፍትህ ስርዓት በምንመለከትበት ጊዜ ሌላውን ለማመስመገን ወይም ለመኮነን መሆን የለበትም ። ዋናው ትኩረት መሆን ያለበት አንድ ሀገር አንድን የፍትህ አስተዳደር ለምን መረጠ የሚለውን ነው። አንዳንዶች እንደሚሉት "ሁሉም ሀገር የራሱ የሆነ የህግ ስርዓት" ለምን ኖረው? የሚለውን መረዳቱ ነው ጠቃሚው ነጥብ።

ይህንን ነጥብ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሀገራችን ያለው የፍታሐ ብሔር ፍትህ ስርዓት /civil justice system/ ምን እንደሚመስል ቀጥለን እንመለከታለን።ቀጥለን በምንመለከታቸው ነጥቦች ላይ ዝርዝር ትምህርቶች ወደፊት ሊሰጡ እንደሚችሉ በማሰብ ፅሁፍ ስርዓቱን /system/ በሚያሣይ መልኩ ብቻ ይቀርባል።

5 .የፍትሐ ብሔር ፍትህ ስርዓት በኢትዩጵያ

በሀገራችን መሠረታዊ ሊባል የሚችል መልኩ መንግስታት ተቀያይረዋል። የፊውዳሉ ስርዓት በ1966 ዓ/ም ከተወገደ በኋላ ይህንኑ ስርዓት የተካው የደርግ ወታደራዊው መንግስት ስርዓት በተመሣሣይ መልኩ በ1983 ዓ/ም ተወግዷል፡ ፡ወታደራዊ የደርግ ስርዓት ከተወገደ በኋላ ሀገራችን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ተቀብላ በተግባር ያዋለቻቸው መሰረታዊ እሴቶች አሉ። የነፃ ገበያ /ገበያ መሪ ኢኮኖሚ/ ፣ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና የህግ የበላይነት እሴቶች /values/ መሠረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ናቸው። እነዚህን እሴቶች በተመለከተ ስልጣኖች ከዚህ ቀደም በወሰዷቸው የህገ መንግስት እና የፖሊሲ ስልጠናዎች ውስጥ በስፋት የተመለከቷቸው በመሆኑ በዚህ ፅሁፍ በድጋሚ የሚታዩ አይሆኑም። እሴቶች ከማወቅ አንፃር እንዲሁም እሴቶቹ ከማስፈፀም አንፃር ያሉ የህግ ማዕቀፎችንና የአፈፃፀሞችን ብቻ እንመለከታለን።

5.1 የህግ ማዕቀፍ

5.1.1 ህገ መንግስቱና የፍታሐ ብሔር ህግ

በተለምዶ የሲቪል ሎው ሀገሮች አየተባሉ በሚጠሩት ሀገሮች ውስጥ ህጐች መሠረታዊ በሚባል መልኩ በሁለት ይከፈላሉ፤ የመንግስት /public/ እና የግል / Private/ ይህ የህግ ክፍፍል የሲቪል ሎው የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓትን ለመረዳት የሚጠቅም ሲሆን የፍ/ቤት አደረጃጀቶችንም ሲወስን ይታያል። በህግ ትምህርት ቤቶቻቸውም የዚሁኑ አይነት ክፍፍል ያለበት ትምህርት ሲሰጡ

ይታያሉ። የፍ/ቤቶችን አደረጃጀት በተመለከተ የመንግስት ህግ የተባሉትን የሚዳኙ የተለዩ የአስተዳዳር ፍ/ቤቶችን የሚያቋቁሙ አሉ /ፈረንሣይ ጀርመን / የመንግስት ጉዳዬች /ከወንጀል ጉዳዬች በቀር/ በነዚሁ ፍ/ቤቶች ይታያሉ ማለት ነው። በሀገራችን የዚህን አይነት ክፍፍል መሠረታዊ በሚባል መልኩ አናገኝም። በሀገራችን የፍታሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር የግልም ሆኑ የመንግስት ጉዳዬች በፍ/ቤቶች የሚታዩ ሲሆን የተወሰኑ ልዩ የፍታሐ ብሔር ጉዳዬችን ብቻ ለልዩ ፍ/ቤቶች /ውሣኔ ሰጪ አካላት/ ይዳኛሉ። የሆኖ ሆኖ ሁሉም ውሣኔ ሰጪ አካላት ክፍ ሲል በተመለከትናቸው መሠረታዊ እሴቶች ውስጥ ሆነው ውሣኔ ሊሰጡ ይጠበቃል። እሴቶቹም ከህገ-መንግስቱ አንስቶ በልዩ ልዩ ህጐች ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን። በ1987 የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በመግቢያው ላይ የህጉን አላማ ሲያስቀምጥ የኢትዩጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች "ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገታቸው እንዲፋጠን" ቆርጠው መነሳታቸውን ያስምርበታል። ይህንን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን አስፈላጊ ከሆኑት ጉዳዬች ውስጥ አንዱ ኢኮኖሚውን ገበያው እንዲመራው ማድረግ ሲሆን በገበያው ውስጥም ማንኛውም ኢትዩጵያዊ በመረጠው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሰማራ መፍቀድ ሌላው ነው። ህገ መግስቱ የህግ የበላይነት እንዲኙን ፣ ፈጣን የፍትህ ስርዐት እንዲኖር ፣ ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ የሚያስምር በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዐታችን ውስጥ መነሻው ህግ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ሀገሪቱ ተቀብላ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የህግ ሰነዶችም ለፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደሩ ሌላው የህግ ማዕቀፍ ናቸው።

ለፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች ህጐች ውስጥ የፍታሐ ብሔር ህግ / civil code/ የሚጠቀስ ነው። ሀገራችን በ1952 ያወጣቸው የፍ/ህግ ባለቤትነት ናት ። የፍ/ሐብሔር ህግ ያላቸው ሀገራት ህጋቸውን በዋነኛነት በ5 ርዕሶች / በሰዎች ህግ፣ በቤተሰብ ህግ፣ በንብረት ህግ፣ በውርስ ህግ እና በግዴታዎች ህግ/ ይከፋፈሉታል። የፍ/ብሔር ህጋችንም በተመሣሣይ መልኩ በ4 መፅሐፎች /በሰዎች ህግ፣ በቤተሰብ ህግ ፣ በግዴታዎች ፣ በንብረት የተከፋፈለ ነው። የፍ/ብሔር ህግ ጉዳዬችን በተመለከተ በህገ መንግስቱ ላይ እንደተመለከተው ስልጣኑ በዋነኛነት የክልል ነው ህገ መንግስቱ የሚለው በፌዴራል መንግስቱ በኩል ህግ የሚያሰፈልጋቸው " አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ" ለመፍጠር ያስፈልጋል ተብለው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዬች ላይ ነው የህዝብ ተወካዬች

ምክር ቤት ህግ የሚያወጣው፡፡ ስለሆነም በፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን /ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ እንዲሁም ንግድ ህግ በቀር/ በሌሎች የፍ/ብሔር ጉዳዬች ላይ የፌዴራል፣ የክልል፣ ህጐች ሊኖሩን ይችላሉ ማለት ነው፡ ለአብነትም የቤተሰብ ህግን ስንመለከት በአሁኑ ስዓት የክልል የቤተሰብ ህጐች/ ትግራይ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ/ የፌዴራል የቤተሰብ ህጉ እና የፍ/ብሔር ህጉ እንዲፈፀሙ እናገኛቸዋለን፡፡ ሀገራችን የምትከተለው ስርዐት የፌዴራሊዝም መሆኑን ከዚህ ቀደም በነበሩ ትምህርቶች ተመልክተናል፡፡ ይህንን የመንግስት ቅርፅ የሚከተል ስርዐት የህግ አውጣጡንም ሆነ አፈፃፀሙን በዛው ልክ “ ፌዴራላዊ” ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ ስርዐቱ ህግ ከማውጣት በተጨማሪ በባህል መዳኘትን በተመሣሣይ መልኩ ይፈቅዳል፡፡ ስለሆነም በፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ ባህሎች ፣ ልዩነቶች መደበኛ የህግ ብዙህነት እውቅና አግኝተነዋል ማለት ነው፡፡ መደበኛ እውቀት ከማግኘታቸው በተጨማሪም ህገ መንግስቱ እስካልተቃረነ ድረስ ሰዎች በራሳቸው ባህል፣ወግ ሊተዳደሩ ይችላሉ፡፡ አንድ ማህበረሰብ በራሱ የፍታሐ ብሐር ተቋም፣ በራሱ የፍ/ብሐር ባህላዊ ህግ፣ በራሱ ተከራካሪ እና ውሳኔ ሰጪ አካል ለዳኙ ሊካስ ይችላል፡፡ ወለለ ህገ መንግስቱ ያስቀመጠው ጥበቃ ሆኖ ጣራውን ይህ ባህላዊ ስርዐት ሊወስድ ይችላል፡፡ስለሆነም ህገ- መንግስቱ አንቀፅ 34/4/፣ 78/5/፣ 91፣ ከመግቢያው ፣ እና ከመሳሻነት አንቀጾች የምንረዳው በኢትዩጵያ ውስጥ ከዚህ ህግነት / legal pluralism/ ከማንነት፣ ከኮመን ሴንስ፣ ህጋዊነት፣/ ligatures / ፣ ከገበያ፣ ከሰላም፣ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው በመሆኑ መደበኛ መደበኛም /formally and Informally/ ባልሆነ መልኩም ተፈፃሚ እንዲሆን የተደረገ መሆኑን ነው!! የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችም አንደ ወሳኝ አካል ነው፡፡ ዝርዝሩ በሌሎች ትምህርቶች ይሸፈናል፡፡

የሰዎች ህግ በጥቅሉ በህግ ሊመሩ የሚገባቸውን /subjects of law/ ሰዎች እና የህግ ተቋማትን የሚመለከት ነው፡፡በአጠቃላይ የሰዎች ስም፣ሁኔታ /status/፣ ችሎታ፣ ችሎታ የሌላቸውን ጥበቃ ማድረግን የሚመለከቱ ህጐችን የያዘ ነው፡፡ የፍትህ አስተዳደሩ መነሻ ይህ ይሁን እንጅ በርካታ አንጻሮች የወቅቱን የገበያ ሁኔታ፣ፖሊሲ እንዲሁም የሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ጥበቃ በተሻለ ለማስፈፀም በልዩ ልዩ ህጐች መሻሻላቸውን ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡ የውጭ ሀገር ዜጐች ንብረት በማፍራት ረገድ የነበረው ፍትሐብሔራዊ ገደብ መላላቱ፣ የጋብቻ እድሜ ከፍ ማለቱ ሊጠቀስ ይችላሉ፡፡

በዚህ በሰዎች ህግ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ሊሰጣቸው ከማገቡ ጉዳዬች ውስጥ የሁኔታ/status/ ምዝገባ ነው። ልደት፣ ሞት፣ጋብቻ... አግባብ ባለው የፍትህ አካል ቀርበው መመዝገባቸው ለፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደሩ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ነው። ይህ የምዝገባ ስርዐት /vital statistics/ በአለም አቀፍ ሰነዶች /በተቀበልናቸው/ ግዴታ ሆኖ የተቀመጠም ነው። ምዝገባው ስርዐቱ መተግበር /መፈፀም/ ለበርካታ ፍትህ መዛነፍ ምክንያት ለሚሆኑ ጉዳዬች መፍትሔ የሚሰጥ ነው። የእድሜ ክርክር፣ የሞት ቀን ክርክር ወዘተ ጊዜ መሸኛና ፍትህ ማዛቢያ መሆናቸውን ያስቀራል።

5.1.2 <u>የቤተሰብ ህግ</u>

ሌላው የፍታሐ ብሔር የሚመለከተው /የጋብቻን የቤተሰብ ህግን/ ጉዳይ ነው። ጋብቻ ስለሚመለከትበት ሁኔታ፣የጋብቻ ህጋዊ ዉጤቶችን፣ ጋብቻ ስለሚመሰረትበት ሁኔታ፣ መለያየት፣ አባትነት እና የቤተሰብ መረዳዳት /support obligation/ ድንጋጌዎች እና የመሣሠሉትን የያዙ ነው። የፍታሐ ብሐር ህጉ በእነዚህ ነጥቦች ላይ በርካታ ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን አብዛኛዎች ተሸረዋል ወይም ተሻሽለዋል። ለህጐቹ መሻሻል/ ውርስ በአብዛኛው ሀገሮች የፍታብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ እንደምክንያት የሚወስዱት፡-

1. የጋብቻ ፍቺን ነፃ ማድረግ
2. ለመተሳሰብ ጉዳይ ላይ እና በንብረት አስተዳደሩ ጉዳይ ላይ ሴቶች ከወንዶች እኩል አቋም /position/ እንዲኖራቸው ማድረግ እና
3. ከጋብቻን ውጪ እና በጋብቻ ውስጥ ለተወለዱ ልጆችን ጥቅም ሁኔታ ማመሣሠል /assimilation/ ናቸው።

የሀገራችን ስርዓት በቤተሰብ ህግ ፍትህ አስተዳደር ላይ ክለሣ ሲያደርጉ መነሻቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ይመስላሉ። ማንኛውም ወንድ እና ሴት የጋብቻ እድሜ ላይ ሲደርስ ጋብቻ የመመስረት ብቻ ሣይሆን ጋብቻ ሲመሰረት/ አፈፃፀም/፣ በጋብቻው ዘመን እንዲሁም በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው ። ጋብቻም በተጋቢዎች “ሙሉ እና ነፃ” ፈቃድ መመስረት ያለበት ለመሆኑ በህጉ መንግስቱ የተደነገገው መነሻ የነበረውን የጋብቻ ለመቀየር መሰረታዊ መነሻ ነው። ህጉ በዚህ መልኩ የሚፈፀም ጋብቻ ጤናማ ዜጋን ለማፍራት ብቻ ሣይሆ የዳበረ ማህበረሰብ እና ኢኮኖሚ እንዲኖር የማስቻል መነሻ ሃሣብ

የያዘ ህግ ነው። ይህህግ ቀደም ሲል በወጣው የፍትሐ ብሔር ህግ ውስጥ ከውርስ ህግ ጋር በአንድነት በመጽሐፍ መልክ የወጣ ነበር ። በተመሣሣይ መልኩ አንድን ሰው ለራሱ ጥቅም የሚሆን ትክክለኛ ምክንያት ያለ እንደሆነ ዳኞች ሲያፀድቁት በጉድፈቻ ውል ልጅ ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ የሚደነግግ ህግም ያቀፈ ነበር። የፍትሐ ብሔር ህጉ በቤተሰብ ህጉ ክፍል ውስጥ መተጫጨትን የመሰሉ ሰፊ ድንጋጌዎች ይዘው ይገኙ ነበር። የጉዲፈቻና የውርስ ድንጋጌዎች አሁንም ድረስ የፍትሐብሔር ህጉን መሠረት በማድረግ የሚፈፀም ናቸው መተጫጨትን የተመለከተው የፍታሐ ብሔር ህጉ ድንጋጌ የተሻ ሻሸ ሲሆን ይህ ስርዐት ያስፈልገናል የሚሉ ክልሎች /ምሣሌ አማራ/ በቤተሰብ ህጋቸው ውስጥ በተሻሻለ መልኩ ተካቶ እንዲወጣ አድርገዋል። የፌዴራል የቤተሰብ ህግ በበኩሉ ይህንን ስርዐት አስቀርቶታል።

የውርስ ህግ አስተዳደርን አስመልክቶ የፍ/ብሔር ፍትህ ስርዐታችን ከ200 በላይ የሚሆኑ የህግ ቁጥሮችን ይዟል። በህጐቹ ላይ እንደተመለከተው ሰው መብቱንም ግዴታውን ለወራሾች ማስተላለፍ ይችላል። ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው መተላለፍ የማይችሉት ከሟች ጋር የሚቀሩ መብቶች እና ግዴታዎች ካልሆኑ በቀር መብቶች እና ግዴታዎች ለወራሽ ይተላለፋሉ። ለወራሽ የሚተላለፈውም አንድም በኑዛዜ አለዚያም ያለ ኑዛዜ ነው። የፍ/ብሔር ህጋችን የሟች ፍላጐት አጥብቆ እንዲፈፀም ይጠበቃል። ለዚህም የኑዛዜ አይነቶችም በጥንቃቄ መርጦ ያስቀመጠ ሲሆን በትኑዛዜ አይነቶችም ውስጥ ሊፈፀም የሚገባውን ስነ- ስርዐት ለይቶ ያስቀመጠ ነው። ሰው ኑዛዜ ያልተወ ቢሆን እንኳን ውርሱ የሚተላለፈው ሟች ኑዛዜ ቢተው ኖሮ ምክንያታዊ በሆነ አግባብ ያወረሳቸዋል ተብሎ ለሚገመቱ ሰዎች በቅደም ተከተል መሠረት ነው። ህጉ ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ የሟች ፍላጐት መግለጫ እና ማስፈፀሚያ እንዲሆን ያስቀመጠው ስነ- ስርዐት እንዲሁም ኑዛዜ በሌለ ጊዜም /ወይም ፈራሽ በሆነ ጊዜ/ ወራሽ የሚሆኑ የቅርብ ሰዎችን ስንመለከት የፍ/ህጉ በውርስ አፈፃፀም ላይ ምክንያታዊነትን /Reasonableness/ መነሻ ያደረገ ይመስላል።

ከፍ ሲል እንደተመለከተው በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ በውርስ የሚተላለፈው ልዩ ሁኔታዎችን እንደተጠበቀ ሆነው ማንኛውም መብት እና ግዴታ ነው። ስለሆነም ሰው በሚንቀሳቀስም ሆነ በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ ያለውን መብት ሊያስተላልፍ ይችላል ማለት ነው። በመሬት ላይ ያለውን መብትም ማስተላለፍ ይችላሉ። ይሁን እንጅ ማስተላለፍ የሚፈቀድለት ያለውን መብት ብቻ ነው። በመሬት ላይ ያለው

መብት ሲባዛ የይዞታ ስለሚሆን ባለቤትነትን ለማስተላለፍ ስርዐቱ አይፈቅድም ። ሰው የሚያስተላልፈው ግዴታውንም ጭምር ነው። በይህወት ዘመኑ የገባው እዳዎች ካሉ ውርሱ ከመከፈሉ በፊት ተካፋይ ናቸው። የውርስ ንብረቱም የተለየ ንብረት ሆኖ ለእዳ "መያዣ" ሆኖ ይቆያል። ይህንን ክፍያ ለመፈፀም የውርስ አጣሪ የመጀመሪያ ግዴታ አለበት። ግዴታው ማስታወቂያ በማውጣት ባለገንዘቦችን እስከ መጥራት ይደርሳል። ማስታወቂያውም ለ3 ወር ጊዜ እንዲቆይ ይጠበቃል። ሰዎች በህይወት ዘመናቸው የሚገቡዋቸው ልዩ ልዩ እዳዎች በሞት እንዳይቋረጡ ለባለንገንዘቦች አስተማማኝ ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ስርዐት ነው። የሰውን ከዚህ አለም ማለፍ ሰጋት ምክንያት በማድረግ የንግድ የንግድ ልውውጦ ሳንካ እንዳይገጥማቸው ለማስቻል ያለመ የህግ ስርዐት ነው። ይህ ስርዐትም የንግድ ልውውጦች አስተማማኝ የንብረት ዋስትና እንዲያገኙ የሚያስችል ሲሆን ከሚች እና ወራሾች እንዲሁም ከአጠቃላይ ህብረተሰብ ፍላጐት ውስጥ ነው ተብሎ አይታሰብም ።

የፍ/ብሔር ስርዐታችን የገንዘብ ጠያቂዎችን ፍላጐት በተለየ መልኩም ይጠበቃል። ወራሽ ውርስ አልፈፀመም ያለው ከእርሱ ገንዘብ የሚጠየቁ ሰዎችን ጥቅም ለ ለመጉዳት በማሰብ መሆኑ ከተረጋገጠ በገንዘቡ ልክ ውርሱን እንዲቀበል ሊገደድም ይችላል።

ሌላው እዚሁ ጋር ሊጠቀም አስፈላጊ የሚሆነው በውርስ አስተዳደር ህጋችን ውስጥ በቃል ኑዛዜ ከሚፈፀመ ውርሶች በቀር ማንኛውንም አይነት ንብረት በማንኛውም አይነት ኑዛዜ ማስተላለፍ በመርህ ደረጃ የተፈቀደ ነው ለማለት ይችላል። ይሁን እንጅ በመሬት ጉዳይ ላይ የኑዛዜዉ አወራረድ፣ የሚተላለፍላቸው ሰዎች ለዚሁ በወጡ በልዩ ህጐች የተቀመጡ መሆናቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው። በመሬት ጉዳይ ወራሽ የሚሆኑ ሰዎች ከሚች ጋር በቤተሰብነት፣በጣሪነት አብረው የሚኖሩ፤ ሌላ ገቢ የሌላቸው እንዲሆኑ የሚጠበቅ ሲሆን በመደበኛው ህግ ግን ወራሽ በመሆን ይህ ግድ አይደለም።

ለመሬት ጉዳይ "ቤተሰብ" የሚባለው ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ሊቀር ንብረቶቻቸው ወራሽ ለመሆን የኑዛዜ መኖር ወይም የዘር ሀረግን መቀጠር ግድ ነው። በሁለቱ ህጐች የተለየዩ የውርስ አፈፃፀም መኖራቸው መሬት በተቻለ መጠን የህዝብ እንዲሆነ ከማድረግ ጋር የተያየዘ ነው። በሌላ በኩል ሌሎችን ንብረቶች ከላይ በተመለከተው አግባብ በተቻለ መጠን ለዘመድ /ከውርስ ለመነቀል በቂ ምክንያትም ይጠቃል/ እንዲቀር እሳቤም ይሂል።

በውርስ ንብረት አስተዳደር ላይ የፍ/ህጋችን የሚከተለው ስርዐት ውርስ የማጣራቱ ተግባር በተቻለ መጠን "የውርስ አጣሪ" እንጂ የፍ/ቤት እንዲሆን አለማፈላለጉን ነው። ወራሽ ማን ሊሆን ይገባል? ለየትኛው ንብረት ይወርሳል? የትኛው እና እዳ ይከፈላል? የሚሉትንና መሰል ጥንያቄዎች መልስ ውርሱን እንደዘጋ የሚጠበቀው ይኸው አጣሪ ነው። የውርስ አጣሪ በመሰረቱ ወራሽ ነው። ይህ ወራሽ የማይታወቁ ሲሆን ወይም አውራሽ ውርሱን ለማጣራት የማይፈቀድ ሲሆን ብቻ ፍ/ቤቱ ሌላ አጣሪ ሊመደብ ይችላል። ይሁን እንጅ የፍ/ብሔር ህጉ በሚያዘው መልኩ በአግባቡ እየተፈፀመ ባለመሆኑ በርካታ ፍ/ቤቶች /በተለየ የወረዳ/ በውርስ ማጣራት ጥያቄ ውስጥ እየገቡ ሲጨነቁ ይታያል።

ሌላው በውርስ አፈፃፀም ስርዐታችን የተፈቀደው /ግን ሲፈፀም የማይታየው/ ጉዳይ የቀረለብ መጠየቅ ስርዐት ነው። ከውርስ ውስጥ የሚች ወላጆች፣ ተወላጅነት፣ ወንድሞች ፣ እህቶች፣ ባል ወይም ሚስት ቀለብ የማግኘት መብት አላቸው። እነዚህ ሰዎች "በችግር ላይ ከተገኙና" ሰርተው ኑሯቸውን ለማሸነፍ ካቃታቸው ከውርሱ ሃብት የሚከፈል ቀለብ መጠየቅ ይችላሉ። የውርስ አጣሪም ይህንን ጥያቄ እየመረመረ ከውርሱ ማግኘት በሚችሉት ገንዘብ መጠን ልክ /መጦሪያ/ ቀለብ ሊቆረጥባቸው ይችላሉ። ይሁን እንጅ ይህ በተግባር ሲፈፀም አይታይም።

በአጠቃላይ የውርስ ስርዐታችን ስንመለከት በሚች ፍላጐት እና በህዝብ ፍላጐት ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑን እንረዳለን። በዚህ ውስጥም የሚች ዘመዶችጠቤተሰቦች፣ ህዝቡ፣ የሚች ወይም የወራሽ ገንዘብ ጠያቂዎች፣ ከሚች ቀለብ ፈላጊዎች፣ እና ገበያው አስፈላጊው ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

5.1.3 የንብረት ህግ

ሌላው በፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የህግ ማዕቀፍ ያገኘው የንብረት ህግ ነው። የንብረት አይነቶች በርካታ ናቸው።የንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የሀገራችን የፍትህ ስርዓት የሚንቀሣቀሱ እና የማይንቀሣቀስ ንብረት በማለት ይከፍለዋል። ከታሪክ እንደምንረዳው በሀገራችን የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ከሚንቀሣቀሱት የበለጠ ጠቃሚ ተደርገው ይወሰዳሉ። ለዛም ነው የማንይንቀሣቀሱ ንብረቶችን አስመልክቶ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የበለጠ ገደብ የምንናገኘው ።

የሀገራችን ህጐች ንብረትን አስመልክቶ ሁለት መሠረታዊ መብቶችን ያስቀምጣሉ፤የንብረት ባለቤት መሆን እና በንብረት መጠቀም ውስጥ ይዞታ፣ አለባ፣ አገልግሎት ወዘተ ሊካተቱ ይችላሉ። መጠቀም ንብረት የሚጨበጥም የማይጨበጥም ሆኖ ሰዎች በገንዘብ የሚተመን ጥቅም የሚያገኙበት ነው ካልን ሁሉም አይነት ንብረት በባለቤትነት ሊያዝ ይችላል። ይሁን እንጅ ከንብረት አይነቶች ውስጥ በሀገችን መሬት በግል ባለቤትነት ሊያዝ አይችልም። ቀሪ ንብረቶችን ሰዎች በባለቤትነት ይዘው ሊቆዩ፣ በቀጥታ ሊጠቀምባቸው፣ በተዘዋዋሪ ሊጠቀሙባቸው ፣ ሊያበሏቸው፣ ሊያጠፏቸው ይችላሉ። በባለቤትነት መብት ላይ ይህ የነፃነት መርህ /Principle of freedom/ ያለ ቢሆንም እንደማንኛውም ሀገር የሀገራችንም የፍትህ አስተዳደር የንብረት ባለቤት በንብረቱ ሲጠቀም የሌሎች ሰዎች መብት ሊቃረኑ አይገባም፣ አለዚያም የህዝቡ ጥቅምን ሊጋፉ አይገባም በማለት ተደንግጓል። በተመሣሣይ መልኩ በህጐቻችን ውስጥ "የህዝብ ጥቅም" ከንብረት ባለቤትነት መብት በላይ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። ለምሣሌ ለህዝብ ጥቅማ ሲባል የባለቤትነት መብት መገደብ ብቻ ሣይሆን ንብረትም በመንግስት ሊወሰድ ይችላል።

ንብረት ለተወሰነ ጊዜ የተተወ፣የጠፋ ሊሆን ቢችልም ያለባለቤት አይኖረም ብሎ በጥቅሉ መናገርም ይቻላል። አንዳንድ ሀገሮች በዚህ መልኩ ያለባቤት የሚገኙ /vacant/ ንብረቶችን ወዲያኑ በመንግስት ባለቤትነት ስር የሚያስቀምጡ ሲሆን የኛ ሀገር የህግ ስርዓት ግን የጠፋ ፣ የተተወ ንብርት በመንግስት ባለቤትነት ስር ከመውደቁ በፊት ለፍለጋ የተወሰነ ስነ- ስርዐት እንዲያልፍ ያደርጋሉ። ለአብነት ማስታወቂያ ማውጣት፣ የተወሰነ ጊዜ /1 ወር/ ወዘተ።ይህም በሀገራችን የህግ ስርዐት ለንብረት ብቻ ሳይሆን ለባለቤትም ጥበቃ መኖሩን ያሳየናል።ተያይዞም የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱን ካገኘበት የመጠየቅ /Right of pursuit/ እና ከባለገንዘቦች ይልቅ ቅድሚያ የመጠየቅ/ Right of Preference/ መብቶች ያሉት ሲሆን በንብረት አስተዳደር ህጋችንም የታወቁ ናቸው።

የንብረት ህግ ውስጥ ጐልቶ የሚታወቀው ሰዎች ያላቸው መብቶች መዘርዝራቸው ነው። ለዛም ነው የንብረት ህግ ማለት የመብቶች ስብስባ /bundle of Rights/ የሚባለው ። ይህ በጥቅሉ ሲታይ ተነፃፃሪ ግዴታን/correlative duty/ ጭምር ይዟል ሊባል ይችላል። በንብረት መብት አለመሠራት / አለመጠቀምም/ ከንብረት ባለቤትነት አለመፈናቀልን አያስከትልም ለማለት ይቻላል። ይሁን እንጅ በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ውስጥ ይህ እውነታ ለሚንቀሣቀሱ ንብረት ትክክል ነው ቢባል

ለማይንቀሣቀስ ንብረት ግን ሁል ጊዜ ትክክል ነው ለማለት አይቻልም። ስርዐታችን በማይንቀሣቀስ ንብረት በተለይ በመሬት ላይ የመጠቀም መብትን ብቻ ሣይሆን የሚዘረዘረው የመጠቀም ግዴታን ጭምር ነው። ለአብነት በአማራ ክልል የመሬት አጠቃቀም አዋጅ 133/98 ላይ የመሬት ባለይዞታ መሬቱን የመንከባከብ አካባቢውን የመጠበቅ፣ ዛፎችን መትከልና ተንከባክቦ ማሣደግ፣ የአፈር ክለትን የመቀነስ፣ የውሃ መሰብሰብ ስልትን መከተል፣ እርከንና የአፈር ጥበቃ ሰራዎች ማከናወን ምንጭ እንዳይደርቅ ማድረግ ፣ መሬትን በእቅድ መጠቀም፣ ድንበር አለመግፋት፣ የመሬት ባለይዞታ ደብተር መያዝ፣ ከወንዝ አርቆ ማረስ፣ ወዘተ ግዴታዎች አሉበት ።የደን ውጤትን አልመቁረጥ፣በተቆረጠ ደን የመተካት /reforestation እና trifling/ ፣ረግረግ ቦታን የማድረቅ፣ የተወሰነ አትክልት አይነት/ tobacco/ ከመትከል መከልከል በሌላ በኩል የተወሰነ አትክልት የማልማት፣ ግዴታ በተጨማሪ ሊጣሉ ይችላሉ። አዋጅ መሬት ያለን ሰፊ ሀብት ቢሆንም ውስን መሆኑ፣ መጠቀሙ ከመልሶ ማልማት ያነሰ መሆን የሌለበት መሆኑን እና በመሬት ይዞታ / ድንበር / የተነሣ በርካታ ግጭቶች እንደሚኖሩ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የመሬት ባይዞታ በመብቱ እየሰራ ግዴታውን ካልተወጣ አቃል ማስጠንቀቂያ አንስቶ መሬቱን እስከመከልከል የሚደርስ ውሣኔ ሊሰጥበት ይችላል።

ሌላው በዚሁ የንብረት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ሊሰመርበት የሚገባው ሀሣቦችን ንብረትን የሚንቀሣቀስ እና የማይንቀሣቀስ በማለት ሲከፍል ቀደም ሲል እንደነበረው ከጋብቻ እና ውርስ ንብረት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ብቻ ሣይሆን ሌሎች በርካታ ጥቅሞችም አሉት። ።ለምሣሌ ንብረት በአንድ ወይም በሌላው መስመር መፈረጁ ንብረቱን ከመያዝ አንስቶ እጅ እስከ ማዛወር ድረስ ያሉ ሀሣቦችም በዛው መስመር ተለይተው እንዲፈፀሙ ያደርጋል። ይህም ማለት ንብረትን መያዝ /Possession/፣ በይዞታ ባለቤት መሆንን፣ ንብረት እጅ የሚዞርበት ስርዓት /formality/፣ የንብረት አስተዳዳሪ ስልጣን፣ ችሎታ፣የመያዣ አፈፃፀም፣የፍርድ ቤት ስልጣን፣ ስም ለማዞር የሚጣል ግብር ወዘተ የመሣሠሉት ነጥቦች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት ሀሣቦች በዛው ልክ የተለዩ እንዲሆኑ ያደርጋል። ለምሣሌ ጊዜው ይጠርም ይርዘምም ንብረትን በመያዝ ባለቤት መሆን የሚቻል ሲሆን መሬትን ግን ለማንኛውም ጊዜ ያህል በመያዝ ባለቤት መሆን አይቸልም። ህጋችን የሚንቀሣቀስ ንብረትን ለማስተላለፍ /ምሣሌ በሽያጭ/ ከውል

ግንኙት ተጨማሪ የምዝገባ ሰነ- ስርዓት እንዲፈፀም ግድ የሚሉ ሲሆን /የውል ህግ፣የመሬት አስተዳደ ህጐች /ይህ የምዝገባ ሰነ-ስርዓት ለሁሉም የሚንቀሣቀስ ንብረት አይሰራም። ስለሆነም በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ለማግኘት ወይም የመጠቀም መብት ለማግኘት / ለመሬት/ የፍታሐ ብሔር ስርዓታችን ምዝገባን እንደመርህ /rule/ ግድ ይላል ማለት ነው።

ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆንባቸው ንድፍ ሃሣቦች / theory/ የተለያዩ ናቸው። የመያዝ ንድፍ ሃሣብ /theory of possession/፣ የጉልበት ውጤት ንድፈ ሃሣብ /Theory of lab our/ የምጣኔ ሀብት ንድፈ ሃሣብ /theory of economics የስብዕና ንድፈ ሃሣብ /theory of personality ሊጠቀሱ ይችላሉ በንድፈ ሃሳቦቹ መሠረት እንደ ቅደም ተከተላቸው ሰው ንብረትን መጀመሪያ በመያዙ/ ማግኘቱ/፣ ንብረቱ የጉልበቱ /የልፋቱ/ ዋጋ በመሆኑ፣ የግል ንብረት ባለቤትነት ምርታማነትን የሚጨምር በመሆኑ የንብረት ባለቤት መሆን የሰው ልጅ ነፃነት ውጫዊ / ሰብዕና/ መ ገለጫ በመሆኑ ነው። የሀገራችን ህገ መንግስት በአንቀፅ 40 ስር ስለ ንብረት መብት ሲደነግግ ሰው በጉልበቱ እና በገንዘቡ ላፈራው የግል ንብረት ባለቤትነት ምርታማነት የሚጨምር በመሆኑ የንብረት ባለቤት ነው በማለት ደንግጐ እናገኘዋለን። በሌላ በኩል ከማይነቀሣቀሱ ንብረቶች ውስጥ በተለይ መሬት የህዝብ በመሆኑና ህገ መንግስቱ የህዝቡ የለኡላዊነት መገለጫ መሆኑን ስንመለከት ንብረት ከስብዕና / ዝሀብ/ ጋር ያለውን ቁርኝት ያስነሰል። ስለሆነም የሀገራችን ንብርት ፍትህ አስተዳደር ጉልበት ፣ ምጣኔ ሀብት እና ሰብዕና የሚሉትን / ንድፈ ሃሣቦችን መሰረት ያደገ ነው ለማለት ያስችለናል።

ይህም ተጠቃሎ የስርዐቱ መሠረት ለሀገራችን ለማይንቀሣቀስ ንብረት ይሰጥ የነበረው ከፍተኛ ቦታ ከመሆኑ በተጨማሪ ህገ- መንግስቱ ላይ የተቀመጠው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የማምጣት ፍላጐትም ነው ለማለት ይቻላል። ለንብረት መብቶች ለተለያየ ደረጃ የሚደረግላቸው የህግ ጥበቃ ይህ መሠረት እንዳለው በማሠብ ህጐችን በአግባቡ መፈፀም ያስፈልጋል። ለምሣሌ የንብረት የፍታሐ ብሔር ግንኙነቶች ቀልጣፋ እና የተሻለ ፍትህ መሰጠት ወደ ሚያስችለው የምዝገባ ስርዓት ማምጣት ያስፈልጋል። ለንብረት ላይ በሁለት ይወገድልኝ ስም የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ክሶች /አቤቱታዎች/ በእርግጥ በሰነ-ስርዓቱ መሠረት የክስ ምክንያት ያላቸው ለመሆኑ ቀደሞ መመርመር ይገባል።

የንብረት ፍትህ አስተዳደር አፈፃፀም ስርዐታችን ይህንን እና መሰል መሠረታዊ መነሻዎችን ግምት ውስጥ ባለመስገባት በርካታ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ለረዥም ጊዜያት ታግደው እንደሚቆዩ በስራ አጋጣሚ የምናስታውሰው ነው።

ንብረትን አስመልክቶ ያለን የፍታሐ ብሔር አስተዳዳር የፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ የተመለከተው ብቻ ሣይሆን በልዩ ልዩ አዋጆች ውስጥም የተመለከተ በመሆኑ ክርክርን /ክስን/ ሣይመረምሩ በመቀበል በስተመጨረሻ በአዋጅ መሠረት ለመወሰን መታቀብና መመርመር ያስፈልጋል።

የፍታሐ ብሔር ፍትህ ስርዓታችን ጥበቃ የሚያደርገው ግዙፍ ለሆኑት ንብረቶች ብቻ ሣይሆን ለማይጨበጡ /ለማይዳሰሱትም/ / incorporeal rights/ንብረቶች ጭምር ነው። የኮፒ ራይት ህጐች፣ የፓተንት ህጐች በልዩ ህጐች ጭምር ጥበቃ እንዲያገኙ የተደነገጉ ናቸው።

ሌላው የህጉ መለያ ባህሪ ነፃ የንብረት ዝውውር በተወሰኑ ምክንያቶች ለባለቤቱ፣ ለተቀባይ ወይም በ3ኛ ወገን ጥቅም ሲባል ከሚገድብ በቀር የተፈቀደ መሆኑና ሁኔታዎቹ በቋሚነት ንብረትን የማስተላለፍ መብት /በመሸጥ፣መለወጥ፣ ስጦታ፣ /perpetual inalienability ሊገደብ የማይችል መሆኑ ነው።

የንብረት ጥበቃ ከፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር የተሻለ ጥበቃ ከተደረገባቸው መንገዶች ውስጥ የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወሰድበት ጊዜ "የህዝብ ጥቅም መኖሩ መረጋገጥ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ ከመወሰዱ አስቀድሞ የሚከፈል" ተመጣጣኝ ካሣ " "መኖሩ ነው" ንብረት በተለይ የማይንቀሣቀስ ንብረትን ባለመጠቀም የባለቤትነት መብትን ማጣት የማይቻል ሲሆን ይህንን መብት ባለመጠቀም ለማጣት ሌሎች ሰዎች በንብረቱ የመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎች ግዴታዎችን ይጥላል። ይህ ተጨማሪ ግዴታ /ምሣሌ ግብር በስም መክፈል/ በስርዓቱ ውስጥ ሰው ንብረቱን በቀላሉ እንዲያጣ ለማስቻል የተቀመጠ ጥበቃ ነው።።

ሌላው ንብረትን አስመልክቶ እንደ ስርዓት ሊነሣ የሚገባው ነጥብ የንብረት ህግ በዋነኛነት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም ይህ የህግ ክፍል በተለያዩ ጊዜያት በወጡ አዋጆች መሠረታዊ በሆነ መልኩ ለውጥ የተደረገባቸው ጉዳዬችን የያዘ መሆኑ ነው።።። ለአብነት የከተማም ሆነ የገጠር መሬት በግል ባለቤትነት ሊያዝ እንደሚችል ከአ.ቁ 47/67 እና 31 /67 አንስቶ ተደንግጓል። ስለሆነም በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ የመሬት

መሬት በግለሰብ ባቤትነት ሊያዝ እንደሚችል የሚደነግጉት አንቀጾች ተሸረዋል/ ተሻሽለዋል/ ማለት ነው ። አንዳንድ ጊዜም ለምሳሌ የመሬቱ ባለቤት እየተቃወመ በመሬቱ ላይ ቤት ሌላ ሰው ሲሳራ ሲሳራ ይከፈለዋል /ወይም ቤቱን ለቆ ይሄዳል/ የሚሉት ድንጋጌዎች አስፈላጊው ለውጥ /mutants mutandis/ እየተደረገባቸው "ይዞታ" በሚልም ሊነበቡ ይችላሉ። ዝርዝሩ በንብረት ህግ ውስጥ ይታያል።

በተመሣሣይ መልኩ ንብረት አስመልክቶ እንደ ስርዐት ሊነሣ የሚገባው ነጥብ ንብረት የፍ/ቤት ስልጣንን ሊወስን የሚችል ሲሆን በአፈፃፀም ጊዜም የምንከተለው ስነ ስርዓት ላይም ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ነው። የማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ንብረቱ የሚገኝበት ነው። በግል አለም አቀፍ ህግም እንዲሁ። የማይንቀሣቀስ ንብረት በሀራጅ መሸጥ ቢያስፈለግ ለየት ያለ ጥበቅ ስርዓተ ህጋችን ይጠይቃል።

በተወሰነ ጉዳይም በተለይም የገንዘብ ዝውውር እንዳይስተጓጐል የግለሰብ እና የህዝብ ጥቅምን አመዛዝኖ ለመመለስ ይቻል ዘንድም ፍ/ቤት የማይመለከቷቸው የንብረት ጉዳዬች አሉ። ለአብነት ባንክ ቤቶች በውል የሰጡትን ገንዘብ በውላቸው መሠረት መመለስ እንዲችሉ በመያዣ የያዙትን የማይንቀሣቅስ ንብረት /ቤት/ በሀራጅ መሸጥና ገንዘባቸውን መሰብሰብ ይችላሉ። በተመሣሣይ መልኩ አ.ቁ.47/67 የተወረሱ/ የተወሰዱ/ ቤቶችን በተመለከተም /በአዋጅ መሠረት ወይም ከአዋጅ ውጪ/ ፍ/ቤት ክርክር ቢቀርብ ጉዳዩን ለመመልከት አሁንም ስርዓቱ አይፈቀድም። ይሁን እንጅ በርካታ ቤቶች በፍ/ቤት ውሣነ ሲመለሱ የምንታዘበው ነው።

በንብረት ጉዳይ ላይ ሌላው ራሱን የቻለ አስተዳደር ያለው በተለይ መጠቀስ ያለበት መሬት ነው። መሬትን የሰው ልጅ በህይወት እያለም ሆነ ከዚህ አለም ካለፈ በኋላ በዋነኛነት ለመጠቀሚያነት ይፈልገዋል። መሬት የህዝብ እንዲሆን ፡ "መሬት ላራሹ" ከሚለው የ1960 ዎች፡ ጥያቄ አንስቶ ሲጠየቅ የቆየ ነው ጥያቄው በ1967 ምላሽ ያገኘ ቢሆንም በመሬት ዙሪያ ያሉ ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ አፈፃፀሙ አልመለሰውም። በመሬት የመጠቀም መብት እና ግዴታ በአግባቡ ሣይፈፀም ቀርቷል። መሬትን መጠቀም መልስ ከማልማት በላይ እየሆኑ ጉዳት ሲያደርስ ቆይቷል የመሬት አለመግባባት ግጭቶች አግባብ ባለው አካል ሲፈቱ አልቆዩም። እነዚህ ችግሮች ለመቅረፍ ስለመሬት አጠቃቀም እንዲሁም ስለግብርና ገጠር ልማት ከወጣው ፖሊሲ አንስቶ አዋጆች ወጥተዋል።

አዋጆቹ አብዛኛው የመሬት ጉዳይ / የገጠር እና የከተማ/ ከፍርድ ቤቶች ውጪ በተለይ በአማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች እንዲፈቱ የሚፈልጉ መሆኑን ማስታወሱ ተገቢ ነው። የገጠርም ሆነ የከተማ ቦታን አስመልክቶ እንደ ስርዓተ ፍ/ቤት ያላቸው ስልጣን "ቀሪው" /Residual/ ሊባል እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። በመሬት ጉዳይ ላይ ግጭቶች በአግባቡ ባለመፈታታቸው ለበርካታ ወንጀሎች መንስኤ እንደሆኑ፣ ሴቶች ፣ ወጣቶች ፣ ደካሞች እና አካል ጉዳተኞች በመሬት የመጠቀም መብታቸው በጉልበተኞች የማይሸራረፍ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።ይህንን ማህበራዊ ቀውስ /ወንጀል፣ ማህበራዊ ችግር/ ለመፍታት ግጭቶች አማራጭ መንገዶችን ተጠቅሞ መፍታት ተገቢ ሲሆን ክርክሩ እልባት በሚያገኝበት ጊዜም ማህበራዊ እሴቶችንና ህጉን ባገናዘበ መልኩ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል።

5.1.3 የግዴታዎች ህግ

የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ትኩረት የሚሰጠው ሌላው የህግ አይነት ስለግዴታዎች የተደነገገው የህግ አይነት ነው።ይህ የህግ ክፍል በጣም ቴክኒካል፣ ረቂቅ እና ከሞላ ጎደል ብዙ ያልተለወጠ /የተረጋጋ/ የህግ አይነት ነው። የሚሸፈነውም ለመብት ጥያቄ /claims, rights/ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉንም አይነት ድርጊቶች ፣አለድረጊቶች እና ሁኔታዎች /situations /ነው። በስርዐታችን የውል ህግ ፣ ውል ሣይኖር ስለሚኖር ኃላፊነት የሚመለከተውን ህግ እና አላግባብ መበልፀግን የሚመለከተውን ህግ ይሸፍናል። ከዚህ በተጨማሪም ሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ልዩ ትኩረት የሚሻቸው ልዩ የውል አይነቶች በልዩ ህጐችም እንዲመሩ ተደንግጓል። ልዩ ህጐቹ የፍትሐብሔር ህጉም ከፍ/ብሔር ህጉ ሆነ ውጭ ይገኛሉ። ለአብነትም የማይንቀሣቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች፣ ሽያጭን የሚመለከቱ ውሎች ፣ ውክልናን የሚመለከቱ ውሎች፣ የሥራ ውልን ፣ የእቃ ግልጋሎትና አደራ ጠባቂነትን፣ የአስተዳደር ውሎች ፣ ግልግል ፣ ወዘተ እና የመሣሰሉት ውሎች የልዩ ህግ ሽፋን ያላቸው ናቸው።

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የህግ መንግስቱ አንዱ ዋነኛ አላማ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት ብቻ ሣይሆን በተፋጠነ ሁኔታ ማምጣት ነው። የኢኮኖሚ እድገት ዋስትና ያለው ገበያ ይፈልጋል። ገበያ በውል ህግ የሚሰራ ነው። ገበያ ነፃ መሆን ያለበት በመሆኑም ውሎችም በዛው ልክ ነፃ መሆን አለባቸው። የፍ/ብሔር ህጋችን በዚህ ረገድ

የሚፈቀደው የመዋዋል ነፃነት ትርጉም ባለው መልኩ ሊሰመርበት ይገባል። ውሎች ማንኛውም አይነት ቢሆኑ በፍትሐ ብሔር ህጉ ውስጥ በተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው ። ይሁን እንጅ ልዩ ውሎች እነዚህን ጠቅላላ ድንጋጌዎች ሊያሞሉ እንደሚችሉም ሁሉ ሊለወጡም ይችላሉ። ተፈፃሚም ይሆናሉ። ለምሣሌ የንግዱን ማህበረሰብ የንግድ ልውውጥ ፈጣንና ልምዱን መሠረት በማድረግ እንዲፈፀም የንግድ ህጉ የውል ድንጋጌዎች በልዩ ሁኔታ ይፈፀማሉ። የንግድ ግንኙነቶች በአብዛኛው ልማድን ወይም ተግባርን /practice/ መሠረት አድርገው የሚዳብሩና ህጐችም ይህንኑ ተግባር እውቅና እየሰጡ የሚመጡ በመሆናቸው ለጠቅላላው ውል በማሰብ ከተደነገገው ህግ በልዩ ሁኔታ መፈፀማቸው ተገቢ ነው። ይህንኑ ስርዓት ለማራመድ በወጣው ሌላው የውል ህግ መሠረት ያለውና ፍታብሔራዊ አስተዳደር የሚጠይቀው የአሰሪና ሠራተኛ ህግ የውል መሠረት ያለው ቢሆንም መንግስት በቁጥጥር መልክ የሚገባበት ነው ። የአሰሪና ሰራተኛ ህግ በመፅሐፍ መልክ ሣይሆን በአዋጅ ፣ደንብ መልክ የወጣ ነው። የስራ ግንኙነቶች ላይ የሚያተኩር ህግ ነው። የአሰሪና ሠራተኛ ህጋችን በመሰረቱ በስራ ቦታዎች ላይ የኢንድስትሪ ሰላም እንዲኖር የማስቻል አሳቤ አለው። ነፃ ገበያ ይህንን የሚፈልግ ከመሆኑ በላይ ጉልበት በነፃ ይዘዋወር ዘንድም ስለሚፈቅ አዋጆች በዚሁ መልኩ የወጡ ናቸው ። ሰራተኛ በፈለገው ጊዜ ስራ መልቀቅ የሚያስችል ሲሆን ያለ በቂ ምክንያትም እንዲይሰናበት የሚከለክል ነው። ሰራተኛው በለአንድስትሪ ሰላም መስፈን በድርጅቱ አንዳንድ ውሣኔዎች /shop -floor decision -making/ ላይም እንዲሳተፍ ያደርጋል። ሰራተኛ በማህበር እንዲደራጅ የሚፈቅድ ሲሆን የቅርብ አላማውም ሰራተኞች የራሣቸውን የሥራ እና የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻል ማስቻል ሲሆን የሩቅ አላማው ደግሞ ኢንዱስትሪው ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የሚጫወተው ሚና አሳታፊ በሆነ መልኩ ከፍ እንዲል ማድረግ ነው። በዚህ አላማ መሳካትም ሰራተኛው ከበሽታ በራቀ አካባቢ እና ከአደጋ በራቀ አካባቢ የመመሥረት መብት እንዲኖራቸው ያስገድዳል። የአሰሪና ሰራተኛ የውል ህግም የኢንዲስትሪውን ሰላም ለመፍጠር ታስበው የሚወጡ በመሆናቸው በልዩ ሁኔታ በጥንቃቄ መፈፀም ይገባቸዋል። <u>የግንባታ ስራዎችን</u> የሚመለከቱት ውሎች በልዩ ሁኔታ ከመደበኛ ሽያጭ ውል ተለይተው መፈፀሙ ለኢኮኖሚው እድገት መፋጠን ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ።ውል ሳይኖር ኃላፊነትን አስመልክቶ ህጋችን ሰፊ አንቀፃችን ይዟል ።የውል ግዴታን ካለማክበር ውጪ ያሉ የፍ/ብሔር ስህተቶችን የሚመለከት ጉዳይ ነው።በመሠረቱ የዚህ አይነቱ ኃላፊነት የሚመለከተው አንድ ሰው ከሌላው ሰው ጋር

ባለው ግንኙነት በተነሳ የተፈጠረው ስትህተት ያሰከተለውን ጉዳት ነው፡፡ ይሁን እንጅ በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን የዚህ አይነት ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖርም በሌላ ሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሰው ኃላፊ ሊሆን ይችላል፡፡ ጉዳት የደረሰው ድርጊት /አልድርጊት/ የወንጀል ህጉ ውስጥ ወንጀል የተባለ ሲሆን ይችላል፡፡ በፍ/ፍትህ አስተዳደራችን ሁሉም ወንጀሎች ህግን መተላለፍን ስለሚያመላክቱ የፍ/ብሔር ኃላፊነትን ያስከትላሉ፡፡ የወንጀል ህጐችን መተላለፍ ብቻ ሳይሆን የአስተዳደር ወይም ሌሎች ህጐችንም መተላለፍና ጉዳት ማድረስ ተመሳሳይ ኃላፊነት ያስከትላል፡፡ ስለሆነም በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ውስጥ የተሻለ ቀላል የሚሆነው ውል ሳይኖር ኃላፊነት የሚያስከትሉትን መዘረዝር ባይሆን የሚቻልከሆነ ኃላፊነት የሚያስከትሉትን መዘርዘር ነው፡፡ አመሳስለን ለመግለፅ በህግ በስርዐታችን አንድ ሰው አባት ሳይሆን የግድ ልጅ ነው፡፡ አንድ ጉዳት ያደረሰ ድርጊትም /አልድረጊትም/ ወንጀል ወይም ደንብ መተላለፍ ከሆነ የግድ ውል ሳይኖር ኃላፊነት ያስከትላል በተገላቢጦሽ ግን ሁል ጊዜ ሳይሆን ይችላል፡፡ በስዕል ለመግለፅ

ሰው ⇔ልጅ ⟵⟶ አባት

ድረጊት ⇔ ውል ሳይኖር ⟵ወንድም/ ደንብ መተላለፍ

/ሊኖር/ /ላይኖር/ ይችላል ማለት ነው፡፡

ከዚህ ስርዐት የምንረዳው በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ የውል ሳይኖር ኃላፊነት ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው የመከላከል ፍላጐት ያለው ብቻ ሳይሆን ወንጀል እንዳይፈፀም ተጨማሪ የመከላከያ መንገድም ነው ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ይህ የወንጀል መከላከል /Prevention/ ተግባር በዋነኛነት መፈፀም ያለበት በወንጀል ህግ/ ከህግ አንፃር/ ሲሆን የውል ሳይኖር ኃላፊነትም ተጨማሪ ግብአት ነው፡፡ የውል ሳይኖር ኃላፊነት የተለያዩ አላማዎች አሉት፡፡ በታሪክ እንደሚታወቁው መበቀል፣ መቀጣት፣ፍትህ ማስፈን፣ መካስ፣ ጉዳትን ማከፋፋል፣ በተለያዩ ጊዜያት እየገነኑ አላማዎቹ ሆነው ቆይተዋል፡፡

የፍትሐ ብሐር የፍትህ ስርዐታችንን ስንመለከት የዚህ ህግ ዋነኛና የመጀመሪያ አላማው ጉዳትን መካስ ነው፡፡ ጉዳት ከኪሣራው ጋር ተመዛዛኝ መሆን አለበት፡፡ ተጐጅው በሌላ መልኩ/ በኢንሹራንስ፣ በጡረታ / ሊካስ የሚችል ቢሆን እንኳን በዚህ መልኩ ካሣ ያገኛሉ በማለት ስርዐቱ መደንገጉ ህጉ ከካሳ በላይም ተጨማሪ አላማም አለው እንድንል ያደርገናል ፡፡ መከለከል አንዱ ነው፡፡ ፍትህ

ማስፈን ሌላው ነው፡፡ የውል ግንኙነቶች በአግባቡ ከተፈፀመ ሁለቱም ወገኖች ወደ ተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ሲሆን የውል ሳይኖር ኃላፊነት ህጐች በአግባቡ ሲፈፀሙ የደረሰን ጉዳት በተለይ ሁለቱ መካከል እንዲከፈል ያደርጋል፡፡ ይህ ከገበያ አንፃር ካየነው ሰዎች ከውል ውጪ የሚፈፀሟቸው ግንኙነቶችም በስረዐትና በጥንቃቄ እንዲመራ ያስችላል፡፡ ህጉ በሰው ላይ የደረሰው ጉዳት በኪሳራ ብቻ ይሸራል የሚል እስኬ የሌለው መሆኑንም የተለየያ ተጨማሪ “የካሳ” ማንነታችንም ተዘርዝረዋል፡፡ለምሳሌ በነፃ ገቢያ ስም የተፈጠረ አላግባብ ውድድር ካለ / unfair competition/ ይህ ውድድር በፍጥነት እንዲቆም ማዘዝ ይቻላል፡፡ ይህም ነፃ ገበያ ስርዐት ይዞ እንዲጐለብት አይነተኛ መንገድ ነው፡፡

ጉዳት ተመዛዛኝ መሆን ይገባልዋ ቢባልም በተለዋዋጭ አለም ውስጥ በተለይ የወደፊት ጉዳትን መገመት /ማረጋገጥ/ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ በዚህም ህጉ ርትዕን መሠረት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥ ይፈቅዳል፡፡

5.1.4 <u>የንግድ እና ሌሎች ህጐች</u>

በፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ የንግድ አይነተኛ አነስተኛ ቦታ አለው ፡፡ የንግድ ህጉ በአጠቃላይ የንግድ ድርጅቶችን / corporations/፣ የንግድ ማህበራትን ፣ኑጋዴን፣ የባንክ አሰራርን፣ የመድህን አሰራርን፣ የንግድ ሰነዶችን ፣ እና ሌሎች የንግድ ግንኙነቶቻችን የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንዴ አስቸጋሪ እንደሚሆነው ሣይሆን የንግድ ህጋችን “ ኑጋዴ” እና “የንግድ ግንኙነት” ለሚለው ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጅ የንግድ ህጉ የፍ/ብሔር ህጉን ያህል ጠቅላላ መርህን የያዘ አይደለም፡፡ በሌላ በኩልም በውስጡ ያለው መነበብ / internal coherence/ የፍ/ብሔር ህጉን ያህል አይደለም፡፡ ለዚህም የፍትሐ ብሔር ህጉ ለንግድ ህጉ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን / civilization of commercial code/ በር ይከፍታል፡፡ በተገላቢጦሽም አላስፈላጊ / “formalism” ከሚሰጠው ትኩረት ይልቅ 3ኛ ወገኖች በእምነት ለሚፈፅሙት ግብይት ጥበቃ መስጠቱ፣ የንግድ ግንኙነቶችም አንደ ሚፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ተከታታይ የሆኑ ግንኙነቶች/ an on-going relationship rather than isolated legal events / መሆናቸውን የተረዳ የህግ አይነት ነው፡፡ ይህ አስተሣሰብም /commercialization of civil code/ በተለይ ወደ ኋላ ለወጡ የፍ/ብሔር ህጐች ውስጥ እየገባ ነው ፡፡ይህ የሃሣብ

እና የህግ መወራረስ ቢኖም በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ውስጥ አንዳንድ ሀገሮች እንዳደጉት በፍ/ህጉ ጋር እንዲጠቃለል በማድረግ ሣይሆን/ ሲዊዘርላንድ/ የንግድ ህጉ ራሱን ችሎ እንደቆመ ለሌሎች የንግድ ህጐችም መሠረት ሆኖ እያገለገለ ነው።

ከንግድ ህጉ ጋር ተያይዘው ጐን ለጐን መታየት ያለባቸው ሌሎች የንግድ / ቢዝነስ/ ህጐች ናቸው። የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ስርዓት በእዝ ይመራ በነበረበት ጊዜ አስፈላጊ ያልነበሩ ህጐች አሁን በነፃው ኢኮኖሚ አስፈላጊ ሆነው የወጡ አሉ። የግል ባለሀብቶችን ለማበረታታት በርካታ የኢንቨስትመትንት ህጐች ወጥተዋል። የግል ባለሀብቶች ለኢኮኖሚው መፈጠን ከፍተኛ አስተዋፅዎ የሚያበረክቱ በመሆናቸው የሚበረታታባቸው ህጐችም ወጥተዋል። በፍትህ አካላት ዘንድ አፈፃፀማቸው ቀልጣፋና የግል ባሀብቱ እንደህጉ በሚበረታታበት መልኩ መሆን ይገባዋል። በነበረው ስርዓት ባለመፈቀዳቸው ያልተለመዱ በመሆናቸው በዚህ ረገድ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን የልምድ እጥረት ሊገጥመው እንዳሚችል አያጠራጥርም። ይሁን እንጅ ጠቅላላው የንግድ ህግ በነጋዴ ልማድ /practice/ ላይ ተመስርቶ ያደገ መሆኑን እንደተመለከትነው ሁሉ የሌሎች ቢዝነስ ህጐችም መሠረቱና አላማው በኢንቨስትመንት ልምድ ላይ ተመስርቶ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባዋል። ህጉ መሰረቱ በተለያዩ ጊዜ የተገኙ ልምዶች ናቸው።

በሌላ በኩል በስርዐታችን ውስጥ ነፃ ገበያ እና የመዋዋል ነፃነት አለ ሲባል ዘፈቀዳዊ ነው ለማለት አይደለም። ሁሉም ግንኙነት ነፃ የሚሆነው በህግ አጥር ስር ሆኖ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት እስካስቻለ ድረስ ነው። ከጨዋታው ህግ የወጣውን በነፃነት ስም የሚያበረታታ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ስርዓት የለንም። ጨዋታው ነፃ የሚሆነው በዚሁ የጨዋታው ህግ ውስጥ ብቻ ነው። በሌላ ሰው የስራ ድካም መበልፀግ አይፈቀድም። በሌላው ሰው ሀብት በቂ ባልሆነ ምክንያት ተገልግሎ መበልፀግ አይፈቀድም። ይህ በሆነ ጊዜ ያላግባብ የበለፀገው ሰው ለደከመው ወይም ለባለንብረቱ መካስ ግዴታው ነው። ውል ማፍረሱ፣ ውል ሣይኖር ጉዳት በመድረሱ ወይም ሌላው ያላግባብ በመበልፀግ ጉዳት ለደረሰበት ባለሀብት /ሰው/ በደረሰው ጉዳት መጠን / Proportional / ካሣ /compensation/ እንዲያገኝ የሚያስችል የፍትህ ስርዓት አለን ። ይህም በፍታሐብሔር የፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ ያለን የግዴታ ህጐች መሠረታዊ ባህሪ የሚያመሣስል ነው።

የግዴታ ህጐችን አሞላ ጐደል "የተረጋጉ" ናቸው ብንልም በተለያዩ ጊዜያት የወጡ የልዩ ልዩ ውል እና የውል ሣይኖር ኃላፊነት ህጐች ሰዎች በተለይ /በነፃ ገበያ የሚውዳደሩት/ ለሚፈፅሙት ውል አስተማማኝ የውል ጥበቃ የሚያገኙበት፤ ጉዳት ቢደረስባቸውም በአግባቡ የሚነሱበት እንዲሆን ያደርጋል። አዝማሚያው ሰዎች /ባለሀብቶች/ ምክንያታዊ ጥበቃ እና ግምት / reasonable reliance and expectation/ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። የግዴታ ህጐች አፈፃፀም ይህንኑ መስመር የተከተለና አግባብ ያልሆኑ ብልፅግናዎችን የሚያስቀር መሆን አለበት።

ውሎች በአግባቡ መፈፀም ያለባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ ከውል መለስ ያሉ ስምምነቶች ወይም ውል ሣይኖር የሚደርሱ ጉዳቶችንም የሚክስ ስርዓት አለን። እንደ ኮመን ሎው ሀገሮች የጉዳት አይነቶች ተዘርዝረው ባይቀመጡም ሰው በሌለው ላይ በቀጥታ ወይመ በተዘዋዋሪ ለሚያደርሰው ጉዳት በእርግጥ የደረሰውን ጉዳት የሚክስ ወይመ በርትፅ አይን የደረሰውን ጉዳት የሚክስ ስርዓት አለን። በሀገራችን የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና /public and private insurance scheme አይነት/ ስርዐትም ተደርጐ ሊወሰዱ ይችላሉ። ስርዐቱ የደረሰን የኢኮኖሚ ጉዳት የሚያከፋፍል /Risk distribution/ ሆኖ መፈፀም ይኖርበታል።የጉዳት አይነቶች እና የካሣው መጠን በጥቅሉ መቀመጣቸው ካሳው ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ /proportional/ ሆኖ ለመወሰን ያስችለናል። በአንድ ሀገር መሠረታዊ የፍታሐብሔር ፍትህ አስተዳደር አለ ለማለት ይህ የካሣ መጠን ተመጣጣኝ ሆና እንዲፈፀም የሚያስችል ህግ መኖሩ ነው። ካሳው ተመጣጣኝ ብቻም ሳይሆን በወቅቱ መከፈል ይገባዋል። ይህንን ስርዓት የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን የዘረጋ ሲሆን አፈፃፀሙ እንደ ስርዓቱ ለመሆኑ ወረድ ብለን እንመለከታለን።

5.2. የህግ ምንጮች እና ህጐች

የሲቪል ሎው ተከታይ የሚባሉ ሀገራት የህግ ምንጫቸውን በጥቅሉ በሁለት ይከፍሉታል፤የመጀመሪያው /primary/ እና ተከታይ /secondary/ በመጀመሪያው ረድፍ የታወጀ ህጐች ፣ልማዶች /customs/እና /አንዳንድ ጊዜ/ አጠቃላይ የህግ መርሆዎች /general principles of law/ ይገኙበታል። የመጀመሪያዎቹ ምንጮች ግልፅ ባልሆኑ ፣በሌሉ ወይም ባልታወቁ ጊዜ ኬዝ ሎው፣የህግ ፀሐፊዎች ፅሑፍ፣ ረቂቅ ህጐች/ እንደ

ሁለተኛ ምንጭ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ለምሳሌ በሀገራችም በመፅሐፍ መልክ ራሱን ችሎ ተጠቃሎ የወጣ የማስረጃ ህግ የሌለን ቢሆንም በ1963 የተረቀቀው የማስረጃ ህግ /አዋጅ/ ፍ/ቤቶቻችን በስፋት መርሁን እየጠቀሱ የሚጠቀመብት መሆኑ ግልፅ ነው። አንድ ማስረጃ አንድን ጭብጥ ለማስረዳት ያለውን አግባብነት /Relevancy/፣ የማስረዳት ብቃቱ፣ተቀባይነቱ /admissibility/፣ ልዩ ልዩ ግምቶች /Presumptions/፣ የአካባቢ ማስረጃ ምዘና /circumstantial evidence/ ወዘተ ከዚሁ እየተወሰዱ የሚፈፀም ናቸው። ይሁን እንጅ ምንጭነታቸው ከሀገር ሀገር ፣ ከጊዜ ጊዜ እና ከተያዘው ጉዳይ /subject matter / አንፃር ይለያያል። የህጐቹን ምንጭነት በጥቅሉ ከሀገራችን የፍትህ አስተዳደር አንፃር እንደከተለው እንመለከታለን።

5.2.1 የታወጀ ህግ

በመጀመሪያ ደረጃ የምናገኘው የሀገራችን አስገዳጅ ህግ በህግ መልክ ታውጀው በጋዜጣ የታተሙት ናቸው። በፌዴራል እና በክልል ጋዜጦች ታትመው የወጡት ህጐች ለሚመለከታቸው ቦታ፣ ጊዜ፣ እና ጉዳይ አስገዳጅ ናቸው። ታትመው የወጡ ህጐች በህግ አውጪው፣ በአስፈፃሚው፣ በአስተዳደር አካላት የወጡ ሊሆኑ ይችላሉ። በሀገራችን የፍትህ ስርህት በሪፈረንደም የሚፈፀሙ ጉዳዩች የተወሰኑ ከሚኖሩ በቀር በሪፈረንደም ህግ አይወጣም። የወጡ ህጐች ከህገ- መንግስቱ አንስቶ አዋጆችን፣ ትዕዛዞችን፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን ሊያካያትቱ ይችላል። የተቀበልናቸው ስምምነቶች እና አለም አቀፍ ውሎችም የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን አካላት ናቸው። በጥቅሉ በህግ አውጪው የሚወጡ ህጐች በቁጥር የበዙ ናቸው፡ ተብሎ ቢገመትም በውክልና የሚወጡትም የማይተናነሱ /የሚበልጡ/ መሆናቸውንም ልብ ማለት ይገባል። ስለሆነም የፍትህ አስተዳደሩ የተሞላ እንዲሆን ቴክኒካል እና ውስብስብ ነገሮችን አስመልክቶ በአስፈፃሚው አካላት በውክልና የሚወጡ ህጐችንም ጠንቅቆ ማወቁ ይገባል።ይህ ህግ መኖሩን አላውቅም ነበር የሚለው መቀነስ ያለበት ነው። በህገ-መንግስት ትምህርት ላይ እንደተመለከተው እነዚህ ታትመው የወጡ ህጐችን የፍትህ አካላት በስራ ላይ የማያውሏቸው ከህገ-መንግስቱ ጋር የሚጋጩ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው።

5.2.2 ባህል / custom /

በሲቪል ሎው ሀገሮች ውስጥ ባህል እንደ አንድ የመጀመሪያ አስገዳጅ የህግ ምንጭ ሆኖ ያገለግላላ። አፈፃፀሙ ከሀገር ሀገር ግን ይለያያል። አንዳንድ ሀገሮች የአካባቢ ልማድ በሚተገበሩበት ቦታ ብሔራዊ ህጉ እንደማይፈፀም በመደንገግ ባህልን ጠቃሚና የመጀመሪያ አስገዳጅ ህግ ያደርጉታል ምሳሌ /ስፔን/ አንዳንድ ሀገሮች /ፈረንሣይ/ ባህል ከብሔራዊ ህጉን እንዲያሟላ /supplement/ ሲፈቅዱ የተወሰኑት ደግሞ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ባህል ብሔራዊ ህግ በላይ እንዲፈፀም /abrogation/ ይፈቅዳሉ / ጀርመን/። በፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ በተለይ በንግድ ህግ በአሰሪና ሰራተኛ እንዲሁም በኪዝ ሎው አፈፃፀም ላይ ባህል ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታወቃል። ይሁን እንጅ የፍ/ብሔር ህጋችን በዚህ ረገድ ልማድ በፍ/ብሔር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን ገድቦል።።። ልማድ ተፈፃሚ የሚሆነው የፍትሐ ብሔር ህጉ ከሚመለከታቸው ጉዳዮች ውጭ ባሉ ቁም ነገሮች አለዚያም የፍ/ብሔር ህጉ በሚመለከታቸው ጉዳዬች ላይ በግልፅ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በተፈቀደባቸው ጉዳዬች ላይ ነው። ይህ ፀሐፊዎች እንደሚሉት" legal monism " ነው ።

ኘሮፌሰር ቺቸኖቪች እንዳስቀመጡት ባህል ተፈፃሚ የሚሆነው በህጉ ተፈፃሚ እንዲሆን ሲገለፅ፣ ህጉ በጉዳዩ ላየ ክፍተት ሲኖረው፣ በዳኞች ትርጉም፣ ባህላዊ ተቋማት ስልጣን/ ኃላፊነት/ ሲሰጣቸው /Para legal outlets/ ናቸው። በቤተሰብ ህጉ ውስጥ በርካታ ጉዳዬች በባህል ሊዳኙ ይችላሉ። ይሁን እንጅ እነዚህ ክፍተቶችም ቢሆኑ በፍትሐ ብሔር ህጉ መግቢያ ላይ " ህጉ ካወጣላቸው ሰዎች ልብ የሚደረስ ፍላጐታቸውን የሚሞላ ወይም የተፈጥሮ ፍትህን የሚጠብቅ" ካልሆነ፡ በቀር ዋጋ የለውም በማለት ባስቀመጠው ጋር አይሄድም። የመግቢያው ድንጋጌ ሌላ ሆኖ ባህልን የገደበው ድንጋጌ ወደ /legal monism ያደላ ነው። ይሁን እንጅ ይህ ነገሮችን በአንድ መንገድ የማስተናገድ መርህ ለኢፊዲሪ ህገ መንግስት ቀሪ ሆናል ህገ መንግስቱ " legal pluralism" ያበረታታል። ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 24/5 ላይ የቤተሰብ እና የግል ጉዳዬችን በተመለከተ በባህል ህጐች መሠረት መዳኘትን ይፈቅዳል። ለዚህም የሸርያ ፍ/ቤት ከወረዳ አንስቶ እስከ ጠ/ፍ/ቤት ድረስ ተቋቁሟል ። የፍ/ብሔር ህጉ ስራ ላይ ባለበት ጊዜም ቢሆን በርካታ ጉዳዬች በባህል እልባት እያገኙ ነው። ባህሉ ዘልቆ በገባው የህብረተሰቡ ልብ ውስጥ የህጉ ገደብ ሊገባ የቻለ አይመስልም። አንቀጹ ከውጪ ተገልበጠ እንጅ የፍ/ብሔር ህጉ በመግቢያው ላይም ያሰበው ህጉ የሰውን ልብ፣ ባህል እና ልምድ ካልጠበቀ ዋጋ እንደማይኖረው ነው።

ለዚህም ነው ህገ መግስቱ በተወሰኑ ጉዳዬች ላይ ባህላዊ ዳኝነትን በግልፅ ሲፈቅድ በቀሩት ደግሞ ህገ መንግስቱን እስካልተቃረነ ድረስ ያበረታታሉ የሚለው። ውሪዳ ብለን እንደምንመለከተው ፍ/ቤት ውጤታማ ስራ ለመከወን ያለውን ሀብት/ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ሰው/ ለደንበኞቹ በአግባቡ ማከፋፈል ያለበት ሲሆን ጉዳዶች ሁሉ ህገ መንግስቱን በማይቃረኑ መልኩ በባህል እልባት አንንች ማለት ፍ/ቤት ያለው ሀብት በቀረ ጉዳዬች በተሻለ መጠን እና ጥራት ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል። ይህ ማለትም በባህላቸው ጉዳያቸውን የፈቱ ሰዎች ክርክሩን ለሁሉም በሚጠቅም /win-win መልኩ መቋጨት ብቻ ሣይሆን የፍርድ ቤት ፍትህም ለቀሪው ዜጋ በአግባቡ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል። የሰነ- ስርዓት ህጉም ዳኞች እርቅ፣ ግልግሉ በፍ/ቤት /court annexed ADR/ / እና ከፍ/ቤት ውጪ ለመፈፀም ማነሣሣት እንደሚችሉ ይደነግገል።

ስለሆነም በፍ/ብሔር አሰተዳደሮችን ውስጥ ባህል እንደ አንድ የህግ ምንጭ ብቻ ሣይሆን እንደ ደአንድ የፍ/ብሔር መድረክም ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው።

5.2.3 ጠቅላላ መርሆዎች

ከታወጁ ህጐች /positive laws/ ወይም ከአጠቃላይ የህግ ስርዓቱ /legal order/ የሚመነጩ አጠቃላይ መርሆዎች የህግ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ለአስተዳደር ህጐች አፈፃፀም " ናቹራል ጀስቲስ" መርህ በተደጋጋሚ ሲፈፀም /ሲጠቀስ/ እንሰማለን። ለምሳሌ የአስ/ር ህግ የራሱ የሆነ የሰነ-ስርዐት ህግ የሌለው ቢሆንም ተከራካሪ ወገን በራሱ ጉዳይ ዳኛ መሆን የለበትም በሚል፣ ተከራካሪ ወገን ቀርቦ ሳይሰማ ውሣኔ መሰጠት የለበትም በሚል የሚሰጡት ውሳኔዎች መሠረቱ ይህ መርህ ነው። የማይንቀሣቀስ ንብርት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የግድ ምዝገባ ያስፈልገዋል አያስፈልገውም የሚባለው ክርክረ ቢነሣ የንብረት ምዝገባ ለንብረቱ ጥበቃ የተሻለ ዋስትና የሚያስገኝ በመሆኑና ይህም ለሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት አስፈላጊ በመሆኑ ምዝገባም አስፈላጊ ነው በማለት መከራከር ይቻላል። በርካታ ጉዳዬች ላይ ምክንያታዊነት /reasonableness/ መልካም ግብር ገብነት /good moral /በተመሳሳይ መልኩ ለውሳኔ መሠረት እየሆኑ ሲጠቀሱ እናያለን።

5.2.4 የህግ ትርጉም

ሌላው በህጋችን ከዚህ ጋር በተመሣሰለ መልኩ ለፍትህ ስርዓታችን በህግ ምንጭነት የሚያገለግለን የህግ ትርጉም ነው። የህግ መዕሐፎች በሚይዟቸው ጉዳዬች ላይ ኤግዘስቲሽ ናቸው ቢባልም ሁል ጊዜ ግን አይሆኑም። በሀገራችን ያሉ የህግ መዕሐፍትም በዚህ መልኩ የተጠቃለሉ ሣይሆኑ በልዩ ልዩ አዋጆች ታግዘው የሚሟሉ ናቸው። በኮመን ሎው ሀገሮች ኬዝ ሎው ወሣኝ እንደሆነው ሁሉ በሀገራችን የፍትህ አስተዳደርም የፍትህ አካላት ህጐችን እንዲተረጉም ይጠበቃል።ዳኞች /የፍትህ አካላት/ በትርጉም ሰራቸው መጀመሪያ የሚገጥማቸው ለቃላት ትርጉም መስጠት ነው። ይህ ህግን መተግበር /apply/ ነው ወይስ ህግን መፈለግ / find/ የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ በየዕለቱ በርካታ የህግ ጥያቄዎቻችን በዚህ መልኩ ምላሽ ያገኛሉ። አጠራጣሪ ህግ ፣ግልፅ ያልሆነ ህግ ፣ ወይም የሚጋጭ / የሚመስል / ህግ ባጋጠመ ጊዜም በተመሣሣይ መልኩ ህግ ይተረጉማል።

በሌላ በኩልም በቀረበ ጉዳይ ላይ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ህግ በሌለ ጊዜ አጠቃላይ የህጉን መንፈስና የሀገራችን የፍትህ ስርዓት መሠረታዊ ባህሪ በመረዳት ህጉን መተርጐም ያስፈልጋል። ህጉ በፍፁም ክፍት በሆነ ጊዜ ወይም ያለው ህግ አሁን ካለንበት አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም በሆነ ጊዜ ዳኞች ህጉን በራሣቸው እንዲያዳብሩም ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የሀገራችን የፍትህ ስርዓት በተለይ የዳኝነት አካሉ የሚጫወተው ሚና ጐልቶ አይታይም። ምናልባትም ህጉ የተሟላ ባይሆንም /complete/ ዝርዝር ህጐችና መርሆዎችን /self sufficiency/ የያዘ በመሆኑ እነዚህኑ ተፈፃሚ በማድረግ ክፍተቱም እየተሟላ ሊሆን ይችላል። በሌላ አነጋገር ህግ በማውጣት ሣይሆን ህጉን ከራሱ በማሣደግ እየተፈፀመ ስላለም ይመስላል። ይሁን እንጅ የፍታሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደራችን የህግ ትርጉም በመፈለግ ህግን መፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አጠቃላይ የህጉን ማዕቀፍ መርህ /basic principles of the legal order / በመመርመር /ዳኞች/ የፈጠራ ተግባር /creative function / መፈፀም እንደሚገባቸው ይጠበቃል።

ለምሣሌ አጠቃላይ የህግ ስርዓታችን ጉዳት ኪሳራ እንደሚያስከፍል ያሳየናል። አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላውን ተከራካሪ ወገን ቢያጉላላው፣ ኪሳራ ሊከፍል እንደሚችል የሰነ ስርዓት ህጉ በኪሣራና ወጪ ድንጋጌዎች አስቀምጧል

፡፡ የቀረበ ክርክር ጊዜ በመውሰድ ሌላውን ለመበደል ለማጉላላት የቀረበ ከሆነ ዳኞች "ኪሣራ ይክሰዋል" ብለው ብቻ ማቆም የሚገባቸው አይመስልም፡፡ በተቻለ መጠን ማጉላላት ፣ ጊዜ መፍጀትንና በደልን ማስቀረት አለባቸው በመሬት ላይ ያለ ክርክር ሁለት እና ሶስት የእርሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢወሰን የማይካስ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ የ3000 ብር በሬ ክርክር ቢቀርብበትና ታግዶ ቆይቶ የእርሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ውሶኔ ቢሰጥበት ኪሳራው " የሚክስ " ላይሆን የችላል"" አንድ ባሀብት ሀብቱን መሬት ላይ ካፈሰሰ በኋላ በክርክር የተነሣ ከስራው ሊታገድ ይችላል፡፡ ለጉዳዩ ላይ ኪሳራ ተወሰኖ በስተመጨረሻ ለባለሀብቱ ቢወሰን እንኳን ባሀብቱ የተሻለ ቀልጣፋ የፍትህ ስርዓተ አለበት ቦታ ማልማት ጀምሮ ይህናል፡፡ ተከራካሪ ወገን ፍትህ ፍትህ ሲተገበር ብቻ ሳይሆን ማየት ያለበት በእርግጥ "ፍትህም አለ ፍትህም ሲተገበር አያለሁ" ብሎ ማመን መቻል አለበት፡፡ በስነ ስርዓት ህጋችን ውስጥ ይህንንን በቀጥታ ባናገኘው እንኳን ሙግት ጊዜ መውሰጃ ፣ ማጉላያ፣ መበደያ፣ መሆን የለበትም፤ ከሆነም ያስቀጣል የሚለው መርህ ለዚህ መደምደሚያ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡ ሌሎች መርሆዎችም በተመሣሣይ ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡

5.2.5 <u>የፍርድ ቤት ውሣኔ /ሔዝ ሎው/</u>

በሲቪል ሎው የህግ ስርዓት ውስጥ የዳኞች ተግባር ተደርጐ በተለይ የሚወሰደው አንድን ጉዳይ መወሰን ነው፡፡ የተመረጡ የህዝብ ተወካዬች ብቻ ህግ ሊያወጡ ይገባል የሚለው እምነት አሁን ድረስ መሠረታዊ ሆኖ የቀጠለ በመሆኑ ይህ የዳኞች ሚና እምብዛም አልተለወጠም፡፡ የሀገራችን የፍትህ ስርዓት ይህንን መስመር የሚከተል ነው፡፡ ይሁን እንጅ ዳኞች በተከታታይ ህግ አያወጡም ለማለትም አይቻልም፡፡ ይህ ህግ ይሆናል? የሚለውና እስከምን ድረስ የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በአጠቃላይ የዳኞቻችን ውሣኔዎች በአጠቃላይ ሲታዩ በበታች ፍ/ቤቶች ላይ፣በተመሣሣይ ፍ/ቤቶች ላይ ወይም በcoordinate **ፍ/ቤቶች ላይ አስገዳጅ አይደሉም፡፡ በሀገራችን ይህ ሁኔታ በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነው፡፡ በመጀመሪያ አንድ ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ በሁለት የተለያዩ መንገድ ለመወሰን መንገዱ ቀላላ አይሆንለትም ፡፡ በስፋት ባይሆንም አልፎ አልፎ በተለምዶ** super- panel of the

court የተባለውን ፓናል መያዝ /ማካሔድ/ አንድን ጉዳይ በተለየ መልኩ ለመወሰን ፍ/ቤቶችን ሲጠቀሙ እንመለከታለን፡፡ የህግ መሠረቱ ግን ግልፅ አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ ፍ/ቤቶችን በስልጣናቸው ውስጥ ህግን መልክ ባለው ተመሳሳይ / Uniform/ መንገድ የመተግበር ግብን መስረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል የበላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ በበታች ፍ/ቤቶች ላይ ያለው እውነት /በእርግጥ / ያለው ተፅዕኖም de facto ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ብንወስን የበላይ ፍ/ቤቶች /ጠቅላይ/ ሊሽረው ይችላል በሚል እምነት የበላይ ፍ/ቤት አስቀድሞ በሰጠው ውሣኔ አቋም መወሰን ይታያል፡፡ ውሣኔ ይሻራል ከሚል ስጋት እና የአዕምሮ ጉልበትን ከመቆጠብ ፍላጐትም ሲመነጭ ይታያል፡፡ምሣሌ፡- ኑዛዜ የፍ/ህ/ቁ 881 የሚጠየቀውን የስነ ስርዐት ፎርማሊቲ በአግባቡ ያላሟላ ከሆነ ፈራሽ ነው እየተባለ በሚቀርብ ክርክር ላይ የክልል ጠ/ፍ/ቤቱ " ለሚሽረው " በማለት ፀሐፊዎች ያስታውሳሉ፡፡ ሲወስን ፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረ ሽያጭን አስመልክቶ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ አለመመዝገቡ ዉጤቱ 3ኛ ወገንን የሚመለከት ነው በሚል የበላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመከተል ውሳኔ ሲሰጥም ቆይተዋል፡፡ ለአብነት የተነሱት ጉዳዬች ላይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በሚየፀና / መልኩ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ የሚያሳየን ኬዚ ሎው አንድ ፍርድ ቤት ከሚይዘው አቋም በላይ በእርግጥ /de facto/ ገዥ እንደነበረ / እንደሆነ/ ነው ፡፡

በሌላ በኩል የተሰጡ ውሣኔዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ህግ /codification/ ሆነው የሚወጡበት አጋጣሚም አለ፡፡ ለምሳሌ የፈረንሣይ የውል ሳይኖር ኃላፊነት ህግ በዚህ መልኩ የዳበረ ነው፡፡ የአስተዳዳር ህግ በአብዛኛው የዳበረው ከተሰጡ ውሣኔዎች ነው፡፡ በህገራችን ጋብቻን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ማስረጃ፣ አባትነትን ስለማስረዳት ስለሚቀበው ማስረጃ፣ የይግባኝ ጊዜ አቆጣጠርን አስመልክቶ የተሰጡ ውሳኔዎች በዚሁ ነጥቦች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች አስተዋያ አላቸው፡፡

በአጠቃላይ የፍ/ቤቶች ውሣኔ በእርግጥ /de facto / የህግ ምንጭ /ህግ/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጡ ውሳኔዎች ብዛት፣ ውሣኔውን የሚሰጠው ፍርድ ቤት ክብር/ importance/፣ በፍርድ ላይ የሰፈረው አስተያየት አፃፃፍ ለዚህ ወሣኝ ናቸው ፡፡ በበላይ ፍ/ቤት /በአቻ/ የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሣነ በ / de facto/ ለበታች ፍ/ቤት ህግ ሲሆን እንደተመለከትነው ሁሉ ከዚህ በተለየ

መልኩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር የተሰጠ ፍርድም በየትኛውም ፍ/ቤት አስገዳጅና ህግ እንዲሆነም አ.ቁ 454/97 ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የህጉ መንግስት አጣሪ ጉባዓ እንዲሁም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በተሰጣቸው የህጉ መንግስት የመተርጐም ስልጣን ላይ የሚሰጡት ውሳኔ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ያለውን ውስጥ /ተፅዓኖ/ ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም በፍ/ብሔር ፍትህ አሰተዳደራችን ውስጥ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን / case law በህግ /de jute / እና በእርግጥ /ac factor/ በለበታች ፍ/ቤቶች ህግ ናቸው ማለት ይችላለ፡፡ ኬዝ ሎው በ /de facto / “ ህግ “ መሆኑ የአፈፃፀም ችግር ስለመሆኑ ለውይይት ክፍት ነው፡፡/case law / በዚህ መልኩ ህግ መሆኑ በተያዘ ጉዳይ ላይ ዜጐቻችንም ምክንያታዊ የሆነ እርግጠኝነት እና ግምት/ reasonable certainty and predictability/፣ ፍትሐዊነት /fairness/ እንዲኖር የሚያደርግ ከመሆኑ በተጨማሪ ፍትህ እንዲታይ ብቻ ሣይሆን ፍትህ ሲተገብርም እንዲታይ ያስችላል፡፡ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳዳዎችን በተረጋጋ ሁኔታ ቀጣይነት /continuity/ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

5.2.5 <u>የህግ ሙህራን ፅሑፍ</u>

ሌላው የህጋችን መሰረት የህግ ምሁራን ፅሑፍ ደ / doctoring ናቸው ፡፡ ኬዝ ሎው የህግ ምንጭ ሊሆን እንደሚችለው ሁሉ የህግ ባለመያዎች /legal scholears ፅሑፎችም በተመሳሳይ መልኩ የህግ ምንጮቻችን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ኬዝ ሎው ለተግማችነት የሚጠቅመን ሲሆን የህግ ፅሑፎች ግን የህግ ጥያቄ የረጋ መልስ እንዲኖረው ወይም በተነሳው ጥያቄ ላይ ህጉ ምላሽ ከሌለው አጋዥ መልስ በመሆን ያግዘናል፡፡ የህግ ፅሁፎች ተፅዕኖነቸው ቀጥታኛ አይደለም ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ በህግ መፅሐፎቻችን ላይ የተሰጡ አስተያየቶች፣ ለጠቅላላ ፅሑፎች፣ ለመመረቂያ ፅሑፎች፣ ለሙያ አስተያየቶች ወዘተ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ቦታ ይሰጣል፡፡በዚህ መሠረት በውል ህጋችን ላይ በደቪድ እና ቺቺኖቪች የተሰጡ አስተያየቶች፣ በይግባኝ ጊዜ አቆጣጠር ላይ የተፅፉት አስተያየቶች ፣ በስነ ስርዐት ህጉ ላይ በሴድለር የተፃፉ ፅሁፎች፣ በጋብቻ ማስረጃ ላይ የቀረቡት ፅሁፎች፣ በይግባኝ ጊዜ አቆጣጠር፣ በዳኞች ስነምግባር ደንብ፣ በፊዲሪሽነ ምክር ቤት እና አጣሪ ጉባዔ አሰራር ላይ የተፃፉ ጽሑፎች፣

በፍ/ቤቶቻችን ለበርካታ ጊዜ የሚጠቀሱና ለክርክር ገዥ መቋጫ /authority/ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡

የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ምንጮች በመያዝ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሻ ሲሆን ሁለት እርስ በእርስ በውጥረት /tension ላይ ያሉ ነገር ግን የማይጋጩ ነጥቦችን ያያል ተገማችነት predictability እና ተወዋዋጭነት /flexibility/ እንዲሁም መረጋጋት /stability/ እና እድገት / growth/ በተገማችነት እና መረጋጋትን በስርዐቱ ውስጥ በተፃፉት ህጐቻችንና ለኬዝ ሎው ለመሸፈን የሚሞከሩ ሲሆን እድገትና ተለዋዋጭነትን ደግሞ በውስጥ ደንቦች በጠቅላላ አገላለፃችን እና በትርጉም እንዲሸፍን ይጥራሉ፡፡

በውል ህግ፣ በውል ሣይኖር ህግ ፣ በንብረት ህግ አስተዳደራችን "reasonableness' የሚለውን ህግ በምሣሌ ብንመለከት እንኳን እነዚህን ሁለት ውጥረት ውስጥ ያሉ ነጥቦችን መያዙን እንረዳልን፡ ህጉ ተገማች በሆን መልኩ በተረጋገ ሁኔታ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚያስችለ ብቻ ሣይሆን ተለዋዋጭ ሁኔታዎችንም ከወቅቱ ጋር ተጣጥሞ ለመተግበር የሚያስችል ነው፡፡ ይህንን ከላይ የተጠቀሱትን ውሳኔዎች ይሁን እንጅ ፍ/ቤቶች በተለይ ማህበራዊ ግንኙነቶች አንዳዶች ሲቀርቡ / በመርህ ላይመለሱ ይችላሉ/ ህጐች ያልተረጋጉ እና ምክንያታዊ ባልሆኑበት ጊዜ ይህ ተገማችነት ሊጠፉ ይችላል፡፡

5.2.7 ሰነ ስርዓት / procedure /

የክርክር ስርዐቶች የሚመሩበት መስመር በአጠቃላይ አድቨርሰሪያል እና እንኩስቶሪያል በመባል ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ አድቨርሰሪያል የሚባለው የክርክር ስርዐት ተከራካሪ ወገኖች በንቃት እና ያለገደብ ክርክራቸውን ለውሳኔ ሰጪ አካል /ፍ/ቤት/ እዲያቀርቡ የሚፈቀደውን ነው፡፡ ይህ ስርዐት በአብዛኛው በአንግሎ አሜሪካ /ኮመን ሎው ስርዐት/ ተግባራዊ የሚሆን ነው፡፡ በዚህ ስርዐት ውስጥ ዳኞች በክርክሩ አመራር ላይ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርጉ አይታይም ፡፡ ዋናው ተግባራቸው ክርክሩን ተቀብለው ከመረመሩ በኋላ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ በሌላ በኩል የህግ ስርዐታቸው የእንኩሺሲቶሪያል ስርዐት ይከተላሉ የሚባሉ አገሮች ከሞላ ጐደል ተቃራኒ ስርዐት ይከተላሉ፡፡ ይህን ስርዐት የሲቪል ሎው ሀገራት የሚባሉት የሚከተሉት ሲሆን በዚህ

ስርዐት መሠረት ዳኞች በንቃት ክርክርን ይመራሉ፣ ለምስክር ምን ጥያቄ መጠየቅ እንዳለበት ይወስናሉ፣ በምርመራው ስራ ውስጥም እስከ ምን ድረስ ሊኬድ እንደሚችል ይወስናሉ።።

የሀገራችን የፍ/ስ/ስርዐት ህጉ በንፅፅር በቅርብ ጊዜ የወጣ ነው።። ከኮመን ሎው ሀገሮችን በተለይ ከህንድ መወሰዱ ቢገለፅም የዘመኑን የፍትህ አስተዳደር ችግር ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።። በየቦታው እንደጀምንመለከተው የሁለቱ ስርዐቶችን መኖር የሚያንፀባርቁ አንቀጾች እዚህም እዛም ይገኙበታል።።

በመደበኛው ህግ ውስጥ የፍ/ብሔር ህግ ቁልፍ ቦታ እንዳለው ሁሉ በስነ-ስርዓት ጉዳይም ላይ የፍትሐ ብሔር ስን ስርዓት ህጉ ቁልፍ /central/ ቦታ አለው።። ሀገራችን በ1958 ያወጣችው የፍትሐብሐር ስነ ስርዐት ህግ አሉት።።የፍ/ስነ ስርዐት ህጉ በአንድ ጉዳይ ላይ ተከራካሪ ወገን ማን ሊሆን ይችላል፣ ክርክር የት እና እንዴት ሊቀርብ ይችላል ከሚለው ተነስተው የተሰጠ ፍርድ ፍፃሜ የሚያገኝበትን አግባብ ሁሉ የያዘ ነው።። ለክርክር የሚያመቹ ልዩ ልዩ ፎርሞችን የህግ ክፍል አድርጐ ይዟል ።። ህጉ ከጨነሻው በዋነኛነት ከኮመን ሎው ሀገሮች በተለይ በህንድ ተቀድቶ በትዕዛዝ መልክም የወጣ ነው።።

በመሠረቱ የፍ/ብሔር ክርክሮች ለህዝብ ክፍት ሆኖ የሚካሔዱ /publicity/ እና የክርክር አቀራረብ / allegation/ እንዲሁም የማስረጃ ቁጥጥር /proof/ በተከራካሪ ወገኖች የሚመራበት ነው።።

ይሁን እንጅ በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ዳኞች / እንዲሁም ዐ/ሕግ / የፍ/ብሔር ክርክር በመቆጣጠር /supervision/ እና በመምራት የነቃ ተሣትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል።። በሀገራችን የፍ/ብሔር ክርክር ሂደት በእርግጥ /pretrial discovery and trial/ በትክክለኛ ትርጉማቸው ሲፈፀሙ አናገኛቸውም።። በሌላ በኩል ክርክሮቹ የተለያዩ ተከታታይ ግንኙነቶች /meetings/፣ ክስ መሰማት፣ የፅሁፍ ልውውጦች ማካሔድ ማስረጃ መስማት፣ ቀጠሮ እና ውሣኔ የሚሰጥባቸው ሆነው እናገኛቸዋለን።። በዚህ መሀል ዳኞች ጭብጥ በመያዝ / እንዳስፈላጊነቱ በመቀየር/ ምስክሮችን በመጠየቅ የነቃ ተሣትፎ ሲያደርጉ ይታያል።። ዳኞች የባለሙያ ምስክር መጥራት የሚችሉና አስተያየት አዘል ማስረጃዎችን / opinion evidence/ መቀበል

የሚችለው በመሆኑ ብቃት የሌለው ተከራካሪ ወገንን / ለፍትህ/ የማገዝ እድል ያገኛሉ፡፡ ለቀረበ ማስረጃ ዳኞች የሚሰጡት ክብደት ነፃ በሆነ ግምገማቸው /free evolution of evidence/ ላይ ተመስርተው ነው፡፡

በሀገራችን ክርክር እና ማስረጃ ከተጠናቀቀ በኋላ ውሳኔ ወዲያውኑ እንዲሰጥ የሚጠበቅ ሲሆን ክርክሩን እና ማስረጃውን የሰጠው ዳኛ ውሳኔውን እንዲሰጥ የግድ አይልም፡፡ /በጀርመን ክርክሩን የሰጠው ዳኛ ውሣኔ እንዲሰጥ ይገደዳል/፡፡ ውሣኔውም ልዩነት ካለበት ይፃፍበታል እንጅ በተሟላ ዳኛ/ዳኞች/ እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ ያወጡትን ወጪ /cost of litigation / አስመልክቶ ተስፋ የሌላቸውን አላግባብ ሌላውን ወገን ያጉላሉ ክርክሮችን ላለማበረታታት / እንዲሁም ለመካስ/ ዳኞች ካሣ እንዲቆረጡ ይጠበቃል፡፡ ዳኞች በሌሎች ሀገሮች እንደሚደረገው ባለሙያዎች ሆነው በፍሬ ነገሩም ሆነ በህጉ ላይ የመጨረሻ ውሣነ ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ በሀገራችን ዳኞች በፍሬ ነገር ክርክር እንኳን የ jury አይነት እገዛ የሚያገኙበት እድል የለም ፡፡

ሌላው በፍትህ አስተዳደራችን ሊነሣ የሚገባው ክርክሮች በቁጠባና በጥራት /efficiently and economically/ መጠናቀቅ ያለባቸው ሲሆን ለዚህም የስነ-ስርዓት ህጋችን እድል ይሰጣል በእርግጥ እንደጀርመን ባሉ ሀገሮች እንደሚደረገው በንፅፅር ቀላል ለሚባሉ ጉዳዬች በተጠቃለለ መልኩ አንድ ጊዜ ክርክሩን ሰምቶ/ single comprehensive hearing model / መወሰን አያስችሉም ፡፡ ይሁን እንጅ በሀገራችን የፍ/ብሔር የፍትህ ስርዓት ክርክሮች መደበኛ በሆነ፣ በተፋጠነ እና በክለሣ መልክ ሊሰሙ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመርህ ደረጃ ክርክር የሚቀርበው በመደበኛው ስነ-ስርዓት ሆኖ የቃል ክርክርም በሁለት የተለያየ ጊዜ ይካሔዳል፡፡ በተግባር የበርካታ ወረቀት ልውውጥ ይደረጋል እንጅ ህጉ በተለየ እንዲፈፀም የሚያዘው ይህንኑ የቃል ክርክር ነው፡፡ ይህ በንፅፅር ረዘም ያለ ጊዜን ሊወስድ የሚችል ሲሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ክርክር በልዩ ሰነ-ስርዓት እንዲመራ ስርዐታችን በር ይከፍታል ፡፡ ለአብነትም የነፃ ገበያ ቀልጣፋ እንዲሆን መሠረት የሆኑት የውል ክርክሮች፣ የቼክ የሂሣብ ወዘተ ክርክሮችን በተፋጠነ ስነ ስርዓት የሚታዩ ናቸው ፡፡በዚህ ልዩ ስርዐት ጊዜ መልስ ሳይሆን ተከሣሹ መልስ ማቅረቢያ ማስሰፈቀጃ ካላቀረበ / "ወዲያውኑ"ውሣኔ እንዲሰጥ ህጉ ያዛል ፡፡ በሌላ በኩል በሌሎች በተወሰኑ ጉዳዬች

ላይ /ስምን መለወጥ፣ ጋብቻ መፈፀምን መቃወም ፣ መቃወም መዝገባ ላይ የሰፈን ስለመርመር፣ ሰነድ ለመመልከት ስለመጠየቅ/ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ክስ ሣይሰማ "ማመልከቻን" ብቻ ተመልክቶ /እንዲመረመር ተደርጐ/ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርቡ ጉዳዬች በአንድ ቀን ሊወሱኑ የሚችለ፣ ይግባኝ የማይልባቸው ይግባኝ ቢባልባቸው እንኳን በ60 ቀን ሣይሆን በ10 ቀን ውስጥ ብቻ እንዲቀርብ የሚፈቀድላቸው ናቸው፡፡

በተለምዶ የቼክ ክርክሮች በልዩ ስነ-ስርዓት ተፋጥነው ውሣኔ እንዲሰጥባቸው በህጉ መሠረት ከሚቀርቡ በቀር አብዛኛው ክርክር / አሁን አሁን ከመሻሻለ ጋር/ በመደበኛው መስመር የሚመራ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም በአጭር ሊወሰኑ የሚገባቸውን ጉዳዬች በአንድ ጊዜ መወሰን የህጉም ፍላጐት መሆኑን ተከራካሪዎች እና ዳኞች በጥብቅ ተረድተው ወደ ህጉ አጥብቀው ሊመለሱ ይገባል፡፡

ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ ካገኙ በኋላ በመካከለኛ ደረጃ ለሚገኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብን ህጋችን ይፈቅዳለ፡፡ መካከለኛው ፍ/ቤት የበታች ፍ/ቤት ለሰጠው ውሣኔ ላይ ሙሉውን መዝገብ ይከልሣል/ Review de novo/ ተጨማሪ ማስረጃ የመስማት እድል ቢኖረውም በአብዛኛው በመጀመሪያው ሪከርድ /መዝገብ ተመስርተው ውሣኔ ይሰጣለ፡፡ የፍ/ስ/ስ ህጋችን 2ተኛ ይግባኝ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ተሻሽሏል ፡፡ ይሁን እንጅ አሁን 2ተኛ ይግባኝ በልዩ ሁኔታ ብቻ የሚቀርቡ የዳኝነት ስርዐት አለን፡፡ ለምሣሌ በፌዴራል ጉዳይ ላይ የጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሰሚው ከተስማማ 2ተኛ ይግባኝ አይኖርም፡፡ ጉዳዩ በሰበር ብቻ ይታያል፡፡ በንድፈ ሃሣብ ደረጃ 2ኛ ይግባኝ ሲቀርብ የህግ ጥያቄ ብቻ ይመረምራል፡፡ በሀገራችን አሁንም 2ኛ ይግባኝ ሲቀርብ በተግባር በልምድ / ሙሉ ክለሣ ነው የሚደረገው ፡፡ ሰበር በመሠረቱ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት፣ በክልል ጉዳይ በክልል ፍ/ቤቶች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በክልሎች ጠ/ፍ/ቤት እንዲሁም በክልል ከፍ/ፍ/ቤቶች /በአማራ/ ይታያል፡፡ በማናቸውም ፍ/ቤት በመጨረሻ ደረጃ በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ ሰበር ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ለክልል ጠ/ፍ/ቤት፣ የማ/ፍ/ቤት ክርክሮች እና ደግሞ ለክልል ከፍ/ፍ/ቤት /አማራ/ ይቀርባል፡፡ በሰበር የሚሰጡ ውሣኔዎች በመሠረቱ የዳኝነት አካሉ በህግ አውጪው በህግ መልኩ የወጡ ደንቦች /norms/ ተገዥ እንዲሆን ለማስቻል አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም /authoritative interpretation/ እንዲሰጥበት የሚጠበቅ ሲሆን በሀገራችን

የፍትህ ስርዓት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሚሰጠው የሰበር ውሳኔ ብቻ ነው የዚህ ውጤት የማኖረው፡፡ ሰበር / cassation /caser ከሚለው የመጣ/ በጥሬ ትርጉሙ መሰበር / break, quash / ማድረግ ማለት በመሆኑ አንዳንድ ሀገሮች በሰበር የሚሰጡ ውሳኔዎች የበታች ውሳኔን በመሻር መልሶ መላክ እንጅ በራስ ውሳኔ አይተካም፡፡ በሀገሪችን የፍትህ አስተዳዳር ግን የሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ከሻራ በኋላ በራሱ ውሳኔ ተክቶ እንዲመልስ ህጉ ይፈቅዳል፡፡ / ስዊዘርላንድ ን ፣ጀርመን፣ አውስትራሊያ በውጤት የኛው አይነት ስርዓት አላቸው ፡፡ /

በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ውስጥ መንግስትን የሚመለከቱ የፍ/ብሔር ጉዳዬችም እንደማንኛውም የፍ/ብሔር ክርክር በመደበኛ ፍ/ቤት ይታያሉ፡፡ ሌሎች ሀገሮች የሚፈቀዱት የአስተዳደር ፍ/ቤት በዚህ መልኩ ለሚመጡ የፍ/ብሔር ጉዳዬች አልተቋቋመም፡፡ በጀርመን ያለው የአስ/ር ፍ/ቤት በመደበኛ ፍ/ቤት ውስጥ ሆኖ የመንግስት የፍ/ብሔር ክርክሮችን የሚመለከት ሲሆን በስነ-ስርዓቱም ያን ያህል ጥብቅ ያልሆነና /informal/ ወጪ ቆጣቢ / less expensive/ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ሌላው በሰነ- ስርዓት ጉዳይ ላይ በእርግጥ የተሟጋች እና የዳኞች ሚና እና ኃላፊነት / Role and responsibility / ምንድን ነው የሚለውን እንደ ስርዓት / system/ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በልማድ የአንድ ሀገርን የፍትህ ስርዓት ብቻ ሣይሆን የሲቪል ሎው እና የኮመን ሎው ተከታይ ሀገራት ይለዩበታል የሚባልበት አንዱ ይህ ነው፡፡

በጥቅሉ ስንመለከተው በፍትህ ስርዓታችን ውስጥ በእርግጥ ተሟጋቶች ክርክራቸው /the matter in dispute/ ምንድን ነው? አግባብ ያለው ማስረጃ የትኛው ነው? በየቀጠሮው እና በመጨረሻ የሚኖሩ ቀጠሮዎች መቼ ይሁኑ? በህጉ እና በማስረጃው መሠረት ውሣኔው ምን መሆን አለበት? የሚሉትን የሚመልስልን በንቃት ዳኛው ነው፡፡ እነዚህ ሂደቶች ውስጥ የተሟጋች /ጠበቃ/ ሚና “ቀሪው” /Residual/ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በንፅፅር /metaphor/ ለመግ ለፅዳኛው “እንደ ቄሱ” ተሟጋች ደግሞ እንደ ደቀ መዝሙሩ /acolytes/ ናቸው ማለት ነው ፡፡ በኮመን ሎው ሀገሮች ነገሩ በተገላቢጦሽ ሆኖ ዳኛው “passive moderator” መሆኑ ይታወቃል፡፡ የJury ስርዓት በሚከተሉ ሀገራት ደግሞ የበለጠ “passive ይሆናል፡፡ በኮመን ሎው

ሀገራት ተከራካሪዎች በእርግጥም ተሟጋቾች /combatants/ ናቸው እንደ /እግር ኳስ፣ ነፃ ትግል ጨዋታ/ ፡፡

ይሁን እንጅ የሀገራችን የፍትህ ስርዓት ሁሉም አይነት ክርክሮች ላይ የሚኖረውን የዳኛ እና የተከራካሪ ወገኖች ሚና ተመሣሣይ አያደርገውም፡፡ በተለይ ዘመናዊ በሆነ የንግድ ክርክር /commercial litigation/ እና በቤተሰብ ክርክር ላይ የዳኞች ሚና እንደ ስራ መሪ /managerial role/ ሆኖ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር የኮሚቴ አይነት ስራ ይሰራል ለማለት ይቻላል፡፡ ክርክሩ መጨረሻ እልባት የሚያገኘው በክርክር ብቻ ሣይሆን ተከታታይ የሆነ የግልግል /mediation/ እና ድርድር /negotiation/ ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ ነው፡፡

ክርክሩ ወሣኝ አካልን /forum/ በመምረጥ የሚጀመር ሲሆን በውል ካልታሰረ በቀር ይህንን ፎረም የመምረጥ መብት ያለው ተከራካሪ ወገን / በተለይም የተጉዳው/ ነው ዳኞች በዚህ ጊዜ የሚኖራቸው ሚና አውንታዊ negative/ ስልጣን ነው፡፡ ተከራካሪ ወገን የማይገባ ወይም የማይመች መድረክ በመረጠ ቁጥር መመለስ /ወይም ከመቀበል / መታቀብ ብቻ ነው፡፡

የክርክሩ መድረክ ከተመረጠ በኋላ የክስ እና የመልስንም ይዘት / የለም እንደሆነ የተከሣሺ ክስን/ መወሰን የሚችሉት ተከራካሪ ወገኖች ናቸው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንን የመወሰን " ስልጣን" ይኑራቸውም እንጅ በሀገራችን የፍትህ አስተዳዳር ይህ ስልጣን ያላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለማድረግ ዳኞች ክርክሮች እንዲሻሻሉ ለማድረግ የሚያስችል ስፊ ሚና እንደሚጫወቱ ይፈቅዳል ይህንን ሚና በራሳቸው ተነሳሺነት /motion/ እንዲፈፅሙትም ይጠበቃል፡፡ ይህ ሌሎች ሀገሮች ጠባብ በተለይ በኮመን ሎው ሀገሮች የበለጠ ጠባብ ነው፡፡ በሀገራችን ይህ ሚና በስፋት ቢተገበር የፍታሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን የተስተካከለ ፍትህ የሚሰጥበት እንዲሆን ያስችላል፡፡ ዳኞች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ቢሆን ለክርክሩ መቅረብ ያለበትን ማስረጃ relevancy በተዘዋዋሪ ይወስናሉ ፡፡ በንፅፅር ለመናገር "አማኞች"/ believer/ ከመጽሐፉ መማር ያለባቸው ርዕስ ይመርጣሉ "ቄሶች ደግሞ ትምህርቱን /sermon / ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህ ሚና ዳኞች የቀረቡላቸውን ክርክሮች ተቀብለው ተከሳሺን ከመጥራታቸው በፊት "የክስ ምክንያት አለ? ብለው እንዲመረምሩ የሚፈቅድ በመሆኑ በቂ ክርክር ወይም የክስ ምክንያት ሣይኖር የሚቀርቡ ክርክሮች እንዳይቀጥሉ የሚያደርግም ነው፡፡ ለምሣለ

የማይንቀሣቀሱ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ አግባብ ያለው የምዝገባ ማስረጃ ካልቀረበ በህጉ መሠረት በቂ ምክንያት የለም በማለት መመለስ የሚየስችላቸው ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ለበርካታ ኢንቨስትመንት ስራዎች ማስነሺያ / ማገጃ/ ምክንያት ነው እየተባለ ትችት ሲቀርብበት የሚሰማው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር በህጉ መሠረት ሁከት መኖሩን ካላረጋገጠ / ከመነሻው/ ተቀባይነት የለውም ቢባል እንቨስተር አይስተጓጐልም፤ ፍ/ቤቶችም ተስፋ በሌላቸው ክርክሮች አይጨናነቁም፡፡ ተከራካሪ ወገን ክሱን ሲመሠርት የክስ ምክንያት አለኝ በማለት የያዋጣኛል ግምገማ አድርጐ / feasibility evaluation/ ሊሆን ቢችልም የፍትህ ስርዓታችን ዳኞች በዚህ መልኩ የምሁራዊ እና ስትራቴጂካዊ ግምገማ / Intellectual evolution/ እንዲያደርጉም ይፈቅዳል፡፡ የሚያስፈልገው ክርክር የቀረበበትን ህግ አጥብቆ መመርመር ብቻ ነው፡፡ ውጤታማ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ትክክለ፣/ just / ውጤት ላይ ለመድረስ አንዱ የፍትህ አስተዳደር በራችን ይህ ነው፡፡ ሌላው ክርክሩ ከቀጠለ በኋላም ቢሆን ተከራካሪ ወገኖች ለራሳቸው ፡ “ታክቲካዊ” ምክንያት የፃፉቸውን በመመርመር ዳኞች “ቴክኒካሊ” በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለው አንኳር ግጭት የትኛው ነው የሚለውን መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ዳኞች judicial activism/ ሚናን በስፋት እንዲጫወቱ በተለይም በቅድመ ምርመራ ተግባራቸው ስፊ የጉዳይ አመራር ክሎት እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ነው ፡፡ ዳኞች ጉዳዩን ከመነሻው ሲመርምሩ በስተመጨረሻ ከመንመለከታቸው 3ት መንገዶች /tracks/ የተያዘው ጉዳይ በየትኛው / /track/መግባት አለበት የሚለውንም ለመወሰን ያስችለቸዋል ፡፡ ይህ የስራ አመራር ክህሎት ጉዳዩ መታየት በጀመረበት ጊዜ ብቻ ሣይሆን በክርክሩ ሂደት ሁሉ ለመተግበር ስርዓታችን ያስችላል፡፡ ህጉ እና ስነ-ስርዓቱ በአግባቡ እንዲተገበር በመፈልግ ረገድ ስርዓታችን የዳኛ ሚና ከፍተኛ እንዲሆን የሚፈለግ /judge central / ሲሆን ይህም ለተገልጋዩ ቀልጣፋ ፣ ውጤታማ፣ ፍትሐዊ የሆነ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ እንዲቻል መሆኑን ታሳቢ ማድረግ ይገባል፡፡ ስርዓቱ በመጨረሻ አገልግሎቱ ዜጋ ተኮር “service /client centered” / ነው ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ሀገሮች በተለይ እንደሚያደርጉት በተለይ በንግድ ክርክሮች ፣ ውስብስብ ጭብጥ ባለባቸው ክርክሮች እና ከፍተኛ ደረጃ ቴክኒካል /ምህድስና፣ ሃሰብ ፣ ሳይንስት የወጭ ህግ ትንተና ፣ ቋንቋ.../ በሆኑ ክርክርሮች ላይ ይህ ሚና ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ዳኞች በተምዶ ሚናቸው ውሳኔ መስጠት ብቻ /” sheer

decisional function” / ነው የሚለው እምነት ተለውጦ የተከራካሪ ወገን ንቁ እና ፈጣሪ / active creative / ሚና እንደሚያስፈልግ ሁሉ የዳኞችም የበለጠ ተነሳሽ ፣ ፈጠራ፣ አትኩረት ሰጪ፣ ተለዋዋጭ/ flexible/ ሥራ አመራራዊ ሚና ጉልቶ ሊሰመርበት ይገባል።። *የፍ/ብሔር የፍትህ ስርዓታችን ይህንን ይፈቅዳል። የተፋጠነ ስነ-ስርዓት አላማ ክርክሮች ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚ፣ ውጪ ቆጣቢ ወዘተ በሆነ መልኩ መጠናቀቅ አለባቸው የሚለው ግብ ይህን ኃላፊነት የሚጠቀልል ነገው ልዩ ህጎችን ስንመለከትም /ምሣሌ የሊዝ ፣ እንቪስትመንት ህጐች/ ክርክሮች በተለይ ያለ ብዙ ውጣ ውረድ በአጭር ጊዜ መወሰን አለባቸው ማለቱ የዳኞች ኃላፊነት በስርዓታችን ድረብ መሆኑን ያስገነዝበናል።*

በአጠቃላይ የዳኞች እና የተከራካሪ ወገኖችን ኃላፊነት ከስነ- ስርዓቱ ህጉ አጠቃላይ ይዘት ስንመለከተው ጉዳዬች በሂደታቸው እና በውጤታቸው ትክክለኛ /just/ እንዲሆን ማስቻል እንደሆነ እንረዳለን። የጨዋታውን ሜዳ ለተከራካሪ ወገኖች እኩል በማድረግ ወጪና ጊዜን መቆጠብ ይፈለጋል። ዳኞት ጉዳይን በሚመለከቱበት ጊዜ የገንዘቡን መጠን፣ የጉዳዩን ክብደት እና ጠቀሚታ ፣ የጭብጡን ውስብስባነት ፣ የተከሰራካሪ ወገኖች የገንዘብ እና የእውቀት አቅም፣ የፍ/ቤቱንም የሐብት /ሰው፣ ገንዘብ/ መጠን፣ የግራ ቀኙን የማስረጃ ክብደት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ለምሣሌ የብር 10,000 ብድርን በሰው ማስረጃ አስረዳለሁ የሚለው ክርክር ከመቀበል በፊት የፍ/ብሔር ህጉ በዚህ ማስረጃ ላይ ምን ይላል የሚለውን መመርመር ይገባቸዋል። ከፍ ሲል እንደተመለከተው ክርክር በመደበኛው ስነ- ስርዓት፣ በተፋጠነ ወይመ በክለሣ ስነ- ስርዓተ የሚመራ መሆኑን አስቀድመው መለየት ይገባቸዋል። ፍትህ ሊሰጥ የሚገባው የእንደ ጉዳዩ አይነት ነው።/ triages should give in divided attention to cases/ ። አንድ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዘዝ በአሉታ ወይም በአውንታ በሌሎች ጉዳዬች ላይም ተፅዕኖ እንዳለው እንዲገነዘቡ የህጉ መንፈስ ያዛል ፍትህ ለሁሉም መድረስ ይኖርበታል። ፍትህ ሐብትን ግምትም ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚጠፋ ገንዘብ ወይም የሰው ኃይል ሐበት በሌለው ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መረዳትን ይጠብቃል። የፍ/ብሔር ስነ- ስርዓት ህጋችን በተለያዩ ቦታ ይህ ግዴታ ከተሟጋች የሚጠበቅ /expected / እንዲሁም የግድ መፈፀም ያለበት /required / መሆኑን ያሳየናል። ተከራካሪ ወገን በሐሰት ቢጠቀስ ትክክለኛው ሰው ያለኪሣራ እንዲተካ የሚደረገው “ተንኮል” ያልተዘለለ ሲሆን መሆኑ፣ በመጀሪያ ያልቀረበ ክርክር /ማስረጃ/ በሌላ ጊዜ

ለማቅረብ በቂ ምክንያት ማቅረብ ወይም /እንደኪሣራ መክፈል የሚጠበቁ መሆኑ፣ ችልተኝነት /ምሣሌ በመጥሪያ አደራረስ/ ክስን አስከ መዘጋት የሚያደርስ ትዕዛዝ የሚያሰጥ መሆኑ፣ ክርክር /መልስ/ እጥር ፣ ግልፅ እና ያልተድበሰበሰ እንዲሆን መጠበቁ፣ ቀጠሮ ሲሰጥ ጊዜው በቀጠሮው ምክንያት ከሆነው ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለበት ሲሆን የተከራካሪ ጠበቃ /ነገረ ፈጅ/ በቀጠሮ አለመቅረብ ተጨማሪ ቀጠሮ ለመስጠት ምክንያት የማይሆን መሆኑ፣ የቀጠሮው ምክንያት በተከራካሪ ወገን ጉድለት ያልተፈፀመ ከሆነ ያለተጨማሪ ቀጠሮ ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠት ያለበት መሆኑ ፣ ወዘተ ለዚሁ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖችም በክርክሩ ሂደት እና ትክክለኛ ውሣኔ በመስጠት ሂደት ላይ ክፍ/ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታም አለባቸው ማለት ነው።

ፍ/ቤቶች ጉዳዬች በፍጥነት እና ውጤታማ በሆነ አግባብ እልባት እንዲገኙ የሚያስችለው ተጨማሪ ስልጣንም በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥም ተመልክቷል። ለአብነት ተከራካሪ ወገኖች የሚያለያያቸውን በስምምነት ላይተው እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣ ጭብጥን አስቀድሞ መያዝና በህጉ መሠረት ቅደም ተከተል አስይዞ መወሰን፣ ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ከፍ/ቤት ውጭ በእረቅ በግልግል እንደጨረሱ ማበረታታት ወይም ማሳሰብ ፣ ይችላል። እነዚህ የስነ- ስርዓት ድንጋጌዎች በፍ/ብሔር አስተዳደራችን ሙግት ፍትሐዊ በሆነ መልኩ እንዲቋረጭ በማለም የተቀመጡ ናቸው የፍ/ብሔር ስነ- ስርዓት ህጋችን ይህንኑ አላማ ለማሣካት እንዲቻል በፅሁፍ የሚቀርቡ ክርክሮች ይዘትን አስመልክቶ በአባሪነት ፎርም መያዙንም ማስታወሱ ተገቢ ነው።


ሌላው ሊሰመርበት የሚገባው የፍ/አስተዳደር ስርዓታችን በስነ- ስርዓት ህጉ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው እንደ ኮመን ሎው ወይም ሲቪል ሎው ስርዓት ወደ አንድ ጫፍ የደረሰ ሣይሆን ክርክሮች በፅሑፍም በቃልም ተቀናጅተው እንዲቀርቡ የሚፈቀድ ስርዓት ያለን መሆኑ ነው። የፅሁፍ ክርክርም ቢሆን ይዘቱ አሁን በገፅ እየተቆጠረ እንደሚቀርበው መሆን አያስፈልገውም። ፍሬ ነገሩን ከጠቀሰ /ፀሐፊዎች /statement of fact /case/ ይሉታል/ በቂ ነው። ከፍተኛ ስራ የሚከናወነው በክስ / /ክርክር/ መሰማት እና ማስረጃ መመርመር ጊዜ ነው። የፅሁፍ ቅብብል በአንዳንድ ሀገሮች በመርህ ደረጃ በዳኞች ሳይሆን በሌሎች የፍርድ ቤት ባልደረቦች /ሪጅስትራር/ አማካኝነት የሚፈፀም ሲሆን የሀገራችን የፍትህ ስርዓት ይህም ተግባር በዳኞች እንዲከናወን ይጠብቃል። ዳኞች ይህን ተግባር ሲከውኑ ከጉዳዬች መጨናነቅ ጋር በዋናው ጭብጥ መያዝ እና የማስረጃ

ቀደም ተከተል መለየት ተግባርን ሲዘነጉ ይስተዋላል። የተከሳሺ መልስ ከቀረበ በኋላም የከሳሺ ምስክር እንዲቀርብ የሚታዘዘው ለዚሁ ነው። ማስረጃ ሁሉ ከተሰማ በኋላ በስተመጨረሻ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ጭብጥ ሲያዝ ክርክሩ የህግ ብቻ እየሆነ / ወይም ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የሌለው መሆኑ እየተለየ ወዘተ መዝገብ ሲዘጋ ይስተዋላል። ጭብጥን እስከ ክርክሩ መጨረሻ አድፍጦ ማኖረ ክርክር በእርግጥ ግልፅ /public/ ነበር? ፍርድ ቤቱስ በአሰራሩ ለተሞጋች ተደራሽ ነበር? የመደመጥ መብትን አይጠብም የተሟጋች ፍ/ቤት ጊዜና ጉልበት አያባክንም ።

6. ተዋንያን /Actors/

በአንድ ሀገር የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው በርካታ ባለሙያዎች አካላት ይገኛሉ። እያንዳንዱ ባለሙያ አበሰራው የተያያዘ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ጋር በመስተብር የሚሰራ ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛም /Interdependent / የሆነ ነው። የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደሩ ጠቃሚ እንዲሆንን እና ህይወት እንዲኖረው የሚያስችሉት እነሁ የግል ጠበቆች፣ ዳኞች፣ ዐ/ሕግ፣ የመንግስት ነገረ ፈጆች፣ የህግ ምሁራን ናቸው። የሰራው ትስስር እና ተመጋቢ መሆኑ በየደረጃው ለሚሰጠው ውሳኔ የሙያ ነፃነት መግፊያ ምክንያት ግን አይሆንም።

በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ውስጥ ተሣታፊ የሚሆኑት ባለሙያዎች መገኛቸው የህግ ት/ት/ቤት ናቸው /ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው።/ በባሙያቻዋ በህግ ት/ት/ቤት ቆይታቸው የሚወስዱት ት/ት ጠቅላላ /general / የሚባል ነው። እንደ ኮመን ሎው ሀገሮች አንድን ጉዳይ በዝርዝር በማየት ሣይሆን በአጠቃላይ የህግ ስርዓቶች በማጥናት የሚጀምር ነው። ይህንን የህግ



ቅርንጫፍ በክፍፍል ያልተማረ የለም። እንዳውም ሁሉም ኮርሶች ሲጀምሩ በዚሁ ክፍፍል ይመሰላል። የክፍፍሉ መነሻ፣ ፅንሰ ሃሣቦች እና መርሆዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል። ከዚህ በቀር ዳኞች በዚህ ቦታ ከመመደባቸው በፊት የቅደምስራ ስልጠና እንዲወስዱ የማድረግ ጀምር በሀገራችን ይታያል። አሉ ሌሎች ሀገሮችም የረዥም ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና ከተግባር ልምድ ጋር እንዲሰጥ ይደረጋሉ።/ ፈረንሣይ ፣ጃፖን/የተግባር ልምምድ ከተጠናቀቀ በኋላም ፈተና ማለፍን የሚጠይቁ አሉ/ ፈረንሣይ ፣ጀርመን/ ።
በሀገራችን የፍትህ አስተዳደር ይህ ሁኔታ በቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለወጠ ስልጠና ቅድመ ሁኔታ መሆን ጀምሯል።ዳኞች በህግ ስልጠና ውስጥ ማለፋቸው is a civil servant who performs important but essentiality uncreative functions ” **በማለት ያስቀመጠው እደዲቀየር ያደርጋል የሚል እውነት አለ።**

በፍ/ብሔር ፍትህ አስተደደሮችን ውስጥ ነገር ፈጆች ጠቃሚ ቦታ አላቸው በዐ/ሕግም በተለዩ የህዝብ ጥቅም አለባቸው የፍ/ብሔር ጉዳዬች ላይ ጣልቃ እየገባ ወይም ክርክሩ በቀጥታ በመያዝ እንደከራከር ስርዓታችን ይፈቅዳል። የገንዘብ መጠናቸው ከፍተኛ በሆኑ የመንግስት የፍ/ብሔር ክርክሮች፣ በሰዎች መብት ፣ ችሎታ ስለማጣት፣ ስለጋብቻ እና ስለኪሣራ በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ቀርበው መከራከር መቻላቸው ለአብነት ሊጠቀስ ይችላሉ። በኛው ስርዓት ዐ/ሕግ የዳኝነት አካል የሚሆነው ውሣኔ ለመስጠት ተለይተው በተሰጡት ጉዳዬች ላይ /ምሣሌ/ የከተማ ቤት ክርክር ላይ የወሣኝ ቦርድ ሰብሳቢ በመሆን/ ብቻ ነው። ከዛ ውጪ የፍ/ብሔር የፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ በቀጥታ በዳኝነት ለመስራት የዳኝነት ስራ ውስጥ ራሱን በቻለ አኳኋም መመደብ ይኖርበታል።

በመጨረሻም በፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደሮችን ውስጥ የህግ ምሁራን ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ይጠበቃል ። በመግቢያው ላይ እንደተመለከተው የህግ ምሁራን የፍትህ ስረዓታችን ለመሻሻል ግንባርቀደም ሚና ሊጫወቱ ይገባል። የማህበረሰቡ ሳይንስ ምሁሩ ዋሽረ “the unforgotten men of the law “ እንዳላቸው ብለክስቶን “ living oracles “ እንዲላቸው የፍት/ብሔር ፍትህ አስተዳደራችን ህግ መንግስት ያስቀመጠውን ግብ ማሳኪያ እንዲሆን ከፍተኛ የሀገራዊ ሚናቸውን ለውጦ ይገባል።

በፍ/ብሔር ፍትህ አሰተዳደራችን ውስጥ ሌላው ተዋናና ጠበቆች ናቸው። ጠበቆች የክልል፣ የፌዴራል ተብለው በሁለት የተለያዩ አካላት የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጣቸው ናቸው ። የትምህርት ዝግጅታቸው እና /ወይም በህግ የካበቱት ልምድ

ታይቶ በጉባዔ ፈተና አልፈው ፈቃዳ የሚሰጣቸው ናቸው።።ጠበቆች የፍ/ብሔር የህግ ምክር በመስጠት፣ ክስና መልስ እንዲሁም ልዩ ልዩ ፅሑፎችን በማዘጋጀት ፣ ውለታን፣ ጋብቻን፣በማርቀቅ፣ በፍ/ቤት ቀርበው በመከራከር ይሣተፋሉ ።።በሀገራችን ፍትህ አስተዳደር የጠበቀ ደረጃ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ ሆኖ በሁሉም ፍ/ቤቶች መከራከር የሚያስችል ወይም በተወሰኑት ብቻ መከራከር የሚየስችል ነው።። ፍቃድ ያልተሰጣቸው ዜጐችም ይህንን ማዕረግ ሣይጠቁሙ በማማከር እና ክርክር ፅሁፍ በማዘጋጀት የሚሳተፉ መሆኑ ይታወቃል።። በሀገራችን ያሉ ጠበቆች በአይነት ቢከፋፈሉም ተግባራቸው ከላይ የተመለከትነው ወሰን ድረስ ብቻ ነው!! ከላይ ከተጠቀሰው ውጪ ሰነድ በማረጋገጥ / Citification/ ሰነድን ማስቀመጥ/ depository / በመሆን አያገለግሉም።። በተለምዶ እንደሚታወቀውም ጠበቆቻችን አንዱ ተግባር ላይ በተለይ ተክናው /specialization/ የሚሰራ ሳይሆን የተፈቀደውን ሁሉንም ተግባር የሚከናወኑ ናቸው። ።

ውድ ሠልጣኞች እስካሁን ድረስ ለማመልከት የሞከርነው ባገራችን ውስጥ ያለው የፍታሐ ብሔር ፍትህ ስርዐት ነው።። ይህ ስርዓት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጐኖች አሉት ።። ደካማ ጐኖች በተለይ በአፈፃፀም ደረጃ የሚገለፁ ናቸው።። ቀጥለን የሥርዐቱ ደካማና ጠንካራ ጐኖች በጥቅል የመፍትሔ ሃሣብ ጋር እንመለከታለን።።

7.ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት አስፈላጊነት

የፍትሐብሔር ክርክሮች ምንም እንኳን በሁለት ወገኖች የሚደረጉ ክርክሮች ቢሆኑም በሃገሪቱ አጠቃላይ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማትና የሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው።። ስለሆነም በፍትሐብሔር ለሚነሱ ክርክሮች አፋጣኝ ፍትሃዊ ተገማችና ውጤታማ የሆነ_ወሰን የሚሰጥ ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት የግድ ይላል።። በሁለት ባለጉዳዮች የተነሳው የፍትሐብሔር ክርክር ሕግን መሰረት አድርጎ በሰላማዊ አግባብ ካልተፈታ ዞሮ ዞሮ ወደ ሃይል ማምራቱ አይቀርም።። ሃይል ደግሞ የብጥብጥ የፀረ ሰላም ምንጭ መሆኑ አይካድም።። በሃገራችን የነበረው ተጨባጭ ሁኔታ መለስ ብለን ብንቃኝ ቅንጣት በምታህል የገጠር መሬት በግለሰቦች የተነሳው ክርክር ሰላማዊ መፍትሔ አጥቶ ከግለሰቦች ጠብ ጀምሮ ወደ ዘመድ አዝማድ ከዚያም

አልፎ ወደጉላና ሃይማኖት እንዲሁም ብሔር ብሄረሰብ ዘልቆ በመግባት እየተቀጣጠለ በሃገራችን ላይ ከፍተኛ ብጥብጥ ሲፈጥር እንደነበረ የሚታወቅ ነው።
በሕግ መሰረት ያልተቋጨ የውል ክርክም እንዲሁ በሁለት ግለሰቦች ከሚፈጠረው የጥላቻ ጠባሳ ባሻገር በሃገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲሁም ኢንቨስትመንት በመሳብና በነፃ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመወጣት ያለው ተዕዕኖ የከፋ ነው።

በአሰሪና ሰራተኛ የተነሳ ክርክርም ቢሆን በአፋጣኝ ሕግን መሰረት አድርጎ መቋጫ ካላገኘ የኢንዱስትሪ ሰላምን ከማናጋቱ ባሻገር ሰራተኛው ወደ የስራ ማቆም አድማ በመምራት የሃገሪቱን ገቢ ያቀጭጫል። ወደ ብጥብጥ ከተሻገረም በሃገሪቱ ሃብትና ንብርት ከፍተኛ ውድመትን ያስከትላል ከዚያም አልፎ አስከፊ የሰው እልቂት ያደርሳል። ስርዓቱንም በእጅግ ይፈታተናል። በአለማችን በአውሮፖና በተለያዩ ሃገራት የሚታዩት የሰራተኛው የስራ ማቆም አድማዎች የሚያረጋግጡልንም ይህንኑ ነው።

በመንግስትና በሕብረተሰቡ ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግለት የጋብቻ ጉዳይም እንዲሁ አፋጣኝና ሕጋዊ ምላሽ ካላገኘ የቤተሰብ መፍረስ ያስከትላል። የህፃናት መብት አደጋ ላይ ይወድቃል ጤናማ ዜጋን የመገንባቱ ጉዳይ አጠያያቂ ይሆናል። ስለሆነም ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ግለሰቦችም የሆኑ ተቋማት መብቶቻቸውን በተገቢው መንገድ ለማስከበር ኢንቨስትመንትን በማበራታታት እንዲሁም የውስጥም ይሆን የውጭ የንግድ ልውውጥ ስለማዊና ሕጋዊ በመሆነ መንግድ በማስኬድ በሃገሪቱ ሰላም፣ ዲማክራሲ እንዲሁም ፈጣን ልማት በማረጋገጥ አንፃር የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው።
ለጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት እውን መሆን ደግሞ በሃገራችን ሆነ በሌሎች አገሮች ከታየው ልምድ መገንዘብ የሚቻለው ተዕዕኖ የሚያሳድሩ ክስተቶች መኖራቸውን ነው። እነዚህም፡-

- ሕብረተሰቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአስተሳሰቡ በእውቀቱና በፍላጎቱ እያደገ ሲሂድ የፍትሕ ስርዓቱ ከሕብረተሰቡ ፍላጎት ጋር ሊራመድ አለመቻል።
- ፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት ፈጣንና የተወሳሰበ የገበያ ልውውጥ እየተመዘገበ የፍትሕ ስርዓቱ ግን ከዚህ እድገት ጋር ተጣጥሞ ለመሄድ አለመቻል።

- የፍትሕ ስርዓቱ እጅግ ዘገምታዊ መሆንና (too slow) በየጊዜው ራሱን እየለወጠና እያሻሻለ የማይሄድ መሆኑ
- የፍትሕ ስርዓቱ በጣም ዘገምተዊ በመሆኑ ባለጉዳዮች ላልተገመቱና ከአቅም ባላይ ለሆኑ ወጪ መዳረግ (too expensive and unpredictable)
- የፍትሕ ስርዓቱ ተደራሽ ያልሆነ የተወሳሰበና በቀላሉ ባለጉዳዮች የሚገባ ያለመሆኑ (Very complex and in not understandable accessible) ተጠቃሽ ናቸው።

ይህም በመሆኑ ብዙ ሃገሮች ከሕብረተሰቡ ዕድገትና ፍላጎት፣ በፍጥነት በማደግ ላይ ካለው ፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት የኢኮኖሚ ለውጥና የገበያ ልውውጥ አብሮ ሊጓዝ የሚችል ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ለመገንባት የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት የማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት ለመመስረት ደፋ ቀና ሲሉ የሚታዩት።

የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ጠንካራ ከሆነ

- ሚዛናዊና ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይቻላል፣
- ባለጉዳዮች በእኩል አይን አይቶ የሚያስተናግድ ይሆናል፣
- ክርክር የሚወሰደው ጊዜና ወጪ ተገማች እንዲሆን ያስችላል litigation will be certain in terms of time and cost
- ካላንዳች ጂኦግራፊያዊ፣ ኢኮናሚያዊ፣ ስነስርዓታዊ መሰናክል በቀላሉ የሚደረስበት ይሆናል (accessible)
- ለሁሉም ጉዳዮች ተገቢውን ጊዜ ስጥቶ በመስማት ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል።
- ሁሉም ባለጉዳዩች የፍርድ ቤቱን አካሄድ በሚገባ ተረድተው ጉዳያቸውን በሙሉ እውቀት የሚከተታተሉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።
- ሁሉም ጉዳዮች ሕግን መሰረት አድርገው ሰለሚወሰኑ የሕግ የበላይነት ይሰፈናል ውጤታማ ይሆናል።

ይህ ከሆነ ደግሞ ሕብረተሰቡ በፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት አመኔታን ያሳድራል። በተለይ የውል ክርክር የንግድ ልውውጥ ክርክር በቀላሉ የሚቋጭና ፍትሃዊ

በሆነ መንግድ ቅልጥፍና በተሞላው ሁኔታ የሚወሰን ከሆነ ኢንቨስትሩ የሕግ ዋስትና አለኝ ሰለሚል በኢንቨስትመንቱ የሚጫወተው ሚና ያድጋል ይህ ማለት ደግሞ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ እምርታ እንዲታይ ያስችላል። እንድ አንድ ምሁር አገላለፅ በፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓቱ የሚደረገው የማሻሻል እምምጃ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል።

It is usually believed that civil justice reform will significantly improve economic performance (Sherwood 1999)

ለኢንቨስተሩ በመንግስት የሚደረግለት ድጋፍና ማበረታቻ ቢኖርም ዋናው ጥያቄው ለሃብቱና ለንበረቱ ዋስትና የሚሰጥ ጠንካራ አስተዳደር የፍትሕ ስርዓት አለ ወይ የለም የሚለው ነው። ይህም ከሚከተለው አገላለፅ መረዳት ይቻላል።

With out a strong justice system traders would be reluctant to enter info wealth enhanced exchanges for fear that the bargain wouldn't be honored. In Hobbes words when two parties enter into a contract "he that performeth first has no insurance the other will performed after because the bonds of words are too weak to bridle men's ambitions, avarice, anger as other passions with out the fear of same coercive power (Hobbes 1651)

አንድ የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት የውልን ክርክር በሚገባ የማያስፈፅም ከሆነ የሚባዛው ልውውጥ አየር ባየር ወደ መሆን ደረጃ የመራል ወይም ውል ሳይፈርስ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበትን አካሄድ እየመረጠ ሃብቱን ያሰማራል። ስለሆነም በአንድ ሃገር ጠንካራ የኢኮኖሚ ዕድገት ለመሰረት የሚችለው ለረዥም ጊዜ በሚቆዩ ውሎች ላይ የተመሰረተ የንግድ ልውውጥ ልምድ ሲኖርና ይህንኑም ሊያስፈፅም የሚችል ጠንካራ የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ሲኖር ነው። ይህም አንዳንድ ሊቃውንቶች በሚከተለው መልክ ይገልፁታል In William's (1995) view a high performance economy is one that is characterized by a significant number of long term contracts Just the type of business relation ships that is unlikely to thrive in the absence of a well- functioning justice

በፔሩ በተደረገው ጥናት አብዛኛዎቹ ነጋዲዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁት ሰው በስተቀር ምንም እንኳን ዎጋው ቢቀንስም ከአዲስ ነጋዴ ጋር ውል እንደማይገቡ ጥናቶች ያስረዳሉ። የዚህም ዋናው ምክንያት ከመጀመሪያው ጋር የመሰረቱት ውል ከረጅም ግዜ

ተሞክሮ በኋላ አስተማማኝነቱ ስላረጋገጡትና ውሉን አያፈርስም ብለው ስለተማመኑ ሲሆን አዲሱን ግን በተግባር አልሞከሩትም ውሉን ቢያፈርስም ውሉ የሚያስፈፀም ጠንካራ የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት በሀገሪቱ የለም የሚል ስጋት ስላላቸው ነው።

In Peru almost a third of those responding to a world Bank poll said that they wouldn't switch from a trusted supplier to a new one even if a lower price were offered for fear the new supplier couldn't beheld to the new bargain (Dokoliad 1996)

በኢኮዶርም እንዲሁ የቢዝነስ ሰዎች ሃብታቸው በሃገሪቱ ለማሰማራት ብዙ አይደፍሩም የዚህም ዋና ምክንያት ውሎችን የሚያስፈፅም ጠንካራ የፍትህ ስርዓት ባለመኖሩ ነው።

A similar survey in Ecuador found that business men were hesitant to in vest because of the uncertainty of and potential clack of timeliness in enforcing contract rights (Dokolias 1996)

በብራዚልም እንዲሁም ብዙ ኢንቨስተሮች ተጠይቀው ሲመልሱ ብራዚል በገበያ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደአላዩ ሃገሮች ልክ የሚራመድ የፍትህ ስርዓት ቢኖራት ኖሮ የሃገር ውሰጥ ኢንቨስትመንት 10% ያድግ ነበር ሲሉ ይገልፃሉ።

In depth interviews of Brazilian entrepreneurs suggest that domestic investment would increase 10 percent if the Brazilian Justice were on par with those that advanced market economics (catelar pinheris 1998)

አሁን በቅርቡ በ69 ሃገራት በሚገኙ በ3600 የንግድ ተቋሞች በተደረገው ጥናት ከ70% የሚሆኑ መልስ ሰጪዎች የሚገልፁትም በተለያዩ ሃገራት ያለው ተገማች ያልሆነ የፍትህ ስርዓት በንግድ ስራ እንቅስቃሴያቸው ዋንኛ ጋሬጣ እንደሆነባቸው ይገልፃሉ።

Most recently in a survey of 3600 firms in 69 countries more than 70 percent of the respondents said that an unpredictable justice system was a major problem in their business operations" (World Bank 1997:36) ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት መኖር በአንዲት ሃገር የኢኮኖሚ ግንባታ ምን ያህል ሚና ሊጫወት እንደሚችል ነው። በተለይም አንደኛ ባለ ድሃ አገር ከድህነት ለመውጣት ገና በመንገዳገድ ላይ ባለ ሃገር የጠንካራ የፍትሕ ሰርዓት መኖር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይሆንም። ብቻም ሳይሆን ጊዜ ሳይሰጥ ሊገነባ የሚገባና የህልውናም ጉዳይ ተደርጐ መወሰድ እንዳለበት ሊሰመርበት ይገባል።

ሌላው ምንም እንኳን የፍትሐብሐር የፍትህ ስርዓቱ ክርክርን ሰምቶ የሚወስን ቢሆንም የሚሰጠው ውሳኔ በሃገሪቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለውም መገንዘብም ያስፈልጋል፡፡ የፍትሕ ስርዓቱ እንድ አንድ የሙግት መፍቻ ዘዴ ይሁን እንጂ የተለያዩ ተያያዥ ስራዎችን በማከናወን በሃገሪቱ አጠቃላይ ስርዓት ግንባታ የሚጫወተው ሚና የላቀ መሆኑን የፍትሕ አካላትም ይሁኑ ሌሎች በውል ካልተረዱት አደገኛነቱ አይቀሬ ነው፡፡ የዚሁ የፍትሕ ስርዓት መጠናከር በሃገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ሁኔታ በመቀየርና የሕብረተሰቡን ፍላጎት በማሟላት የራሱ ድርሻ እንደሚጫወት በመረዳት ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት እንዲኖር የሚመለከተው ሁሉ ትኩረት ሰጥቶ ሊረባረብበት ይገባል፡፡

እሰከ አሁን ከተቀመጡት አገላለፆች መረዳት የሚቻለው ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት መገንባት ለአንዲት ሃገር ያለው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ከመሆኑም ባሻገር በሕገ መንግስቱ የተቀመጡትን የንብረትም ይሁን ሌሎች መብቶች በማስከበርና በማክበር ረገድም የላቀ ድርሻ እንዳለው ነው፡፡ የንብረት ባለሃብት መሆንና ሕገ መንግስታዊ እውቀና መስጠቱ ብቻ በራሱ በቂ አይሆንም፡፡ ይህንን በተግባር ሊተረጎም የሚችል ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት መኖር የግድ ይላል፡፡

የንብረት ባለሃብትነት ሕጋዊ ዋስትና አግኝቶ መከበር ደግሞ በራሱ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማሕብራዊ መረጋጋትን በመፍጠር እና ምርትንና ምረታማነትን በማሳደግ ገረድ በርካታ ጠቀሜታ አሉት፡፡

የንብረት ባለሃብትነት ለማህበሪዊ መረጋጋትና ድህነትም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የሚረጋገጠው አንድ ሰው ያገኘውን በእውቀቱ የፈጠረውን ወይም በጉልበቱ የሰራውን ወይም በሕግ መስረት በሌላ ሁኔታ በቁጥጥሩ ስር ያደረገውን ያለምንም ጣልቃ ገብነት በሰላም ለራሱ ጥቅም ሊያውለው ነው፡፡

የንብረት ባለሃብትነት በሕገ መንግስት በፍትሐብሔር እና በወንጀለ ሕጐች መከበር ለሃብት ክምችት ለቁጠባ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ባለንብረት በንብረቱ በመገልገል ትርፍ ወይም ሌላ ተጨማሪ ነገር ለማግኘት ጥረት ያደርገል፡፡ ለስራ ይነሳሳል፡፡ በዚህም የንግድ፣ የእርሻ፣ የኮንስትራክሽን ወይም የኢንዱስትሪ ወይም የሌላ ዓይነት ኢንቨስትመንት ስራም ይበረታታል አገርም ይበላፀጋል፣ ያድጋል፡፡ ለዚህ ሁሉ ቁልፍ ጉዳይ ግን በአንድ ሃገር የሚኖርው ጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት በአስተማማኝ

መሰረት ተገንብቶ በሃገራቱ አስተማማኝ ሰላም ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሲኖር ነው።

በአንዣሩ ደካማ የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት መኖር የፍትሕ ስርዓቱ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ ፍትሐዊ ተገማችና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል። ሃገራቱን ወደ አልተፈለገ ብጥብጥና የኢኮኖሚ ዝቅጠት ይመራል።

ዜጎች ጉዳያቸውን በሰላማዊ መንገድ እንደመፍታት በአቋራጭ የመፍታት መንግድ ይሻሉ። ይህ በአቋራጭ የመፍታት መንግድ ለጊዜው የመፍቻ መንገድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል በዘላቂነት ግን ሃገራቱን ለገፋ ቀውስ የሚዳርግ የሕብረተሰቡ የጋራ መግባባት (Social consensus) የሚያጨልም፣ ውጤቱ ወደ አልታወቀና በጣም ወደተወሳሰበ ማሕበራዊ ግንኙነት በማምራት አጠቃላይ ስርዓቱን የሚፈታተን ይሆናል። ይህንን አንዳንድ ምሁራን በዚህ መልክ ያስቀመጡታል the justice system in one country perform a series of vital functions for any political system… Law definition, conflict resolution, and social control, and where they fail to perform them according to citizens needs and expectations. There are a series of negative social. Political and economic consequences. Often their failure encourage the creation of alternative mechanism and practices that undercuts judicial legitmacy, and eventually threatens that of the entire political system

በሃገራችን ደካማ የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት እንዲኖር ከሚያደርጉት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹን መጥቀስ ያስፈልጋል።

በሃገራችን ደካማ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት መኖር ተጠቃሽ የሚሆኑት ከሃይለስላሴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለው ቁልፍ ችግር ምንም እንኳን የወጡት ሕጎች የራሳቸው ችግር ቢኖርባቸውም ዋንኛው ችግር ግን ሕጉ እያለ በልምድ መመራት ነው።

በሃይለስላሴ የነበሩት ዳኞች አብዛኛዎቹ ያልተማሩ ወይም በጣም አነስተኛ ትምህርት እንደነበራቸው ይታወቃል። እነዚህ ሰዎች የሚቀናቸው በልምድ መሐይድ እንጂ ዘመናዊ የሆኑ ሕጎችን መከተል አይደለም ቢፈልጉም እውቀቱም ይሁን ብቃቱ አልነበራቸውም።

በኃላም ወደ ፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓቱ የተቀላቀሉት ምሁራንም ቢሆኑም ያሻሻሉት ነገር የለም ባይባልም እነሱም ቢሆኑ የቆየውን ልምድ መቅረፍ አልቻሉም ብቻ ሳይሆን

የቆያቸውን ልምድ ይዘው መሄድ ቀጠሉ። ቀስ በቀስ ልምድ ሕጉን እየገዛው ሕጉ እየተተወ ልምድ ሕግ መሆን ጀመረ። ይህ እውነታ በቅርቡ ከዳኞች ጋር በተካሄደው የፍትሐብሔር የስነ ስርዓት ሕጎችን የተረሱ የወንጀል ስነ ስርዓት ሕጎች እንዲሁም በቅርቡ በአቶ መንበረፀሐይ ታደሰ የቀረበው የመያዣ ሕግ እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው። አሁን በፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት የሚታዩ የጉዳዮች መጓተት፣ የባለጉዳዮች መንገላታት ኢፍትሐዊ ወጪትና ተስፋ መቁረጥ ያልተፈለገ ወጪ አብዛኛዎቹ ከሕጉ የመነጩ አይደሉም። ይልቁንም በልምድ የዳበሩ ሕጉን ተክተው የሕግ አውጪውን ዓላማ በሚያጨናገፉቸው አሁን የሚታየው የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓቱ አስተዳደር በአጠቃላይ የፍትህ ስርዓቱን አመኔታን ተስፋ የመቁረጥን ሌላ የራስ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንግድ መፈለግ ሊከሰት ችሏል።

የደካማ የፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት ሌላው ችግር በዩንቨርሲቲዎች የሚሰጠው የሕግ ትምህርት ነው። በዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠው የሕግ ትምህርት የራሱ የሆነ አውንታዊ ጎን ቢኖሩትም ተማሪውን ግን ችግር ፈቹ ያለውን ስርዓት ተረድቶ ከሃገራችንና አለም አቀፋዊ ሁኔታ አዛምዶ ሕጎችን በስራ ላይ እንዲያውል የሚያስችል ብቃት ይዞ እንዲወጣ አድርጎ የሚቀርፅ አይደለም። የዚሁ ክፍተት የሚሟላ የዳኞችና የአቃቤ ሕግ ስልጣኝ ማዕከል አሁን በቅርቡ የተጀመረ እንጂ አብሮ ከፍርድ ቤቶች መቋቋም ጋር የተጀመረ አልነበረም። ይህም በመሆኑ ስርዓቱን ለማገልገል የሚሾሙት ዳኞች የእውቀት የክህሎትና የአስተሳሰብ ችግር የነበራቸው የፍትሐብሔር ስርዓቱን እንደማጠናከር ይበልጥ ደካማ እንዲሆን የራሳቸው አስተዋፅኦ አበርክተዋል ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም።

ሌላው የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ሰርዓቱ መዳከም ተጠቃሽ ተደርጎ የሚወሰደው የፍትሕ ስርዓቱ ከሕብረተሰቡ ፍላጎት ሃገሪቱ ልታስመዘግበው ከምትፈልገው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ሊራመድ አለመቻሉ ነው። የፍትህ ስርዓቱ ካለው አሃጉራዊ አለምአቀፋዊ የዕድገት አንፃር አብሮ የሚጓዝ ይህንንም መሰረት በማድረግ ራሱን ዘመናዊ በሆነ መለኩ የሚያደራጅ መሆን ቢገባው አሁን እንደ ጅምር ከማታየው መሻሻል በስተቀር ገና ብዙ የሚቀረው ነው። ጉዳዮችን ተዳራሽ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ ውጤታማ በሆነ መንግድ እንዲያልቁ የሚያስችል የሕብረተሰብ አመኔታ ያልተጎናፀፈ ነው ይህ ደግሞ ሃገሪቱ ልታስመዘግበው ለምትፈልገው ኢኮኖሚያዊ ስርዓትና ከድህነት የመውጣት ራኢ እንኳንስ የራሱን ሚና ሊጫወት ማነቆ ሆኖ ስርዓቱን ወደ ከፋ ችግር የሚጥል ነው።

ስለሆነም የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓቱ ጠንካራ እነደሆን ዘመናዊ መልኩ የተደራጀ ዘመናዊ አስተሳሰብ የተላበሰ የተሟላና ውጤታማ የሆነ መሆን ይኖርበታል። (it should be effective adequately resourced and organized) ከዚህ ጐን ለጐን አብሮ ሊታይ የሚገባው የፍትሐብሔር ስርዓት መዳከም አስተዋፅኦ የሚያደርግ ለፍትሐበሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓቱ መጠናከር የሚረዱ ሕጉ መቋቋም አለባቸው ያላቸው ተቋማት እንደ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝጋቢ አካል፣

- የወሊድ የሞት የጋብቻ መዝጋቢ አካል

- የኑዛዜና የሌሎች ሰነዶች ጠባቂ አካል ወዘተ ያለመቋቋም ናቸው። እነዚህ አካላት በፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት የሚሰጡት ውሳኔዎች አስተማማኝነት አሁን ላለው የልተፈለገ ውዝግብና መተራመስ እንዲሁም ከፍተኛ ወጪ የሚያስቀሩ ከመሆናቸውም ባሻገር አስተማማኝና ቀልጣፋ ውሳኔን ለመስጠት የሚያስችሉ ናቸው።

- ሌላው ለፍትሐብሔር የፍትሕ ሰርዓቱ መዳከም የራሱ የሆነ አሉታዊ ሚና ሊጫወት የሚችል የባለጉዳዮችና የምስክሮች ለፍትሕ ስርዓቱ ያላቸው አጋዥነት የሚገባውን ያህል አለመሆን ነው። በፍትሐበሔር የፍትሕ ስርዓት የባለጉዳዮች ትጋት የምስክሮች ቅንነት ቀልጣፋና ሕግን መሰረት ያደረገ ተአማኒነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት ያስችላል። ሆኖም አሁንም ቢሆን የባለጉዳዮች ነገሮችን የማወሳሰብ ጉዳያቸውን በተገቢው መልክና ሕገ በሚያዘው መሰረት አለማቅረብ በተለይም አንዳንድ ጠበቆች የሚያሳዩት ከሙያዊ ስነ ምግባር ውጪ የሆነ አካሄድ፣ በምስክሮች የሚታየው የቅነነት መጓደልና ለመመስከር ፍቃደኛ አለመሆን የፍትሐበሔር የፍትሕ ስርዓቱን ደካማ እንዲሆን የሚፈታተኑት ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ለፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት መዳከም ሳይጠቀስ የማያልፍ በፍርድ ቤቶች የጉዳዮች አካሄድ አመራር አለመኖር ነው።

የፍታብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ ተገማች ውጤታማ ገንዘብንና ጊዜን ቆጣቢ እንዲሆን ከተፈለገ ፍርድ ቤቶች የሚመሩበት የጉዳዮች አካሄድ አመራር (Case flow management) ሊኖራቸው ይገባል።

የጉዳዮች አካሄድ አመራር ስንል ጉዳዮች በባህሪያቸውና በውስብስብነታቸው ተለይተው ከክስ እስከ ውሳኔ አሰጣጥ ያለውን አካሄድ ማስቀመጥ ማለት ነው። ወደ ሃገራችን

የፍታብሔር ስነስርዓት ሕግ ስንመጣ ጉዳዮች በሶስት መንገዶች የሚመሩበት አገባብ ተካትቷል፡፡

ሀ. መደበኛ የሙግት አቅጣጫ (ፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 213-223)

ለ. በአጭር ሁኔታ ስለሚደረጉ ክርክሮች (summary Procedure)

ሐ. የተፋጠነ ስነስርዓት (Accelerated Procedure)

ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት ሁለት አላማዎች አሉት እነሱም:-

1. ጉዳዮች እንደባህሪያቸው በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ፣
2. የፍርድ ቤትን ጊዜና ሃብት (Resource) እንደ ጉዳዮች ባህሪ ውጤታማ ማድረግ ናቸው፡፡

ስለሆነም ጉዳዮችን መምራት ያለባቸው ተከራካሪ ወገኖች ሳይሆኑ ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን ለመስማት ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ ጉዳዮች በእርግጠኝነት እንደሚሰሙ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የእርግጠኝነት ስሜት ለመፍጠር ጠንካራ የቀጠሮ አሰጣጥ ፖሊሲ መንደፍ አለባቸው፡፡

የጉዳዮች አካሄድ አመራር

- ውዝፍ መዛግብትን በመቀነስ (Back log)
- የማጣራት አቅምን በመጨመር (Clearance rate)
- የስራ ብዛትን በአግባቡ ለመቆጣጠር (Work load)
- ጊዜን የሰው ሃይልን ንብረትን በአግባቡ ለመጠቀም (Efficient utilization of frame human, material and financial resources)
- አፋጣኝ መፍትሄዎችን ለመወሰን (Immediate volition)
- ውጤታማነትን ለመለካት (Effectiveness)
- ጥሩ ውጤት ያመጡትን ለመሸለም የደከመውንም የእርምት እርምጃ ለመውሰድ (Motivation and Accountability) ጠቀሜታ አለው፡፡ ስለሆነም የፍታብሄር የፍትህ ስርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን የጉዳዮች አካሄድ አመራር ተግባራዊ ማድረግ

የግድ ይላል። ይህ በቀጣይ ራሱን ችሎ የሚታይ ስለሚሆን ከዚህ በላይ ማስፍት አልተፈለገም።

በመጨረሻ የፍታብሄር የፍትህ ስርዓቱ ተጠናክሮ በዘላቂነት እንዲቀጥል ከተፈለገ የዳኞች ነጻነት ተጠያቂነት አብሮ ማስኬድ ያስፈልጋል። የዳኞች የስራ አፈፃፀም ምዘናን መሰረት ያደረገ ተጠያቂነት በሁሉም ፍርድ ቤቶች ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል።

ከጠንካራ የፍታብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት መገንባት ጎን ለጎን አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችንም ማሰብ ተገቢ ይሆናል። በተለይም የዳኝነት ስርዓቱን ከማጠናከር ጐን ለጐን የዳኝነት ስርዓቱን የማያናጉ ለዳኝነት ሥርዓቱ መጠናከር አጋዥ የሆኑ ሕብረተሰቡም በቀላሉ ሊገለገልባቸው የሚችል የክርክር መፍቻ ዘዴዎች መሻት አስፈላጊ ነው ብቻም ሳይሆን የሁሉም አገሮች ተመኩሮ የሚያሳየንም ይህንኑ ሐቅ ነው።

ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች በሙሉ የሚስተናገዱባቸው ቢሆኑም ይህ ግን ዜጎች ከፍርድ ቤቶች ውጪ ጉዳዮችን እንዳይጨርሱ የሚገታ አይደለም። ይልቁንም በተቻለ መጠን በመካከላቸው የሚፈጠረው አለመግባባት ከፍርድ ቤቶች ውጪ እንዲጨርሱ ሊበረታቱ ይገባል። በመሆኑም በአገሪቱ ካሉ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጐን ለጐን አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት የሚደራጅበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል። አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ በብዙ ሃገራት ልምድ እንደሚታየው በተለይም አሁን ካለው የክርክር ብዛትና ውስብስብነት እንዲሁም በነባ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ከመገኘት ሰላማዊ የንግድ ልውውጥን ከማበረታታት አንፃር ያለው ጠቀሜታ በእጅጉ የላቀ ነው። ሌላው ጥቅሙም የፍርድ ቤትን ጊዜ ይቆጥባል ፍርድቤቶች ጊዜያቸውን በፍርድ ቤት ማለቅ ባለባቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ያግዛል። ስለሆነም ሃብት፣ ጊዜ ጉልበት በመቆጠብ ተጠቃሚ የሚሆነው አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴ የሚጠቀም ባለጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሌላው በፍርድ ቤት የሚጠቀመውን ተገልጋይም ጭምር ነው።

አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ከሚባሉት

- Negotiation
- Mediation
- Conciliation
- Arbitration የሚባሉት የሚገኙባቸው ሲሆኑ የእነዚህን ምንነትና እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በውስጣቸው ያለው ልዩነትና አንድነት በቀጣይ እራሱን

ችሎ የምታዩት በመሆኑ በዚህ ፅሁፍ ዘርዘር ባለ መልኩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ መጠቀም የሚኖረው ጥቅምና ሊያስከትለው የሚችል ጉዳት ምን ሊሆን እንደሚችል ብቻ ለመዳሰስ ይሞክራል።

7.4አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴ መጠቀም ያለው ጠቀሜታ፡-

ሀ. በቅልጥፍና አንፃር (Speed)

አንድ የተዋጣለት ጉዳይ በ (mediation) ለመጨረስ አንድ ቀን አንዳንድ ጊዜ ሁለት ቀን ይጨርሳል በልዩ ሁኔታ እስከ አምስት ቀን ሊራዘም ይችላል። ከዚህም ባጠረ ሁኔታ ባለጉዳዮች በሚያደርጉት የመግባባት ቅልጥፍና ሊያልቅ ይችላል የዚህ ዋንኛ ችግር የባለጉዳዮቹ ትጋትና ለመግባባት ያላቸው ዝግጁነት ነው። ባለጉዳዮች አንዱ መግባባት ላይ ከደረሱ ሁኔታዎች ካላስገደዱ በቀር ስምምነታቸው ወዲያውኑ ተፈፃሚ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም።

የቅልጥፍና ጉዳይ በንግዱ አለም በተለይ አሁን ካለው የግሎባላይዜሽን ውድድር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። አንድ የፋብሪካ አስተዳደር (ማናጀር) የክርክሩ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ካልቻለ በቀጣይ ለማቀድ አይችልም በተለይ ክርክሩ ረዥም ጊዜ የሚወስድ ከሆነም ውጤቱ በፋብሪካው ላይ የከፋ ይሆናል። በተለይ ለአንዳንዶቹ የንግድ ማህበረሰብ አባላት የክርክሩ መጓተት ወደ አልተፈለገ ኪሳራና ወደ ከፋ ተስፋ መቁረጥ ሊወስዳቸው ይችላል።

ለ. በወጪ አንፃር (Cost)

አንድ ጉዳይ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ መጠቀም በወጪ አንፃር እጅግ ጠቀሜታ ያለው ነው። ጉደዩ በሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፈለጉት ጊዜና ቦታ ስለሚካሄድ ጉዳዮንም በነሱ ፍላጎትና ትጋት ስለሚቋጭ ወጪው አንስተኛ ነው። ይህ ደግሞ ለንግዱ ማህበረሰብ ጠቀሜው ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው።

ሐ. ሂደቱን በመቆጣጠር አንፃር (Control)

ሁለቱም ባለጉዳዮች አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ሂደቱ ቀላል የተወሳሰበ ስነስርዓት የሌለው በራሳቸው አመራር የሚካሄድ በመሆኑ እጅግ

ከተወሳሰበና የተለያዩ የሥነስርዓት ሊገባቸውና ሊቆጣጠሩት ከማይቻል አስፈሪ የፍርድ ቤት አካሄድ ተመራጭ ነው።

ጉዳዮችን በፍርድ ቤት ሲያቀርቡ ጉዳዮን የሚመራው በዳኞች በመሆኑ ጉዳዩ የሚመራው ቀደም ሲል በተቀመጠው ስነስርዓት ነው። ውጤቱም በነሱ የመከራከር ብቃት፣ በሚያቀርቧቸው ምስክሮች ማስረጃዎች እንዲሁም በዳኞች የሕግ አረዳድ የሚመሰረት ነው።

አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ግን በዳኛው የሚመራውን የሙግት አካሄድ ራሳቸው ባለጉዳዮቹ ጉዳያቸው እንዲመሩ የሚያስችል ነው። ውጤቱም በራሳቸው የሚወሰን ነው።

መ. ግንኙነት በተመለከተ (Relation ship)

በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር ረቺና ተረቺ የሚያስቀምጠው ዳኛው በመሆኑ ይህ የረቺና ተረቺ መንፈስ በቀጣይነት የሁለትዮሽ ግንኙነት ወደ ቅራኔ በማምራት ከዚያም አልፎ ወደ አልተፈለገ ጠብና መቃቃር ሊያድግ ይችላል። በተለይ ይህ ደግሞ በንግዱ አለም ለማሰማሩ ሰዎች ሰላማዊ የንግድ ልውውጥ እንዳያካሂዱ እንቅፋት ይሆናል።

የአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ መጠቀም ግን ሂደቱን ራሳቸው ስለሚቆጣጠሩት ውሳኔውም የራሳቸው ፍላጎትና እምነት በመሆኑ በሁለት ተከራካሪ ወገኖች የሚኖረው ዝምድና ወደ ጠብና ጥላቻ የማደጉ አደጋ ይቀንሳል። አንዳንድ ጊዜም በዚህ የተጀመረው ግንኙነት ወደ ላቀ የስራ ግንኙት የሚያመራበት ሁኔታ ያጋጥማል (in some cases may even provide a forum for new and more creative future working relation ship to be established)

በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር በግልጽ ችሎት፣ በመስክሮችና በማስረጃ የተደገፈ በዳኛው የሚወሰን በመሆኑ በችሎት የተገኘ ሰው የሚያውቀው በመገናኛ ብዙሃንም ሊነገር የሚችል በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ በተለይ የካምፓኒውን ስም ወይም ዝና የማጉደፍ ባህሪ ይኖረዋል ከዚያም ተነስቶ ካምፓኒው በደንበኞቹ የነበረው መልካመ ስም (good faith) ይጠፋል ብቻም ሳይሆን ደንበኞቹም ይርቁታል ሌላውም ይበረግጋል በዚህ ምክንያት ወደኪሳራ ሊዳረግ ይችላል። (Litigation can also have implication for a company's image or reputation)

አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ግን ይህንኑ ባህሪ ስለማይከተል ጉዳዩ በመግባባት ስለሚያልቅ ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገን ሳያልፍ ምስጢሩ እንደተጠበቀ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ያለአንዳች ስጋት የነበራቸው መልካም ስምና ዝና ይዘው ሊቀጥሉ ይስችላቸዋል።

ሠ. አዳዲስ ዘዴዎችንና የተለያዩ አማራጮችን በማስቀመጥ አንፃር (Creative and forward looking solution)

በፍርድ ቤት የሚካሄድ ክርክር አስቀድሞ በተቀመጠ መደበኛ ሕግና ስነስርዓት ሕግ ስለሚካሄድ ለተከራካሪ ወገኖች ሕጉ ካስቀመጠው ውጪ አማራጮችን የሚሰጥ አይደለም። አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴ ግን ተከራካሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር የተያዩ አማራጮችን በማስቀመጥ ጉዳያቸውን ለመፍታት የሚያስችላቸው ነው። (the scope for settlement is wider, generating more posibilites and making settlement more likely).

Furthermore, it is logical that a settlement should reflect not only the strict legal positionn (or rather the parties percertion of it) but where possable their personal or commercial interests and needs as well.

ረ. ምስጢራዊነት በመጠበቅ አንፃር (Confidentiality)

የፍርድ ቤት ክርክር በግልጽ ችሎት ህዝብ በተሰበሰበበት ስለሚሰጥ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ አይደለም ሁለት ባለጉዳዮተ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ ተጠቅመው ጉዳያቸውን በመግባባት ከፈቱ ግን ምስጢራዊነቱ በተሻለ የተጠበቀ ይሆናል።

ADR is a private process, and this is frequently cited by parties as a reason for using it.

ሰ. በጉዳዩ ላይ ብቻ ተመስርቶ የማከራከር ሁኔታ (Discipline and focus)

በፍርድ ቤት የሚደረግ ክርክር በተወሰነ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ስለሚሆን ጉዳዮን ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማንሸራሸርና ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ ለማቅረብ አይቻልም። በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ግን በዋናው ጉዳይ ላይ ትኩረት

ሰጥተው የሚከራከሩ ቢሆኑም ሃሳባቸውን በተሟላ መልኩ ሳይገደቡ ለመግለፅና ወደ ጋራ መግባባት ለመድረስ ያስችላቸዋል፡፡

ሸ. ሁለቱም ወገን በጉዳዩ የመርካትና ተገቢውን መልስ የማግኘት ሁኔታ (Satisfaction and Compliance)

አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ለተከራካሪ ወገኖች ከፍርድ ቤት ክርክር ይበልጥ እርካታን ይሰጣል፡፡ (ADR processes are often more satisfying to the parties than a trial or hearing for many reasons. The focus and relief of reaching settlement, and of doing so by consumers, find to penetrate very high levels of satisfaction)

ሌላው ደግሞ ስምምነቱ በጋራ መግባባት ስለሚደረግ በአፈፃፀም ላይ ችግር አያጋጥምም፡፡ since any settlement is reached by consenous, it follows that the implementation or enforcement is much less likely to be a problem than it is where judgment is imposed.

ምንም እንኳን አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ጠቃሚነቱ አጠያያቂ ባይሆንም አደጋ የለውም ማለት ግን አይደለም፡፡

1. የመጀመሪያው አደጋ አንዱ ባለጉዳይ የሌላውን ተከራካሪ ወገን አጠቃላይ ጥንካሬና ድክመት ገምግሞ የሚያዋጣኝ በፍርድ ቤት ብከራከር ይሻላል ወደሚል አዝማሚያ ሊያመራ ይችላል፡፡ “I will disclose my hand” እንደሚባለው የፈረንጆች አባባል፡፡
2. ሌላው አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድን እንደማዘግያ ስልት የመጠቀም ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ (ADR is merely a delaying tactic)
3. ወጪን በመቀነስ አንፃር ዋስትና አለመኖር “there are no real cost savings”
4. ነገር ግን በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ለመፍታት ተዕዕኖ እንደማሳረፊያ መጠቀም “there is pressure to settle”
5. አንዱ ወገን የያዘው ሙግት ደካማና ተጠያቂ እንደሚሆን የሚያደርግ ተዕዕኖ መፍጠሪያ (“I will give the impression of weakness or liability”) በአጠቃላይ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴን ከጉዳቱ ጥቅሙ የሚያመዝን ቢሆንም ይህንን ለመጠቀም መጀመሪያ ዘዴዎቹን በሚገባ ማወቅና ጠንካራና

ደካማ ገኑን መርምሮ የማያዋጣውን መምረጥ ይበጃል። በሃገራችን ሕጎችም ማለትም በፍትሐብሔር የመደበኛውና በስነስርዓት ሕጉ ውሱን መልኩ የተቀመጡ ቢኖሩም በብዛት ስንጠቀምባቸው አይታይም ከዚያም ባሻገር የተለያዩ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ስለማንጠቀም ሁሉም ጉዳዩን በፍትሕ በፍርድ ቤት ብቻ እንዲያልቅ ስለሚፈለግ አማራጭም እስካልተቀመጠለት ፍርድ ቤቶች ቀላሉንም ከባዱንም ጉዳይ እያስተናገዱ በመዛግብት ተጥለቅልቀው ይገኛሉ። የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ስርዓቱ እንዲጠናከር ከተፈለገ ይህ በቀጣይ ጥናት ተደርጎበት መወገድ ያለበት ይሆናል።

ሌላው አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች አብሮ ሊታይ የሚገባው አነስተኛ ጉዳዮችን የሚያይ ተቋም መኖር ነው። (small class tribunals) ከብዙ አገሮች ልምድ እንደሚታየው ቀለል ያሉ ጉዳዮች ጠበቅ ያለ የዳኝነት ስርአት መከተል ላያስፈልጋቸውና የባለሙያን ጊዜ ሳይሻሙ ከሕብረተሰቡ ከራሱ በተሰጠው ወይም በሌላ መንገድ በሚደራጅ ተቋማት እንዲያልቅ ይደረጋሉ። የህብረተሰቡ በነዚህ ተቋማት ያላንዳች ውጣ ውረድ በቀላሉ ይገለገላል ተወራሽ ጊዜንና ወጪውንም ቆጣቢ ናቸው። ውጤታማም ናቸው። በኛ አገርም በቀላሉ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚጫወቱት ሚና መጥቀሱ ይበቃል።

ማጠቃለያ

በሃገራችን ኢትዮጵያ በፍትህ ስርዓት የማሻሻያ ኘሮግራም በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ የለውጥ ጅምር በመታየት ላይ ቢሆንም የተጀመረው የማሻሻያ ኘሮግራም ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሂደቱ በሚገባ እየተገመገመና እየተጠናከረ መሄድ ይኖርበታል። የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ሕገ-መንግስቱ ሊያረጋግጠው የሚፈልገውን ሰላም ዲሞክራሲና ፈጣን ልማት ጋር ተቀራኝቶ መሄድ ይኖርበታል። የፍትሕ ስርዓቱ ራእይ ከአጠቃላይ የሃገሪቱ ራእይ ጋር ተቃኝቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል። በተለይም ለጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት እውን መሆን በአስተሳሰቡ የበሰለ የሰው ሃይል መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ይህም ለማሳካት አሁን የተጀመረው የዳኞችና የአቃቤ ሕግ ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል። ሃገራችን ከድህነት ለመውጣት በምታደርገው የሌት ተቀን እንቅስቃሴ የፍትህ ስርዓቱም ልማቱ ሳይደናቀፍ እንዲራመድ የሕግ ከለላ ሊያደርግለት ይገባል። ጠንካራ የፍትሐብሔር

የፍትሕ ሥርዓት ለሰላምም ለዲሞክራሲም ለልማትም እንዲሁም የሰዎች አምባገነንነት ተወግዶ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ እንዲያገለግል በማመን ሁሉም ለጠንካራ የፍትሐብሔር የፍትህ ስርዓት በሃገራችን እውን ሆኖ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል። እንደአንዳንድ ምሁራን አገላለፅ

With out an effective justice sector to enforce and regulate human conduct the environment in which people live is unsafe and in secure and inhibits wealth creation. It is increasingly accepted that economic development is dependent on a stable and just society.

ጠንካራ የፍታብሔር የፍትሕ ስርዓት እንዲገባ ከተፈለገ ወደ በሶስት አበይት ነገሮች ላይ የጋራ መግባባት መድረስ ይኖርበታል።

- በቅድሚያ የችግሮቹን አአንጥር ማውጣትና በችግሮቹ የጋራ መግባባት መድረስ
- ችግሮቹን ለመቅረፍ በሚወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦችም እንዲሁ የጎራ መግባባት መድረስ
- ችግሮቹን ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴም ተማኝነትና ተነሳሽነትን ማሳየት ያስፈለጋል። ይህ ካልተደረገ እንደ አንደአንዳንድ ምሁራን አባባል ስልጠና፣ የኮምፒተር ጋጋታና የሰው ሃይል ብዛት ብቻውን ለውጥ ማምጣት አይችልም። Training, improving management system and supplying computers and other resources to the justice sector had little impact in countries where a concerns for reform was lacking (Blair and Hansen) Bas caglia, Dakolias, and Ratlify (1995) report that latin American judges often guestirned the volume of training in the absence of more fundamental reform in the judicial system. In many cases, once a judge and been trained, he or she quicfly left the bench for a more we rative position in private bar or private sector.

በአንዳንድ አገሮች የፍትሕ ማሻሻያ ስርዓት እንደታየውም ሁሉም ስልጠና ይፈለጋል። ስልጠናን የሚፈልገው ግን በስልጠናው እውቀቱን ክህሎቱንና አስተሳሰቡን አጎልብቶ

ለፍትሕ ስርዓቱ መሻሻል የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ሳይሆን በስልጠናው ያገኘውን እውቀት ተጠቅሞ ወደተሻለ ስራና ወደተሻለ የገቢ ምንጭ አለበት ወደሚለው ጥብቅና ወይም የግል ሴክተር ይሸጋገራል ይህም አንዳንድ በፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ጥረት ያደረጉ ሰዎች እንዲህ በማለት ይገልፁታል።

የመጀመሪያ ቀን የውይይት ጥያቄዎች

1. በሲቪል ሎው እና በኮመን ሎው የህግ ስርዐት ያለውን ልዩነት አስመልክቶ እንዴት ትገነዘቡታላችሁ?
2. *ሀገራችን ከምትከተለው የፍትሐ ብሔር የፍትህ ስርዐት አንፃርስ ምን ግንዛቤ አላችሁ?*
3. *በመሰክ ጉብኝት ወቅት በተቋማት ውስጥ ያለው የፍ/ብሔር ፍትህ አሰተዳደር ምን እንደሚመስል ግለፅ።*

የሁለተኛ ቀን የውይይት ጥያቄዎች

1. በአንዳንድ የህግ ምሁራን በሀገራችን የፍታሐ ብሐር የፍትህ አስተዳደር ስርዐት ኋላቀር ሊሆን የቻለው ሲቪል ሎው ሰለምንከተል ነው የሚል አስተያየት ሊዘረዝሩ ይሰማል በዚህ ሃሳብ ምን ያህል ትስማማላችሁ ?የምትስማሙ ከሆነ ምክንያቱን የማትስማሙ ከሆነም ምክንያቱን በመግለፅ አስረዱ?
2. በውል ሕግ በንብረት ሕግ በአሰሪና ሠራተኛ ሕግ የሀገራችን የፍታብሐር የፍትሕ ስርዓት የሚከተለው አግባብ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ጋር በማዛመድ አብራሩ? ያላችሁን አስተያየት ከምታውቁት ተጨባጭ አብነቶች ጋር በማዛመድ ብትገልፁት ይመረጣል
3. በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሃገራት የፍታሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት ኋላ ቀር መሆን ተፅኖዎ ሊያሳድር የሚችሉ ክስተቶችን ከነመፍትሔ ሃሣቦቻቸው አስቀምጡ ?

የሶስተኛ ቀን የውይይት ጥያቄዎች

1. ጠንካራ የፍታብሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር ከደካማ የፍታብሔር የፍትህ አስተዳዳር ስርዐት የሚለይበት ሁኔታ በጊዜ አንፃር አስቀምጡ
2. አሁን ያለው የሀገራችን የፍታብሔር የፍትህ አስተዳደር ስርዐት
   - በተደራሽነት
   - በቅልጥፍና
   - በተገማችነት
   - ሕግን መሠረት አድርጎ በመሄድ
   - ባጠቃላይ በውጤታማነትና በፍ/ሰበር አቤቱታ አንፃር እንዴት አገመጉመታላ----
   - ከተጨባጭ አብነት ጋር በማዛመድ ለመወያየት ሞክሩ

የአራተኛ ቀን የውይይት ጥያቄዎች

1. ለፍታብሐር የፍትህ አስተዳደር ስርዓት ጥንካሬና መልካም መሆን
   - የጠበቃ
   - የዓቀቤ ህግ
   - የዳኞች
   - የነገረ ፈጅዎች
   - የምስክሮች ሚና የላቀ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል በሃገራችን የነዚህ አባላት ሚና በጠንካራና በደካማ ጐኑ የሚታይ አለ የምትሉትን አብራሩ
   - አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች የሀገራችን ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚየደርጉ መስናክሎች ምንድ ናቸው ትላላችሁ? ተግባራዊ እንዲሆኑ ምን ቢደረግ ይኖርበታል?
   - ለፍታሐ ብሔር የፍትህ አስተዳደር ስረዐት መጠናከር የዩንቨርስቲዎች እንዲሁም የሌሎች ትምህርት ተቋማት ሚና ምንድ ነው ትላላችሁ?